Barruu Nasiihaa
www.nesiha.com

# ነሲሐ

የዕውቀት ማዕድ

ቅጽ 1 ቁጥር 2 ግንቦት 2011

## አንድነት፣መተባበር እና ኺላፍ

### በሸሪዓዊ መርሆዎች እና በተዛቡ ግንዛቤዎች መካከል



## የኮንዶሚኒየም ቤትን በረጅም ጊዜ ክፍያ መግዛት በሸሪዓ እይታ

በሸይኽ ኢልያስ አሕመድ



## የዘረኝነት ማጥ

ፆም እና ዘካን የተመለከቱ ጠቃሚ መልዕክቶች



ነሲሓ
የዕውቀት ማዕድ
ቅጽ 1 ቁጥር 2 |
ግንቦት 2011
WWW.NESIHA.COM

# በውስጥ ገጾች


## አንድነት መተባበር እና ኺላፍ በሸሪዓዊ መርሆዎች እና በተዛቡ ግንዛቤዎች መካከል 12

## የዘረኝነት ማጥ 15

## የኮንዶሚኒየም ቤትን በረጅም ጊዜ ክፍያ መግዛት በሸሪዓ እይታ 17

## ዝክረ ረመዳን

| | |
|---|---|
| የፆም መደንገግ ጥበቦችና ጥቅሞቹ | 5 |
| አምስቱ የወርሀ ረመዳን ትሩፋቶች | 6 |
| ስለ ፆም አጭር ማብራሪያ | 7 |
| የዘካ ህግጋት | 9 |
| ዘካተል ፊጥር እና አፈጻጸሙ | 10 |

## ነሲሓ ቤተሰብ

| | |
|---|---|
| ጤናማ ትዳር | 20 |
| የልጆችዎን በራስ የመተማመን ስነ-ልቦና ለመገንባት የሚረዱ ነጥቦች | 21 |
| ቤተሰቦቼ አስገድደው ሊድሩኝ ነው ምን ላድርግ? | 22 |
| ከእጹብ ድንቆች ማህደር | 23 |
| ሸይኽ ሙሐመድ ሸይኽ | 24 |

## ✍ ነሲሓ ብዕር

| | |
|---|---|
| ኢስላም ልዩ ነው! | 26 |
| በአላህ ስሞችና ባህሪዎች ዙሪያ አስፈላጊና መሰረታዊ ህጎች | 27 |
| አቡበክር አስሲዲቅ | 29 |
| የህፃናት አመጋገብ | 30 |
| የቁርኣንና የተውሒድ ቁርኝት | 30 |
| ፈታዋ | 31 |




# አዲኑ ነሲሓ

ያለንበት ታላቁ የረመዳን ወር እንደመሆኑ ሙስሊሙ እንደተለመደው በስፋት የኸይር እና የኢባዳ ቦታዎችን በማዘውተር ላይ ነው። የቁርአን ወር ነውና ሰዎች ቁርአንን ለመተዋወስ ይሰባሰባሉ። ይህንን ዕድል በመጠቀም ዱዓቶች እና የቁርአን አስተማሪዎች ያለባቸውን ከፍተኛ ኃላፊነት ሊወጡ እንደሚገባ ልናስታውስ እንወዳለን።

ሙስሊሙ ማህብረተሰብ ለረጅም ጊዜ ሲጠይቅ የነበረው መሪ ተቋሙን ከተፅዕኖ ማላቀቅ እና ሁሉንም አሳታፊ ይሆን ዘንድ ስር ነቀል ተሀድሶ የማድረግ ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ለውጡ መተግበር በመጀመሩ ሙስሊሙ አላህን ሊያመሰግን ይገባል። ኢብኑ መስኡድ ኢስላሚክ ሴንተር ከሰሞኑ ለውጡን በማስመልከት ባስተላለፈው መልዕክት አፅንኦት ከሰጠባቸው ነገሮች አንዱ የኡለማዎች የስምምነት ሰነድ ሁሉንም የሚያግባባ ይሆን ዘንድ መሰረት ሊያደርግ የሚገባው፤ ማእከላዊውን የቀደምት ሰለፎች የአህሉሱና ወልጀማዓ አካሄድ እንጂ የሰሐባ እና ታቢዒይ ትውልዶች ካለፉ በኋላ የመጡ ፈረቆችን አካሄድ እንዳልሆነ ነው። ነሲሓ መጽሔት ይህንኑ አሰባሰቢ ሀሳብ ማህበረሰቡ በሚፈለገው መጠን ይገነዘበው ዘንድ ትሠራለች።

'አህሉሱና ወል ጀማዓህ" የሚለውን መገለጫ አንዳንድ ወገኖች ከትክክለኛው ትርጉሙ ተቃራኒ በሆነ መልኩ ለራሳቸው ቡድን መጠሪያነት ሲጠቀሙበት ይታያል። ስለሆነም ትክክለኛው የአህሉሱና ወልጀማዓህ ምንነትና እምነት ምን እንደሆነ አፅንዖት ሰጥተን ማወቅ እንዳለብን ይሰማናል።

የአህሉሱና ወልጀማዓህ እምነት መልዕክተኛው ﷺበመጡበት በአላህ መጽሐፍ (ቁርኣን) እንዲሁም በመልዕክተኛው ﷺፈለግ (ሱና) መሰረት በመጡት ሁሉ ማመን ነው።

"አህሉ'ሱንና ወ'ል ጀማዓህ" በሚለው ቃል የምናስበው ስለቀናነታቸው እና ስለ ዓርአያነታቸው የተመሰከረላቸውን ሶሓቦችን፣ ታቢዒዮች እና በበጎ የተከተሏቸውን የዚህ ኡማ አበው ትውልድ አኢማዎችን ነው። ከነርሱም መካከል፤ የአራቱ የፊቅህ መዝሃቦች ኢማሞች፣ እንደ አል-ለይሥ ኢብኑ ሰዕድ፣ ኢብኑል ሙባረክ፣ አል-ፉደይል ኢብኑ ዒያድ፣ኢስሓቅ ኢብኑ ራሐወይህ፣ ሁለቱ ሱፍያኖች፣ ሁለቱ ሐምማዶች፣ አቡ ዑበይድ፣ ወኪዕ፣ አል-ቡኻሪ እና ሙስሊም ያሉ ታላላቅ ልሂቃን፣ ከነሱም በኋላ የመጡ ታላላቅ የዲን መሪዎች የሚጠቀሱ ሲሆን በጥቅሉ በፋናቸው ላይ የሚጓዘውን መላውን ህዝበ ሙስሊም የሚያካትት ገለፃ ነው።

አህሉሱና/የሱና ሰዎች ተብለው የተሰየሙበት ምክንያት የመልዕክተኛውን ﷺሱና በመያዛቸው ሲሆን አህሉል ጀማዓህ/ የህብረት ሰዎች የተባሉት ደግሞ በሐቅ ላይ በመሰባሰባቸው ነው።

ትክክለኛውን የአህሉሱና ወል ጀማዓህ እምነትና አካሄድ ማሰራጨት የነሲሓ መጽሔት ዋነኛ አላማ በመሆኑ ሙስሊሙን ኡማ መሰረቱ በደነደነ አንድነት ላይ ለማፅናት የሚደረጉ ጥረቶችን ከመደገፍ አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖራት ዘንድ ራዕያችን ነው።

**የዝግጅት ክፍሉ**


**በአል ሐበሻ ሚዲያና ኮሚዩኒኬሽን ኃ.የተ.የግ.ማህበር እየተዘጋጀ የሚቀርብ መጽሔት**

**ዋና አዘጋጅ**

ናስር ሱለይማን

አድራሻ፡ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 1620

**ኤዲቲንግ ማኔጀር**

ሳላሕ አሕመድ

**ሲኒየር ኤዲተር**

አሕመዲን ከድር

**ሽያጭና ስርጭት**

አንዋር ወልዳይ

09 10 47 82 83


**ስለ እኛ**

ነሲሓ መጽሔት፤ የነብያት ውርስ የሆነውን ሸሪዓዊ ዕውቀት ከምንጩ በመቅዳት ለሕዝባችን ማድረስ ፤ ኡማውን ለሚገጥሙት ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች መፍትሄዎችን ማመላከት እና ቀናውን የሰለፎች ጎዳና ማብራራት የነሲሓ መጽሔት ተቀዳሚ ተልእኮ ነው። ሙስሊሙ ማህበረሰብ በዲናዊም ይሁን ዱንያዊ ጉዳዮች ላይ ብቁ እንዲሆን የበኩሏን ትወጣለች። ለሚያጋጥሙት የተለያዩ ፈተናዎች መፍትሄዎችን ታመላክታለች። በነሲሓ መጽሔት የተለያዩ ኡስታዞችና አምደኞች ጠቃሚ መልዕክቶችን ያስነብባሉ።


**ግራፊክስ ዲዛይን**

ሐይደር ከድር

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**

ኮ/ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፤ ወረዳ 7 ሳራ የገበያ ማዕከል ቢሮ ቁጥር 315

# ተቋማዊ ለውጡን በተመለከተ ከኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር የተላለፈ መልዕክት

الحمد لله رب العالمين، والصلاة والسلام على أشرف الأنبياء والمرسلين، نبينا محمد وعلى آله وصحبه أجمعين، أما بعد:

## አልሐምዱሊላህ. . .

ሚያዝያ 23/8/2011 በአላህ ፈቃድ በተገኘው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማዊ ለውጥ የተግባራዊነት ጅማሮ የተሰማንን ደስታ በመግለፅ ለመላው ሙስሊም ማህበረሰብ እንኳን ደስ ያላችሁ እንላለን።

በዘመናት ትግልና ርብርቦሽ የተደረሰበት ይህ አዲስ ምዕራፍ ለሰፊው ሙስሊም ህብረተሰብ ረጅም የወደፊት ጉዞ መቃናት የሚተገብረውን የጎላ ሚና እና አመዛኝ ጥቅም በማሰብ ሁሉም ወገኖች ለዚህ ግብአት የሚሆኑ አዎንታዊ ተሳትፎዎችን እንዲያበረክቱ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የጋራ ተቋሙ ሊደራጅ የሚገባው ፍትሀዊ አስተዳደርን እውን በማድረግ እንደሆነ እናምናለን። ተቋሙ አካታች በሆነ ተሃድሶ ተጠናክሮ ከዚህ በፊት የነበሩ ብልሹ አሠራሮችን በማስቀረት መላውን ሙስሊም ማህበረሰብ በብቃት የሚያገለግል የጋራ መጠለያ ይሆን ዘንድ ምኞታችን ነው።

በቀጣይ ይህ ለውጥ ክልሎችን ጨምሮ በሁሉም የመጅሊሱ መዋቅሮች ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ በማመቻቸት ከዚህ ቀደም በነበረው ጫና ከየመስጂዱ ለረጅም ጊዜ የተገለሉ ኢማሞችን እንዲሁም ከህብረተሰቡ የተነጠቁ መስጂዶች እና ተቋማትን በተመለከተ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ አዲሱ ምክር ቤት ከተቀዳሚ ተግባራቱ ውስጥ ሊያደርገው እንደሚገባ አደራ እንላለን።

ለኢስላማዊ አንድነት መጣር በጥብቅ የታዘዘ መሆኑን ከማፅናታችን ጋር የእምነት አንድነትን ወይም መቀራረብን ስናስብ በሂደቱ መሰረታዊ የዲን አጀንዳዎች ላይ መደራደር እና ሸሪዓ ከተገነባበት ሚዛናዊው ምልከታ መንሸራተት እንዳይኖር ጥንቃቄ ያስፈልጋል። አላህ በነብያት አማካይነት ሕዝቦችን ወደ አንድነት ሲጠራና ከመለያየት ሲከለክል የዲንን ድንበሮች እንዲጠብቁ ከማዘዝ ጋር በማቆራኘት ነውና። ጌታችን እንዲህ ብሏል:-

شَرَعَ لَكُم مِّنَ ٱلدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِهِۦ نُوحا وَٱلَّذِيٓ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ وَمَا وَصَّيۡنَا بِهِۦٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰٓۖ أَنۡ أَقِيمُواْ ٱلدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُواْ فِيهِۚ

*«ለእናንተ ከሃይማኖት ያንን ኑሕን ያዘዘበትን (አደራ)፣ ያንንም ወዳንተ ያወረድነውንና ኢብራሂምን፣ ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን "ሃይማኖትን በሚገባ አቋቁሙ፤ በእርሱም ላይ አትለያዩ" ማለትን ደነገገ፡፡»* (አሽ ሹራ፡13)

ተቋማችን ኢብኑ መስኡድ ኢስላሚክ ሴንተር ከዚህ ቀደም በህዳር 2011 በሙስሊሙ መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ታስቦ በተዘጋጀው የዑለማዎች የመግባቢያ ሰነድ ላይ ያለውን አስተያየት እና ግምገማ በዝርዝር ማቅረቡ ይታወሳል።

ምንም እንኳን በወቅቱ ኮሚቴው ከቀረቡት ገንቢ ግምገማዎችና ጥቆማዎች አብዛኛዎቹን በመጨረሻው ሰነድ ላይ እንዲካተቱ ባያደርግም ተቋማችን እነዚህን ግምገማዎች እና የመፍትሄ ሀሳቦች ይበልጥ አጠናክሮ ለአዲሱ የዑለማዎች ምክር ቤት ለማቅረብና በሁሉም መስክ የሚጠበቅበትን ገንቢ አስተዋፅኦ ለማበርከት ያለውን ዝግጁነት ይገልፃል።

የተቋማዊ ለውጥ ኮሚቴው ለውጡ እንዳይደናቀፍ በማሰብ ሂደቱ ይቋጭ ዘንድ በአንዳንድ ወገኖች የቀረበውን ቡድናዊ ጥያቄ ለማካተት አግባቢ እንዲሆኑ ታስበው የተቀመጡ ሦስት አማራጭ ገለፃዎችን አባሪ አድርጎ አዲሱ የዑለማ ምክር ቤት ይመክርበት ዘንድ ውሳኔ አስተላልፏል። አዲሱ አባሪ ፍፁም አላስፈላጊ መሆኑን በአፅንኦት እየገለፅን፣ ተገቢ ያልሆነ ምስክርነትን ያቀፈና ለአንደኛው ወገን ከማንኛውም ሂስ እና እርምት ከለላ የሚሰጥ ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም በብዙ መስዋዕትነት የተደረሰበት የስምምነት ድባብ እንዳይደፈርስ ከመጠንቀቅ አንፃር በዋናው ሰነድ ላይ እንደተገለፀው በቁርኣን በሐዲሥና በኢጅማዕ ላይ የተመሰረተ፣ ገለፃውም ሁሉንም ወገኖች በሚያስማማው የአህሉ'ሱና ስያሜ ላይ የተገደበ ይሆን ዘንድ ያለንን ፅኑ ፍላጎት እንገልፃለን።

ለዚህ ታሪካዊ የተቋም ተሀድሶ እና ለውጥ አስተዋፅኦ ላበረከቱ አካላት ሁሉ ምስጋናችን የላቀ ሲሆን አላህ መልካም ምንዳን ይከፍላቸው ዘንድ እንለምነዋለን።

መጪው ረመዳን መልካም ለውጦችን የምናይበት፣ የሰላም እና የመልካም ሥራ ወር ይሆንልን ዘንድ አላህን እንማፀናለን።

ኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር

ሚያዝያ 25/8/2011

ቅጽ 1 ቁጥር 2 | ግንቦት 2011

# ዝክረ ረመዳን

## የረመዳን ልዩ መልዕክቶች

## የፆም መዳንገግ ጥበቦችና ጥቅሞቹ

ከአላህ ስሞች መካከል አንዱ “አል-ሐኪም” የሚለው ነው። “አል-ሐኪም” በመባል የሚጠራው በጥበብ የሚገልጽ አካል ነው። ጥበብ (ሒክማ) ማለት ደግሞ ነገሮችን አሳምሮና አስተካክሎ በየቦታቸው ማኖር ነው። ይህ የአላህ ስም የሚያስገነዝበን እርሱ የፈጠረው ማንኛውም ፍጥረትም ይሁን የደነገገው ድንጋጌ ሁሉ እጅ ግ ለላቀ ጥበብ እንደሆነ ነው። ያወቀ ቢያውቅውም ያላወቀ ባያውቀውም!

አላህ በባሮቹ ላይ የደነገገው እና ግዴታ ያደረገው ፆም በውስጡ ታላላቅ ጥበቦችን እና እጅግ በጣም ብዙ ጥቅሞችን አካቷል።

**ከፆም መደንገግ ጥበቦች መካከል፡**- አንድ ባሪያ በተፈጥሮ እንዲወዳቸው ተደርጎ የተፈጠረባቸውን እንደ ምግብ፣ መጠጥ እና የግብረ ስጋ ግንኙነት ያሉ (ስጋዊ) ፍላጎቶቹን ወደጎን በመተው የጌታውን ውዴታ ለማግኘት እና የተከበረውን አገር ጀነትን ለመታደል ወደርሱ የሚቃረብበት የአምልኮ ተግባር መሆኑ ነው። በዚህ ተግባሩም ነፍሱ ከምትወዳቸው ነገሮች ይልቅ ጌታው የሚወደውን ከቅርቢቱ ዓለም (ዱንያ) ይልቅ የወዲያውኛውን ዓለም (አኼራን) ማስበለጡ ግልፅ ይሆናል።

**ከፆም መደንገግ ጥበቦች መካከል፡**- አንድ ባሪያ የፆም ግዴታውን በሚገባ ከተወጣ የጌታውን ፍራቻ (ተቅዋ) የሚያገኝበት ምክንያት መሆኑ ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

*«እናንተ ያመናችሁ ሆይ ፆም በእነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነገገ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡»(አል-በቀራ፡ 183)*

ፆመኛ አላህን እንዲፈራ ታዟል። እሱም የአላህን ትዕዛዛት መታዘዝ እና ክልከላውን መራቅ ነው። ከፆሙም በዋነኝነት የሚፈለገው ትልቁ ዓላማ እርሱ ሲሆን በአንፃሩ ፆመኛው ምግብን፣ መጠጥን እና የግብረ ስጋ ግንኙነትን በመተው እንዲሰቃይ አይደለም። ነብዩ(ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የሀሰት ንግግርን፣ በሀሰት መሥራትን እንዲሁም የመሀይማንን ተግባር ያልተወ ሰው ምግቡንና መጠጡን ከመተዉ አላህ ጉዳይ የለውም። (ቡኻሪ ዘግበውታል)

የሀሰት ንግግር (قول الزور) የሚለው ሀራም የሆኑ እንደ ውሸት፣ ሀሜት፣ ስድብና ሌሎችም በሸሪዓ የተከለከሉ ነገሮችን መፈጸምን የሚያጠቃልል ነው።

**በሀሰት መሥራት** (العمل بالزور) የሚለው ደግሞ ማንኛውንም በሰዎች ላይ ድንበር ማለፍ ያለበትን እንደ መክዳት፣ ማታለል፣ ሰዎችን መደብደብ፣ ገንዘባቸውን መቀማት እና የመሳሰሉትን ይመለከታል። በተጨማሪም በሸሪዓ መስማት የተከለከሉ እንደ “አል-አጋኒ" ዘፈንና መሰል (በሙዚቃ መሳሪያ የተቀነባበሩ) ነገሮችን መስማትም እዚህ ውስጥ ያካትታል። አልመዓዚፍ (**المعازف**) ማለት የሙዚቃ መሳሪያዎች ማለት ነው። ጀህል (**الجهل**)ማለት ደግሞ ማይምነት (ድንቁርና) ሲሆን በንግግርም ይሁን በተግባር ከትክክለኛው አቋም መራቅን የሚያመለክት ቃል ነው።

አንድ ፆመኛ ከላይ በተጠቀሰው የቁርአን አንቀፅና ሐዲስ መሰረት ከተጓዘ ፆሙ ነፍስን ማስተካከያና መኮትኮቻ፣ እንዲሁም ስነ-ምግባሩን የሚገራበት፣ አካሄዱን የሚያቀናበት ይሆናል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከረመዷን በኋላ በስነ-ምግባሩ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ (መሻሻል) ይታይበታል ማለት ነው።

**ከፆም መደንገግ ጥበቦች መካከል፡**- የሃብት ባለቤት የሆነ ግለሰብ በርሱ ላይ አላህ የዋለው ፀጋና ስጦታ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ይረዳበታል። ይህም የሚሆነው ግለሰቡ የፈለገውን እና የተፈቀደለትን መብላት እና መጠጣት እንዲሁም ከተፈቀደለት አካል ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነትን ማድረግ በፈለገ ሰአት እንዲያገኝ አላህ ያገራለት መሆኑን ስለሚያስተውልበት ነው።

> **“የሀሰት ንግግር” የሚለው ሀራም የሆኑ እንደ ውሸት፣ ሀሜት፣ ስድብና ሌሎችም በሸሪዓ የተከለከሉ ነገሮችን መፈጸምን የሚያጠቃልል ነው።**

ስለሆነም ጌታውን ያመሰግናል፣ ይህንን ማግኘት ያልቻለውን ድሃ ወንድሙን ያስታውሳል በዚህም የተነሳ ለሱ ምፅዋትን (ሰደቃን) ይሰጣል እንዲሁም መልካም ተግባራትን በመፈፀም የቸርነትን ባህሪ ይላበሳል።

**ከፆም መደንገግ ጥበቦች መካከል፡**- የሰው ልጅ እንዴት አድርጎ ነፍሱን (ስሜቱን) መቆጣጠር እና ሙሉ ለሙሉ በርሱ የበላይነት ስር በማዋል ለርሱ በቅርቢቱ ዓለምም (ዱንያ)ም ይሁን በወዲያኛው ዓለም (አኼራ) መልካም እንዲሁም ስኬታማ ወደ ሆነው አቅጣጫ መምራት እንደሚችል የሚለማመድበት መድረክ መሆኑ ነው። በዚህም ነፍሱን ከፍላጎቶቿ መከልከል የማይችል እንስሳዊነት የተጠናወተው ሰብአዊ ፍጡር ከመሆን ይልቅ ለርሷ ጠቃሚ የሆነውን ወደ ማሟላቱ ያዘነብላል።

**ከፆም መደንገግ ጥበቦች መካከል፡**- ፆመኛ ምግብን በመቀነሱ የተነሳ ጨጓራ እና መሰል የምግብ መፈጨት ሂደት የሚከናወንባቸው የሰውነት ክፍሎች ለተወሰነ ጊዜ እረፍት ያገኛሉ በተጨማሪም አንዳንድ ለሰውነት አላስፈላጊ የሆኑ በሰውነት ውስጥ የሚገኙ እንደ ስብ እና መሰል ትርፍ ጎጂ ነገሮች ይወገዳሉ፡፡ እነዚህ ከጤና ጋር ተያያዥነት ካላቸው የፆም ጥቅሞች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

------------*********------------

## ዝክረ ረመዳን አፕ

ረመዳን መጣ ‼ ረመዳን መጣ ‼ ረመዳን መጣ

**የተከበረውና በጉጉት የሚጠበቀው ረመዳን እነሆ መጣ!**

✓ "በረመዳን አምኖና (ከአላህ ምንዳን) ፈልጎ (ሌሊቱን) የሰገደ የቀደመው ወንጀል ይማርለታል" ብለዋል ነብዩ -ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም-

✓ በረመዳን ሸይጧን ይታሰራል፣ ጀሀነም ትዘጋለች፣ አላህ ጀነትን በየቀኑ ለምእመናን ያስውባል ....

✓ የፆመኛ አፍ መዓዛ እንደሚስክ ማራኪ ይሆናል፣ ጿሚዎች እስኪያፈጥሩ መላኢካዎች ምህረት ይለምኑላቸዋል፣ በማፍጠሪያ ሰአት የሚያደርጉት ዱዓም ተቀባይነት ያገኛል ...

✓ በረመዳን ወር ብቻ በምትገኘው ለይለተል ቀድር የሚሰራ ዒባዳ ከ1000 ቀናት አምልኮ ይበልጣል! ሌላም ሌላም ....

### → ታዲያ ይህን በረከት ለመቋደስ ምን ያህል ተዘጋጅተዋል?

ስለ ረመዳን ፆም ህግጋት፣ ፆም ስለሚያበላሹ ነገሮች፣ ፆም የሚያስፈቱ በቂ ምክንያቶች፣ በፆም ወቅት ስለሚወደዱና ስለሚጠሉ ሥራዎች፣ ስለ መጨረሻዎቹ አስር ቀናት፣ ኢዕቲካፍ፣ ዘካተልማል፣ ዘካተል ፊጥር እና የዒድ አከባበር ደምቦች በቀላሉ የሚያሳውቅዎ የሞባይል መተግበሪያ/App እነሆ መጣልዎ!

### ዝክረ ረመዳን የሞባይል አፕ!

ፆም ኢባዳ እንደመሆኑ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ዕውቀትን መሰረት ያደረገ መሆን አለበትና ይህንን አፕ እውርደው ጠቃሚ ዕውቀት ይገብዩ!

◆ አፑ በመጠን አነስተኛ ሆኖ ብዙ ትምህርተቶችን ያቀፈ ሲሆን፤ ፆምን አስመልክቶ ...

1 የተለያዩ መጣጥፎች

2 በራሪ ወረቀቶችና

3 አጫጭር የድምፅ መልዕክቶችንና

4 የኦሮሚኛ እና ትግርኛ ፅሁፎችንም የያዘ ነው።

شَهْرُ رَمَضَانَ الَّذِي أُنْزِلَ فِيهِ الْقُرْآنُ هُدًى لِلنَّاسِ وَبَيِّنَاتٍ مِنَ الْهُدَىٰ وَالْفُرْقَانِ ۚ فَمَنْ شَهِدَ مِنْكُمُ الشَّهْرَ فَلْيَصُمْهُ ۖ

*"ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች ቅኑን መንገድ መሪ የሆነው እና እውነትን ከሀሰት የሚለዩ ገላጭ አንቀጾችን የያዘው ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፤ እንድትፆሙ ተጻፈባችሁ። ከእናንተም ወሩ የገጠመው ሰው ይፁመው!" አል-በቀራ 185*

በአፑ የፆምን ህግጋት ከማብራራት በተጨማሪ ፆምን የተመለከቱ የሀዲስ ጥንቅሮች፣ የሱና ፆሞች ድንጋጌና ሌሎችም ትምህርቶች ተዳስሰውበታል! አፑ በቀላሉ ለሌሎች ወንድም፣ እህቶች ሼር ማድረጊያ እና ከሌሎችም ብዙ አገልግሎቶች ጋር የቀረበ ነው!አሁኑኑ ከፕለይስ ቶር ይጫኑት፤ ለወዳጅ ለዘመድ ያስተዋውቁት!

### ዝክረ ረመዳን አፕ





“ረመዳን በመጣ ጊዜ የጀነት በሮች ይከፈታሉ ፤ የእሳት በሮች ይዘጋሉ ፣ ሰይጣናትም ይታሰራሉ፡ ፡”



# ከምስቱ የወርሀ ረመዳን ትሩፋቶች

ወንድሞቼ! የተከበረው ወር፣ ታላቁ ወር መጣላችሁ በውስጡ አጅር የሚደራረብበት፣ የአላህ ስጦታ የሚበረከትበት፣ መልካምን ለፈለገ ሁሉ የበጎ ነገራት በሮች የሚከፈቱበት የኸይር ወር፣ የበረካ ወር፣ የስጦታና የገፀበረከት ወር። የረመዳን ወር ለሰዎች መሪ፣ ከቀና መንገድ አስታራቂና እውነትን ከውሸት ከሚለዩም ገላጮች ሲሆን ቁርአን የተወረደበት ነው። እዝነትና ምህረት ያካበበው ወር ነው። ጅማሬው እዝነት፣ መሀሉ ምህረት፣ መጨረሻው ከእሳት ነፃ የሚወጣበት ወር ነው። እነዚህንና ሌሎችን ጉዳዮች በተመለከተ ብዙና ግልፅ መረጃዎች ከቀደመው ትውልድ ደርሶናል። ከአቡ ሁረይራ ተይዞ እንደተወራው ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል “ረመዳን በመጣ ጊዜ የጀነት በሮች ይከፈታሉ፤ የእሳት በሮች ይዘጋሉ፣ ሰይጣናትም ይታሰራሉ።” ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

መልካም ሥራዎች ስለሚበዙና የሥራውንም ባለቤቶች ለማበረታታት የጀነት በሮች የሚከፈቱ ሲሆን ከሙእሚኖቹ ዘንድ ወንጀል ስለሚቀንስ የጀሀነም በሮች ይዘጋሉ ሰይጣኖችም ይታሰራሉ።

ኢማሙ አሕመድ አቡ ሁረይራን ጠቅሰው እንደዘገቡት ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል “የእኔ ኡመቶች ረመዳንን አስመልክቶ ከነሱ በፊት ማንም ያልተሰጠውን አምስት ልዩ ነገሮች ተሰጥተዋል። አላህ ዘንድ የፆመኛ አፍ ሽታ ልክ እንደሚስክ ሽታ ነው፣ እስከሚያፈጥሩ ድረስ መላኢካዎች ምህረትን ይጠይቁላቸዋል፣ አላህ በየቀኑ ጀነትን እያሰማመረ መልካም ባሮቼ የሚያስቸግራቸውንና የሚያስከፋቸውን ነገር በመተው ሥራ እንደሚሰርቁት አሁን አይሰርቁም በመጨረሻው ሌሊት ምህረት ይደረግላቸዋል። የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ይህች ሌሊት ለይለቱል ቀደር ናትን? ብለው ሰሃቦች ጠየቋቸው። አይደለችም ግና ሠራተኛ ሥራውን እንደጨረሰ ነው ምንዳው የሚከፈለው አሏቸው።”

እነዚህ አምስት ነገሮች ለሙስሊሞች ነው የተዘጋጁት አላህ በሙስሊሞች ላይ ፀጋዎቹን ሊያሟላ ከሌላው ሕዝብ በተለየ መልኩ ለሙስሊሞች አደረገ።

*“እናንተ በላጭ ሕዝቦች ናችሁ፤ በመልካም ታዛላችሁ፤ ከመጥፎ ትከለክላላችሁ በአላህም ታምናላችሁ።”*

## የመጀመሪያው ገፀ በረከት

የፆመኛ የአፍ ሽታ ልክ እንደሚስክ ነው። አንድ ሰው ከምግብ ሲርቅ አፉ መጥፎ ጠረን ያመጣል። ምንም እንኳን ይህ ጠረን ሰዎች ዘንድ የተጠላ ቢሆንም አላህ ዘንድ ግን ከሚስክ ሽታ የተሻለ ጥሩ ሽታ ነው። ምክንያቱም ደግሞ አላህን በመታዘዝና በማምለክ የመጣ ስለሆነ ነው። ማንኛውም አላህን በመታዘዝና በማምለክ የመጣ ነገር እሱ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ ነው። አላህ ለሠራው ባለቤት የተሻለንና በላጭን ነገር ይተካዋል። ስለዚያ በአላህ መንገድ ላይ የአላህ ቃል የበላይ ትሆን ዘንድ ሲዋጋ ስለተገደለ ሰው ሰምተሃልን? የውመል ቂያማ ቁስሉ ደም እያፈሰሰ ይመጣል፤ መልኩ ልክ እንደ ደም ነው ጠረኑ ደግሞ እንደሚስክ ነው።

በሐጅ ጊዜ በተመሳሳይ መልኩ አላህ መላኢኮችን አረፋ ላይ ስለቆሙ ሰዎች እንዲህ ይላቸዋል “እነኚህን ባሮቼን ተመልከቱ፤ ፀጉራቸው ተንጨባሮና አቧራ ለብሰው ወደ እኔ መጡ።” አህመድና ኢብኑ ሒባን ዘግበውታል።

እዚህ ቦታ ላይ የፀጉር መንጨባረር አላህ ዘንድ ተወዷል። መነሻው አላህን መታዘዝና ኢህራምን ላለመፍታት እንዲሁም አለባበስን ከማሳመር መጠንቀቅ ስላለበት በመሆኑ ነው።

## ሁለተኛው ገፀ በረከት

መላኢካዎች እስከሚያፈጥሩ ድረስ ምህረትን ይጠይቁላቸዋል። መላኢካዎች አላህ ዘንድ የተከበሩ ካዘዛቸው ዝንፍ የማይሉ፣ ከከለከላቸው የማይቀርቡ ብፁአን ፍጥረታት ናቸው። ለፆመኞች የሚያደርጉት ዱዓ በአላህ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ተቀባይነቱ ጥርጥር የለውም። አላህ ለዚህች ኡማህ መላኢካዎች ዱዓ እንዲያደርጉ መፍቀዱ የኡማዋን ትልቅነት፣ የዝናው ከፍ ማለትም የፆማቸውንም ታላቅ ትሩፋት ይገልፃል።

**“ረመዳን በመጣ ጊዜ የጀነት በሮች ይከፈታሉ፤ የእሳት በሮች ይዘጋሉ፣ ሰይጣናትም ይታሰራሉ።”**

ምህረት (ኢስቲግፋር) መፈለግ ማለት አንድ ሰው ወንጀል በዱንያ ሆነ በአኺራ ድብቅ እንዲሆንለት ይህችንም ወንጀል አላህ እንዲያልፈው መጠየቅ ማለት ሲሆን ይህ ደገሞ ከምንፈልጋቸውና ከምንመኛቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ በላጬ ነው። የአደም ልጆች ምንጊዜም ተሳሳቾችና ድንበር አላፊዎች ናቸው በመሆኑም የአላህን ምህረት መከጀል ይገባቸዋል።

## ሦስተኛው ገፀ በረከት

ሰይጣናት በሰንሰለትና እግረ ሙቅ ይታሰራሉ። እስራቱ መልካም የአላህ ባሪያዎችን እንዳያጠምሙና ከሐቅ እንዳያዘናጓቸው ያደርጋል። ይህም የእሳት ባልደረቦች ይሆኑ ዘንድ ጥሪ የሚያደርጉ ጠላቶቻቸውን በማገት አላህ ባሮችን ያገዘበት መንገድ ነው። በዚህ ወር ላይ የሚታየው ከፍተኛ መልካም ሥራን ለመፈፀም የሚደረግ ጉጉትና ከመጥፎ ነገር ለመታቀብ የሚደረገው ጥረት የሰይጣናቱ መታሰር ውጤት ነው።

## አራተኛው ገፀ በረከት

አላህ በየቀኑ ጀነትን ያስውባታል። ባሮቼ የሚያስከፋቸውንና የሚያስጠላቸውን ነገር እርግፍ አድርገው ትተው ወዳንቺ መምጣትን ፈልገዋል፣ ቀርበዋል ይላታል። አላህ ለመልካም ባሮቹ ለማዘጋጀት ያሰማምራታል በየቀኑ ባሮቹ ለእሷ ያላቸው ጉጉት ይጨምር ዘንድ እንዲህም ይላታል *“ባሮቼ የዱንያ ጣጣን ትተው ሲያንገላታቸውና ሲያደክማቸው ሲያስቸግራቸው የነበረን ነገር ሁሉ በመተው ወደ ሰላሟና የክብር ሀገሯ ጀነት የሚያደርሳቸው በጎ ነገርን በመሥራት ላይ ታጥቀው ተነስተዋል። የዱንያም የአኺራም ብቸኛ የደስታ ምንጭም ይህ መሆኑን አውቀዋል።”*

## አምስተኛው ገፀ በረከት

አላህ በዚህ በተባረከ ወር ሌሊቶች በተገቢው ሁኔታ ለሚቆሙ እና ለሚፆሙ ለነብዩ ሙሐመድ ﷺ ኡመቶች ምህረትን ይለግሳቸዋል።

ይህም ሰዎች ሥራቸውን በሚደመድሙበት ጊዜ የሚከፍላቸው ትሩፋት ነው። ሠራተኞች የሥራ ዋጋቸው የሚከፈላቸው ሰራቸውን ሲያጠናቅቁ ነውና። አላህ ለባሮቹ በሦስት መልኩ ችሮታውን ይለግሳቸዋል።

### አንደኛ

ኃጢአትን ለማስማር ደረጃን ከፍ ለማድረግ የሚያስችለን መልካም ሥራ ባሮች እንዲሠሩ መደንገጉ አንደኛው ነው። ይህ ድንጋጌ ባይኖር ኖሮ አላህን በዚህ መልኩ ማምለክ ባልቻሉ ነበር። ኢባዳ በራዕዩ (ወህይ) መልክ ከአላህ ወደ መልዕክተኛው ﷺ የሚተላለፍ ነው። ለዚያም ነው ከአላህ ውጭ ሸሪዓን ወይም ስርዓተ ህግን የሚደነግጉ ሰዎችን ያወገዘውና የሽርክ ሥራ እንደሆነ የገለፀው።

*“ከሃይማኖት አላህ በርሱ ያልፈቀደውን ለርሱ የደነገጉ ተጋሪዎች ለነርሱ አሏቸውን?”*

### ሁለተኛ

ብዙዎች ወደኋላ ያሉበትን መልካም ሥራ እንዲሠሩ አላህ ገጠማቸው። የአላህ እርዳታና መገጠም ባይኖር ኖሮ ለዚህ ባልታደሉ ነበር ችሮታው የአላህ ነውና።

*“በመስለማቸው በአንተ ላይ ይመፃደቃሉ፤ በእስልምናችሁ በእኔ ላይ አትመፃደቁ፤ ይልቁንም አላህ ወደእምነት ስለመራችሁ ይመፃደቅባችኋል፤ እውነተኞች ብትሆኑ (መመፃደቅ ለአላህ ነው) በል።”* አል ሑጅራት 17

### ሦስተኛ

አላህ ለኸይር ሥራዎች ከፍተኛ ምንዳን አዘጋጅቷል። አንድ ሀሰና በአስር፣ በሰባት መቶ፣ በብዙ እጥፍ ድርብ ተባዝቶ ይሰጠዋል። ይህ ችሮታ የአላህ ነው። ምስጋና የተገባው ይሁን።

ወንድሞቼ! የረመዷን መድረስ ትልቅ ፀጋ ነው ሐቁን መወጣት ለቻለና አላህን ከመወንጀል ትዕዛዛቱን ወደ መፈፀም፤ ከዝንጋታ አላህን ወደ ማውሳት፤ አላህን ከመራቅ ወደ እሱ መመለስን ምርጫው ላደረገ ሰው እውነትም ታላቅ ፀጋ ነው።

**(ከሸይኽ ሳሊሕ አል ዑሠይሚን (ረሂመሁላህ) ጽሁፍ የተተረጎመ)**

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# ስለ ፆም አጭር ማብራሪያ

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ የተገባ ነው:: የአላህ ሰላትና ሰላም በነብያችን ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን::

ይህ የፆምን ምንነት፣ ህግጋቶቹን፣ ሰዎች ከዚህ አንፃር ያላቸው ሁኔታን ፣ ፆምን የሚያበላሹ ነገሮችን እና ሌሎች (ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው) ነጥቦችን በጥቂቱ የምንዳስስበት አጭር መልዕክት ነው::

· ፆም ከጎህ መቅደድ እስከ ፀሀይ መጥለቅ ድረስ ፆምን ከሚያበላሹ ነገሮች በመቆጠብ የሚፈፀም የአምልኮ ተግባር ነው::

· የረመዳንን ወር መፆም ከታላላቅ የኢስላም ማዕዘናት አንዱ ነው:: የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ይላሉ:-

*‹‹ኢስላም በአምስት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የተገነባ ነው:: (እነርሱም):- ከአላህ ሌላ አምልኮ የሚገባው አምላክ እንደሌለ ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ እንደሆኑ መመስከር፣ ሰላትን አሟልቶ መስገድ፣ ዘካን መስጠት፣ ረመዳንን መፆም እና ወደ ተከበረው የአላህ ቤት ለሐጅ መጓዝ ናቸው::››* (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

## ሰዎች ከፆም አንፃር

➦ ፆም በእያንዳንዱ ለአካለ መጠን በደረሰ፣ የጤናማ አዕምሮ ባለቤት፣ መፆም የሚያስችለው ጤና ያለው እና መንገደኛ ባልሆነ ሙስሊም ሁሉ ላይ ግዴታ ነው::

➦ ሙስሊም ያልሆነ ሰው የፆም ግዴታነት በቀጥታ አይመለከተውም:: ቢሰልምም ከመስለሙ በፊት ያለፈውን ፆም የመክፈል (ቀዳእ የማውጣት) ግዴታ አይኖርበትም::

➦ ለአካለ መጠን ያልደረሰ (ህፃን) ፆም ግዴታ አይሆንበትም ነገር ግን እንዲለምደው በማሰብ እንዲፆም ይታዘዛል::

➦ የአዕምሮ በሽተኛ የረመዳንን ወር መፆምም ሆነ ለፆም ማካካሻ የሚሆን ምስኪን የማብላት ስርአት ግዴታ አይሆንበትም:: በተመሳሳይ ሁኔታም ነገሮችን መለየት የተሳነው ዘገምተኛ ሰው እና እድሜው በጣም የገፋ ሽማግሌ ፆም ግዴታ አይሆንባቸውም::

➦ እንደ እርጅናና ለመዳን ተስፋ የሌለው በሽታ ባሉ ዘውታሪ ምክንያቶች የተነሳ መፆም የተሳነው ሰው ለእያንዳንዱ ቀን አንድ ምስኪን ያበላል::

➦ መዳኑን ተስፋ በሚያደርገው (ጊዜያዊ በሽታ) የተያዘ ሰው መፆም ከከበደው በህመም ጊዜ ፆሙን በመፍታት ከበሽታው ሲያገግም በመፆም ያካክሳል::

➦ በእርግዝናና በማጥባት ላይ ያሉ በዚሁ ምክንያት ፆሙ ከከበዳቸው አሊያም በልጆቻቸው ላይ ጉዳት እንዳይከሰት ከሰጉ ፆምን በመፍታት ስጋቱ በተወገደና በገራላቸው ወቅት ይፆማሉ::

➦ በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ ያሉ የማይፆሙ ሲሆን ያለፏቸውን የፆም ቀናት በሌላ ጊዜ በመፆም ያካክሳሉ::

➦ በእሳት ቃጠሎ አሊያም በውሃ የመስጠም ወይም በተመሳሳይ አደጋ ላይ የወደቁ ሰዎችን ለመታደግ የነፍስ አድን ሥራ ላይ በመሰማራቱ ፆምን ለመፍታት የተገደደ ሰው ፆሙን ፈትቶ በሌላ ጊዜ በመፆም ያካክሳል::

➦ መንገደኛ (ሙሳፊር) ሰው ከፈለገ ይፆማል ከፈለገም ፆሙን በመፍታት በሌላ ጊዜ ያካክሳል:: ይህም ማለት በድንገት እንደ ዑምራ ላሉ ተግባራት የሚጓዘውንም ይሁን በዘውታሪነት ጉዞ ላይ የሚሆኑትን የአገር አቋራጭ ሕዝብ ማመላሻ ሠራተኞችን ይመለከታል:: እነዚህ ሰዎች በመኖሪያ አገራቸው እስካልሆኑ ድረስ ከፈለጉ ፆምን በመፍታት በሌላ ጊዜ ያካክሳሉ::

## ፆምን የሚያበላሹ ነገሮችን በተመለከተ

*ፆመኛው ፆምን የሚያበላሹ ነገሮችን ረስቶ ወይም ተገዶ አሊያም ባለማወቅ አንዱን ቢፈፅም ፆሙ አይበላሽም:: ይህም በተከታዮቹ ቁርአናዊ መረጃዎች መሰረት ነው::*

*(ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንስት አትያዘን (አትቅጣን)... በሉ)* {አል-በቀራህ፡286}

**ፀሀይ መጥለቋን ወይም ጎህ ያለመቅደዱን በማሰብ ቢበላ አሊያም ቢጠጣ ፆሙ አይበላሽም:: ምክንያቱም እውነታውን ባለማወቁ ነው::**

((ልቡ በእምነት የረጋ ሆኖ (በክህደት ቃል በመናገር) የተገደደ ሰው ብቻ ሲቀር)) {አል-ነህል፡106}

*((በርሱ በተሳሳታችሁበት ነገርም በናንተ ላይ ሀጢአት የለባችሁም፤ ግን ልቦቻችሁ አውቀው በሰሩት (ሀጢአት አለባችሁ)...)) {አል-አህዛብ፡5}*

ስለዚህ ፆመኛው ረስቶ ቢበላ ወይም ቢጠጣ ሆን ብሎ ባለመሆኑ ፆሙ አይበላሽም::

ፀሀይ መጥለቋን ወይም ጎህ ያለመቅደዱን በማሰብ ቢበላ አሊያም ቢጠጣ ፆሙ አይበላሽም:: ምክንያቱም እውነታውን ባለማወቁ ነው::

*ፆመኛው በመጉመጥመጥ ላይ ሳለ ሳያስበው ውሃ ወደ ጉሮሮው ቢወርድ አስቦት ባለመሆኑ ፆሙ አይበላሽም::*

*ፆመኛው በእንቅልፉ ላይ ሳለ የዘር ፈሳሽ ቢፈሰው ፆሙ አይበላሽም:: ምክንያቱም በፍላጎቱ የተከሰተ ባለመሆኑ ነው::*

## ፆምን የሚያበላሹ ነገሮች ስምንት ናቸው::

1. የግብረስጋ ግንኙነት:- የረመዳንን ወር መፆም ግዴታነት የፀናበት ፆመኛ በቀኑ ክፍለ ጊዜ የግብረስጋ ግንኙነት ከፈፀመ በዚህ ድርጊቱ ምክንያት ፆሙ ይበላሻል:: በመሆኑም የዚህን ዕለት ፆም በሌላ ጊዜ መፆሙ ግዴታ ከመሆኑም ባሻገር ከፍተኛ ማካካሻ መክፈል ይጠበቅበታል:: ማካካሻውም ባርያን ነፃ ማውጣት፣ ካላገኘም ሁለት ወራትን በተከታታይ መፆም ይህንም ካልቻለ ስልሣ ምስኪኖችን ማብላት ነው::

2. ብልትን በመነካካት ወይም ከተቃራኒ ፆታ ጋር በመተሻሸት አሊያም በመሳሳም ወይም በመተቃቀፍ እና በመሳሰሉት ሁኔታዎች የዘር ፈሳሽን ማፍሰስ::

3. እንደ ሲጋራ ያሉ የሚጨሱ ነገሮችን ጨምሮ የሚጠቅሙም ሆኑ የሚጎዱ ነገሮችን መብላት ወይም መጠጣት ፆምን ከሚያበላሹ ነገሮች ይመደባል::

4. ምግብን ሊተኩ የሚችሉ (ኃይል ሰጪ) መርፌዎችን መወጋት ምክንያቱም እንደነዚህ አይነቶቹ መድሃኒቶች ሙሉ በሙሉ የምግብ አይነት ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ ከመሆናቸው ጋር የተያያዘ ነው::

የምግብነት ባህሪ የሌላቸውን መድሃኒቶች በመርፌ በጡንቻ ወይም በደም ስር ላይ በመወጋት ቢጠቀም ምንም እንኳ የመድሃኒቱ ጣዕም በጉሮሮው ውስጥ ቢታወቀውም ፆሙ አይበላሽም::

5. ደምን መውሰድ አንድ ፆመኛ ደም ቢፈሰው እና ምትክ ደም መሰጠት አስፈልጎት ደም ቢሰጠው ፆሙ ይበላሻል::

6. የወር አበባ እና የወሊድ ደም መፍሰስ::

7. በዋግምት እና በመሳሰሉት መንገዶች ደምን ማስወጣት ሲሆን ከዚህ ውጪ እንደ ነስር ወይም ጥርስ መነቀል ባሉ ምክንያቶች በራሳቸው ውስጣዊ ግፊት የሚከሰቱ የደም መፍሰሶች ከዋግምት ጋር ተመሳሳይነት የሌላቸው በመሆኑ ፆምን አያበላሹም፡

8. ሆን ብሎ (እጅን እና መሰል ነገሮችን በመጠቀም) ማስታወክ ፆምን የሚያበላሽ ሲሆን ነገር ግን ግለሰቡ ከቁጥጥሩ ውጪ ሆኖ ቢያስመልሰው ፆሙ አይበላሽም::

**✍ ትርጉም ኡስታዝ ጣሃ አሕመድ**

------------*********------------

## 🔔 የማንቂያ ደወል!

የረመዳን ቀናት እየተቆጠሩ ሲያልፉ ምንኛ ይፈጥናሉ! ከረመዳን 1,2,3.. ቀናት ሲያልፉ በጣም ይፈጥናሉ!! መዘናጋት በማንኛውም ሰው ህይወት ውስጥ የተለመደ ክስተት ቢሆንም፤ መዘናጋታችን በአጨዳ ወቅት ከሆነ ግን ኪሳራው ከባድ ነውና እንጠንቀቅ!!

የረመዳን ወቅት በመልካም ሥራ የምንሽቀዳደምበት ወቅት ነው። በጥሩ ሁኔታ አልፎ ከሆነ አሻሽለን መልካም ሥራን እንጨምር፤ ጉድለታችንንም እናሟላ፤ እናካክስ!

በኢባዳ ለመትጋት ብርታቱ ካልራቀን በቀር ይህ የትርፍ ወር የተቆጠሩ ጥቂት ቀናቶች ብቻ መሆኑን አንርሳ!

«أياما معدودات» البقرة 184

«የተቆጠሩን ቀኖች (ጹሙ)» አልበቀራህ 184

# የዘካ አወጣጥን የተመለከቱ ጥቅል ነጥቦች

✍ ሸይኽ ኢልያስ አሕመድ

ዘካ የስርወ-ቃሉ ቋንቋዊ ትርጉም፡- "መብዛት" ፣ "ማደግ"፣ "መጨመር" እንዲሁም "ማወደስ"ና " (ከጉድፈት) ማጥራት" ን የሚያመለክት ነው።

የዘካ ሸሪዓዊ መልዕክት ደግሞ በየተወሰኑ ጊዜያት ከተወሰኑ የንብረት ዓይነቶች ተቆንጥሮ ለተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ከተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች በግዴታነት የሚሰጥ የተገደበ ወጪ ነው።

የዘካ ድንጋጌ እንደሌሎቹ መለኮታዊ ህግጋት ሁሉ ከአምልኮ ዘርፍነቱ ባሻገር ድንቅ፣ ብርቅና ፅድቅ ጥበቦችንና ዓላማዎችን ያነገበ ነው። ሰዎች ሊረዷቸው ከሚችሏቸው ግለሰባዊና ማሕበራዊ ጥቅሞቹና የመፍትሄነት ገፅታዎቹ መካከል፡-

☞ ለችግረኞች እርዳታ መሆኑ

☞ ለድሆች መቋቋሚያ መሆኑ

☞በእምነት ላይ የተመሠረተ የወዳጅነትና የወንድማማችነት ትስስርን ማጥበቁ

☞ ስብዕናን ከስስትና ከንፉግነት ማፅዳቱ

☞ ድሆች ለሀብታሞች ያላቸውን ምልከታ ከምቀኝነት ማጥራቱ

☞ በድህነት ምክንያት የሚፈጸሙ ወንጀሎችን መገደቡ

☞ ከገንዘብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥቅል ኢስላማዊ ጉዳዮችን ለማቀላጠፍ ምክንያት መሆኑና

☞ የንብረት በረከት ማስከተሉ ጥቂቶቹ ናቸው።

## በኢስላም ያለው ደረጃና ብይን

ዘካ ኢስላም ከተገነባባቸው አምስቱ መሠረቶች ሦስተኛው ሲሆን ለዘካ በቂ የሆነ ገንዘብ ያለው ማንኛውም ሙስሊም በግዴታነት ዘካ ማውጣት እንዳለበት በሙስሊሞች መካከል በጥቅሉ ያለምንም ውዝግብ የተረጋገጠ እውነታ ነው። ይህንን የሚያስገነዝቡት ቁርአናዊና ሀዲሳዊ አስተምህሮቶች በርካታ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ፡-

*وَأَقِيمُوا الصَّلَاةَ وَآتُوا الزَّكَاةَ [البقرة: 110]*

*«ሰላትንም አቋቁሙ፤ ዘካንም ስጡ!»*

*فَإِنْ تَابُوا وَأَقَامُوا الصَّلَاةَ وَآتَوُا الزَّكَاةَ فَإِخْوَانُكُمْ فِي الدِّينِ [التوبة:11]*

**«(**ተፀፅትው) ከተመለሱ ሰላትንም ካቋቋሙ ዘካንም ከሰጡ የእምነት ወንድሞቻችሁ ናቸው።»

*عَنْ ابْنِ عُمَرَ —رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُمَا— قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللَّهِ ﷺ : بُنِيَ الْإِسْلَامُ عَلَى خَمْسٍ: شَهَادَةِ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللَّهِ، وَإِقَامِ الصَّلَاةِ، وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ، وَالْحَجِّ، وَصَوْمِ رَمَضَانَ متفق عليه.*

ዓብዱላህ' ብኑ ዑመር የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል አሉ «ኢስላም በአምስት ነገሮች ላይ ተገነባ፡- ከአላህ በቀር አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ሰላትን ማቋቋም፣ ዘካን መስጠት፣ ሐጅ ማድረግና ረመዳንን መፆም»( ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ዘካን ወጪ የማያደርግ ባለሀብቶች ሁለት ዓይነት ናቸው፡-

1ኛው ዓይነት፡- የዘካን ግዴታነት ከማስተባበል ወይም ከኩራትና ከትዕቢት በመነጨ እምቢተኝነት የተነሳ የሚነፍግ ነው፤ ይህ ዓይነቱ ከኢስላም ምንም ድርሻ የሌለው ከሀዲ ስለመሆኑ ጥርጥር የለም።

2ኛው ደግሞ፡- ግዴታነቱን ሳያስተባብል በስስት ወይም በመዘናጋት የተነሳ የሚነፍግ ሲሆን ለእንዲህ ዓይነቱ የሚሰጠውን ብይን አስመልክቶ የኢስላም ሊቃውንት ሁለት አመለካከቶች አሏቸው፤

ጥቂቶቹ ይኸኛው እንደመጀመሪያው ከሀዲ መሆኑን ሲናገሩ ብዙኃኑ ግን ወንጀሉ ከባድ ቢሆንም ከኢስላም የሚያስወጣው የክህደት ደረጃ አይደርስም ይላሉ።

**«ኒሷብ» የደረሰ የገንዘብ መጠን ኖሮት ዓመት ያሳለፈ ሙስሊም ከገንዘቡ 1/40ኛውን (2.5%) ለዘካ መክፈሉ የግድ ይሆናል።**

መልዕክተኛው ﷺ ዘካን የነፈገ በፍርዱ ቀን የሚያጋጥመውን ቅጣት በጠቀሱ ጊዜ፡-

*«…ከዚያም መንገዱን ይመለከታል (ይጠቆማል)፤ ወይ ወደ ጀነት ወይም ወደ እሳት!»* (ሙስሊም ዘግቦታል) ማለታቸው የአብዛኛውን አቋም ይደግፋል።

### ዘካ ግዴታ የሚሆንባቸው መስፈርቶች

የሚከተሉት መስፈርቶች በሙሉ ካልተሟሉ በስተቀር ዘካ ማውጣት ግዴታ አይሆንም፤

1. **ሙስሊም መሆን ፡-** ሙስሊም ያልሆነ ሰው ከዘካ በፊት ሊያሟላቸው የሚገባ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ስላሉ ዘካ መስጠት እንደሙስሊም ግዴታ ይሆንበታል አይባልም። ነገር ግን ሙስሊም ባለመሆኑና ዘካን ጨምሮ ሌሎች ኢስላማዊ ግዴታዎችን ባለመወጣቱ፣ እንዲሁም በዝርዝር ጥፋቶቹ መንስኤነት የወዲያኛው ዓለም ቅጣት እንደሚነባበርበት የሚጠቁሙ ቁርአናዊ መረጃዎች አሉ።

2. **ከባርነት ነፃ መሆን ፡-** ባሪያም በእጁ ያለው ገንዘብም የአሳዳሪው ንብረት ናቸውና ዘካ የማውጣቱ ኃላፊነት እሱን ሳይሆን አለቃውን የተመለከተ ይሆናል።

3. **ሙሉ ባለቤትነት ፡-** እንደ «ወቅፍ» ያለ ውስን ባለቤት የሌለው ንብረት ላይ ዘካ አይደነገግም። በውል ባልተረጋገጠ ባለቤትነት ላይ ያለው ፍርድም ተመሳሳይ ነው።

4. **ንብረቱ «ኒሷብ»** (ዘካ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛው መጠን) መድረሱ፡- ይህ መጠን እንደንብረቱ አይነት ሊለያይ ይችላል።

5. **ንብረቱ በባለቤቱ ይዞታ ስር** ከ«ኒሷብ» ሳይጎድል በጨረቃ አቆጣጠር አንድ ዓመት መቆየቱ ሆኖም ይህ መስፈርት ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ሦስት ነገሮች አሉ፡-

**አንደኛው፡-** አዝርዕትና ብቅሎች (ቡቃያ) - የዘካ ጊዜያቸው የአዝመራ ወቅት ነውና።

**ሁለተኛው፡-** ቅድሚያ ከነበሩ ግመሎች፣ ከብቶች ወይም በጎችና ፍየሎች የተወለዱ አዳዲስ ግልገሎች፤

**ሦስተኛው፡-** የንግድ ትርፍ፤ እነዚህ ሦስት የንብረት ዓይነቶች ዓመት ባይሞላቸውም ሌሎች መስፈርቶች ከተሟሉ የዘካ ግዴታ ይመለከታቸዋል።

ከእነዚህ መስፈርቶች ጋር ለአቅመ አዳም መድረስና የአእምሮ ጤናማነት ያልተጠቀሰበት ምክንያት፡- ህፃን ልጆች ወይም አእምሯቸው የታወከ ግለሰቦች ምንም እንኳን ሸሪዓዊ ግዴታዎች በቀጥታ ባይመለከቷቸውም ንብረታቸው ግን «ኒሷብ» እስከደረሰ ድረስ በንብረትነቱ ብቻ ዘካ ሊወጣለት ስለሚገባ ነው፤ የዘካ ግዴታነት ከንብረቱ እንጂ ከባለንብረቱ ጋር ተያያዥነት የለውምና። ይህ የብዙኃኑ ሊቃውንት አቋም ሲሆን ይህንንም የሚጠቁሙ ንግግሮች ከተለያዩ ሰሃቦች ተዘግበዋል።

## ዘካ የሚሠጣቸው ወገኖች

የዘካ ድጎማ የሚገባቸው ወገኖች ስምንት ዓይነት ናቸው። እነርሱም በሚከተለው የአላህ ቃል ተዘርዝረዋል፡-

*إِنَّمَا الصَّدَقَاتُ لِلْفُقَرَاءِ وَالْمَسَاكِينِ وَالْعَامِلِينَ عَلَيْهَا وَالْمُؤَلَّفَةِ قُلُوبُهُمْ وَفِي الرِّقَابِ وَالْغَارِمِينَ وَفِي سَبِيلِ اللَّهِ وَابْنِ السَّبِيلِ فَرِيضَةً مِنَ اللَّهِ وَاللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ [التوبة: ٦٠]*

*«(ግዴታ) ምፅዋትም ለድሆች፣ ለምስኪኖች፣ በሷም ላይ ሠራዎች ለሆኑ፣ ልቦናቸው (ኢስላምን) የሚላመዱ፣ በባሮችም፣ በባለዕዳዎች፣ በአላህም መንገድና፣ (ካገሩ ለወጣ) መንገደኛ ነች፤ ከአላህ ዘንድ (የተገደበች) ግዴታ፤ አላህም አዋቂ፣ ጥበበኛ ነው።»*

*ማብራሪያው እንዲሚከተለው ይጠቀሳል፡-*

1. **ድሆች፡-** ድሆች የሚባሉት የዕለት ጉርሳቸውን በበቂ መልኩ የማያገኙ ናቸው። ዘካ ሲከፋፈል ቢቻል የመሥራት አቅም ላላቸው ከድህነት ወጥተው የሚቋቋሙበት፣ አቅሙ ለሌላቸው ደግሞ ለዓመት የሚበቃቸውን ያህል ቢለገሱ ይመረጣል።

2. **ምስኪኖች ፡-** ምስኪኖች የሚባሉት አስፈላጊ የኑሮ ማሟያዎችን የማያገኙ ናቸው።

3. **የዘካ ሰብሳቢዎችና አከፋፋዮች፡-** እነርሱም የሙስሊሞች የበላይ መሪ ዘካን እንዲሰበስቡና እንዲያከፋፍሉ የመደባቸው ሲሆኑ ለዚህ ሥራቸው ከዘካ ገንዘብ አበል ይቆረጥላቸዋል።

4. **ልቦናቸው (ኢስላምን) የሚላመዱ፡-** እነኚህም ኢስላምን ለመቀበል ዝንባሌ ያላቸው፣

ወደ ቀጣይ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .

አዲስ ሰለምቴዎች ሆነው እምነታቸው ያልጠነከረ ግለሰቦች ሲሆኑ የዘካ መልካም አድራጎት ለእምነታቸው መስተካከልና መሻሻል አስተዋፅአ እንደሚያበረክት ከተገመተ ከዘካ ወጪ ውስን ድርሻ ይኖራቸዋል።

5. **በባርነት ሥር ያሉ ሙስሊም ወገኖች፡-** በባርነት የሚገዙ ሙስሊሞችን ገዝቶ ነፃ ለማውጣት ወይም በተወሰነ ክፍያ ነፃነታቸውን ለማግኘት ከአሳዳሪዎቻቸው ጋር ውል የፈፀሙትን በክፍያ ለማገዝ ከዘካ ገንዘብ ወጪ ይደረጋል።

አንዳንድ ሊቃውንት ምርኮኛን ለማስለቀቅ የሚከፈል ቤዛ በዚሁ ፍርድ ውስጥ እንደሚካተት ይናገራሉ።

6. **ባለዕዳዎች፡-** ዕዳ ተሸክመው መክፈል የተሳናቸው ወገኖች ዕዳቸውን መክፈል የሚችሉበት የገንዘብ መጠን ከዘካ ይሰጣቸዋል።

***ባለዕዳዎች ሁለት ዓይነት ናቸው ፡-***

1) ለግል ጥቅማቸው ወይም በግል ጥፋታቸው ምክንያት ዕዳ የተጫነባቸው፣

2) በሰዎች መሀል የሚከሰት ጠብን ለማብረድ የንብረት ዋስትና የተሸከሙ፤ እንደነዚህ ዓይነቶቹ የግል ሀብት ቢኖራቸውም ለዘካ ድጎማ ተገቢ ናቸው።

ሌላ ሰው ዘንድ በዕዳ መልክ ገንዘብ ያለው ግለሰብ ዘካን በመስጠት ዕሳቤ ገንዘብ ሳያወጣ ከባለዕዳው ዕዳን ማቃለል ወይም መሰረዝ የራስን ጥቅም መጠበቅ ነውና እንደዘካ አይቆጠርም።

7. **በአላህ መንገድ ላይ ታጋይ የሆኑ፡-** ከሙስሊሞች ግምጃ ቤት ተቆራጭ የሌላቸው ታጋዮች ለ«ጂሃድ» የሚያስፈልጋቸው ወጪ ከዘካ ይሰጣቸዋል። ብዙኃኑ ሊቃውንት ይህ መልዕክት የተጠቀመበት ቁርዓናዊ ቃል (وَفِي سَبِيلِ اللَّهِ)ሌሎች ሰናይ አድራጎቶችን እንደማያካትት አስረግጠው ይናገራሉ።

በዚህም መሠረት መስጂድ ለመገንባት፣ ት/ቤቶችን ለማቋቋም፣ ጠቃሚ መጻሕፍትን አትሞ ለማሰራጨት፣ የሕክምና ማዕከላትን ለመመሥረትና ለመሳሰሉት የበጎ ተግባር መስኮች የዘካ ገንዘብን ማዋል የማይፈቀድ ይሆናል ማለት ነው። ሆኖም ብዙ ሊቃውንት ለኢስላማዊ ዕውቀት ፍለጋ ጊዜያቸውን የሰጡ ተማሪዎች እንደ ታጋዮች የዘካ ድርሻ እንደሚገባቸው ያስፍራሉ።

8. ***ወደ አገሩ የሚመለስበት ወጪ ያጣ መንገደኛ፡-*** እንዲህ ዓይነቱ በመኖሪያ አገሩ በቂ ሀብት ቢኖረው እንኳ ወደ አገሩ መመለሻ የጉዞ ወጪ ከዘካ ገንዘብ ይሰጠዋል።

## «ኒሷብ» እና የገንዘብ ዘካ

በዘመናችን የዋጋ ተመንነትን ተክቶ የሚገኘው የገንዘብ ኖትን አነሳስና ታሪካዊ ሂደት የተመለከቱ በርካታ ጥናቶች ተደርገዋል። በአሁኑ ወቅት ሊሠጠው የሚችለውን ሸሪዓዊ ብይን አስመልክቶም የተለያዩ አስተያየቶች ተሠንዝረዋል። ዳሩ ግን የኢኮኖሚው ዓለም ተጨባጭ ሂደት የሚያስረዳው የገንዘብ ኖት የግብይት ዋነኛ መሣሪያ መሆኑ በተዘዋዋሪ ከወርቅና ከብር ጋር ቢያመሳስለውም ራሱን የቻለ የዋጋ ተመን መሆኑን ነው።

ስለሆነም «ኒሷብ» የደረሰ የገንዘብ መጠን ኖሮት ዓመት ያሳለፈ ሙስሊም ከገንዘቡ 1/40ኛውን (2.5%) ለዘካ መክፈሉ የግድ ይሆናል።

ታዲያ ዘካ ግዴታ የሚሆንበት አነስተኛ የገንዘብ መጠን (ኒሷብ) የሚገደብበት መሠረት የወርቅ ዋጋ ወይስ የብር? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ ብዙኃኑ የዘመናችን ሊቃውንት የመረጡት ሚዛን ደፊ አቋም በወቅቱ ከሁለቱ የኒሷብ ዋጋዎች አነስተኛ በሆነው ላይ እንደሚሆን ነው።

ለምሳሌ፡-ዘካ በሚወጣበት ወቅት የአንድ ግራም ወርቅ ዋጋ 500 ብር ቢሆን ይህንን በ85 ስናበዛው የወርቅ ኒሷብ ዋጋ ይሰጠናል፡-

500 x 85 = 42,500 ብር ይሆናል፤

የብር (ሲልቨር) ዋጋ ደግሞ በግራም 25 ብር ቢሆን ይህንን በ595 ስናበዛው የኒሷቡን ዋጋ ይሠጠናል፡- 25 x 595 = 14,875 ይሆናል፤

ይህ ውጤት ከወርቁ የኒሷብ ዋጋ ያንሳል። በመሆኑም የገንዘብ ኖት ዘካ በወርቅ ሳይሆን በብር ዋጋ ላይ የተመሠረተ ይሆናል ማለት ነው። በአሁኑ ጊዜ ያለው ተመን የሚያሳየንም የብር ኒሷብ ዋጋ ከወርቅ ኒሷብ ዋጋ እጅግ እንደሚያንስ ስለሆነ ቢያንስ 595 ግራም ብር የሚገዛ የገንዘብ መጠን ያለው ባለሀብት 1/40ኛውን (2.5%) ወጪ ማድረግ ይጠበቅበታል።

> **መስጂድ ለመገንባት፣ ት/ቤቶችን ለማቋቋም ፣ ጠቃሚ መጻሕፍትን አትሞ ለማሰራጨት ፣ የሕክምና ማዕከላትን ለመመሥረትና ለመሳሰሉት የበጎ ተግባር መስኮች የዘካ ገንዘብን ማዋል የማይፈቀድ ይሆናል ማለት ነው።**

## የንግድ ዘካ

ለሽያጭ የቀረበ ማንኛውም ሸቀጥና ዕቃ ድምር ተመኑ ከላይ የተጠቀሰውን የጥሬ ገንዘብ «ኒሷብ» የሚያክል ከሆነ ዓመት በሞላው ጊዜ ከዋጋው 1/40ኛውን ለዘካ መውጣት ይኖርበታል።

የንግድ ዘካን አስመልክቶ ማስተዋል የሚሹ በርካታ ነጥቦች አሉ፡-

1. የንግድ ዘካ ግዴታ የሚሆነው ለሽያጭ በተዘጋጁ ንብረቶች ዋጋ ላይ ብቻ ነው። በዚህም መሠረት ለንግዱ ተግባር አጋዥ የሆኑ ማሽኖች፣ ማመላለሻ መኪናዎች፣ ታክሲዎች፣ ለኪራይ የተዘጋጁ ንብረቶችና የመሳሰሉት የዘካ ግዴታ አይመለከታቸውም። ሆኖም ከነዚህ የሚገኘው የገንዘብ ገቢ ለዘካ ብቁ ሆኖ ዓመት ከሞላው እንደማንኛውም የዘካ ንብረት ይታያል።ወደ ሸቀጥነት ተቀይረው ለሽያጭ የሚቀርቡ ጥሬ ዕቃዎች በጥሬ ዕቃነታቸው ዋጋቸው ተተምኖ ዘካ ሊወጣላቸው ይገባል።

2. የንግድ ዘካ ግዴታ የሚሆነው ለሽያጭ በቀረቡት ንብረቶች ድምር ተመን/ዋጋ ላይ እንጂ በንብረቶቹ ራሳቸው ላይ አይደለም። በዚህም መሠረት፡-

2.1 እንደ ከብቶችና ወርቅ ያሉ ሌሎች የዘካ ንብረቶች ለሽያጭ ከቀረቡ የሚመለከታቸው የንግድ ዘካ ብቻ መሆኑን ብዙ ሊቃውንት ይጠቅሳሉ፤ ስለሆነም ዋጋቸው ተተምኖ የንግድ «ኒሷብ» ከደረሰ 1/40ኛው ወጪ ይሆናል እንጂ ሌላ ግዴታ አይመለከታቸውም።

2.2 በንግዱ ዓለም ለሽያጭ የቀረቡ ንብረቶች እየተሸጡ በሌላ መተካታቸው የተለመደ ነውና ሸቀጦቹ ራሳቸው ዓመት ሊሞላቸው የግድ አይደለም፤ ዘካው የተያያዘው ከሸቀጦቹ ካፒታል/ዋጋ ጋር ነውና።

2.3 የንግድ ዘካ ሲሰላ ከሌላ ጥሬ ገንዘብ ጋር ተደምሮ መሆን ይገባዋል። ይህ ጊዜውንም (የዘካ ዓመቱን)፣ መጠኑንም (ኒሷቡንም) የሚመለከት ነው። ለምሣሌ፡- አንድ ሰው ለዘካ የደረሰ ጥሬ ገንዘብ በረመዳን ወር ቢያገኝና ዓመት ሳይሞላው በተወሰነው ገንዘቡ ለንግድ የሚሆኑ ሸቀጦችን ቢገዛ በዘካው ላይ የሚያስከትለው ለውጥ የለም፤ በሚቀጥለው ረመዳን ወር የሸቀጦቹን ድምር ተመን አውጥቶ ከተረፈው ጥሬ ገንዘብ ጋር በማዳበል ዘካ ያወጣል።

እንደዚሁም፡- አንድ ሙስሊም ጥሬ ገንዘብና ሌላ የንግድ ሸቀጥ ኖሮት ሁለቱም እያንዳንዳቸው ኒሷብ ያልደረሱ ሆነው የሁለቱ ድምር ኒሷብ ቢሞላ ከድምሩ ዘካ ማውጣት ይጠበቅበታል።

3. ንግድ ሽያጭ ትርፍ ዘካ መታሰብ የሚጀምረው ለሽያጭ ከሚቀርበው ሸቀጥ ካፒታል መነሻ ስለሆነ አዲስ የዘካ ዓመት አይጀምርለትም።

ለምሣሌ፡-አንድ ባለሀብት በዓመቱ መጀመሪያ በ100 ሺህ ብር ሸቀጦችን ሸምቶ ንግድ ቢጀምርና በዓመቱ መጨረሻ የ30ሺህ ብር ትርፍ ቢያገኝ ዘካ የሚያወጣው ከ130 ሺህ ብር ይሆናል። ኪሳራም ቢያጋጥመው እንዲሁ በዓመቱ መጨረሻ ያለውን ንብረት መጠን ተምኖ 1/40ውን ማውጣት ብቻ ነው የሚኖርበት፤ የ100 ሺህ ብር የንግድ ሸቀጥ ገዝቶ በዓመቱ ማብቂያ የ20 ሺህ ብር ኪሳራ ቢደርስበት ዘካ የሚያወጣው ከ80 ሺህ ብር ብቻ ይሆናል ማለት ነው።

በመሆኑም ለሽያጭ የቀረበው ንብረት ዘካ ሲሰላ የሚታሰበው ንብረቱ የተገዛበት ዋጋ ሳይሆን በዘካው ወቅት የሚሸጥበት ዋጋ መሆኑን ማስተዋል ያሻል።

የንግድ አክሲዮን ባለቤት የሆነ ግለሰብ የአክሲዮኑ ድርሻ የሚወክለውን የሽያጭ ዕቃ ተመንና ትርፍ ከሌላ ጥሬ ገንዘብ ጋር ደምሮ በማስላት ዘካ ያወጣለታል፤ ድርጅቱ የአክሲዮኖቹን ዘካ የሚያወጣ እንደሆነ ግን ግለሰቡ ዳግም ወጪ አይጠበቅበትም።

በመሬት ውስጥ ተቀብሮ የተገኘ የድሮ ቅርስ (ሪካዝ) ቀድሞ የሙስሊም ንብረት እንደነበር የሚጠቁም ምልክት ካለው ለጠፋ ንብረት የሚሰጠው ኢስላማዊ ብይን ይኖረዋል፤ ካልሆነ ግን ጥቅል መጠኑ ይነስም ይብዛም 1/5ኛው (20%) ወጪ ይሆናል። ሆኖም የተገደበ የኒሷብ መጠን የሌለው ከመሆኑ፣ ከወጪ አደራረጉና ከሌሎች ሁኔታዎች አንፃር በዘካ ህግ ስር የማይካተት መሆኑ የብዙኃኑ ሊቃውንት አቋም ነው።

## የዘካ አወጣጥን የተመለከቱ ጥቅል ነጥቦች

### 1. ዘካን በየዓመቱ ማውጣት

ከአዝርዕት በስተቀር ያሉ የዘካ ንብረቶች ከ«ኒሷብ» እስካልጎደሉ ድረስ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየዓመቱ የዘካ ወጪ ይመለከታቸዋል።

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .

### 2. ዘካና ዕዳ

ዕዳ በዘካ ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ አስመልክቶ የኢስላም ሊቃውንት የተለያየ አቋም ይዘዋል። ሆኖም ሚዛን የሚደፋውን አመለካከት መጥቀሱ በቂ ይሆናል፤

**2.1** ዕዳ ያለበት ሰው ዕዳውን የሚከፍልበት ጊዜ ካልደረሰ በስተቀር ከዘካ ሒሳቡ ላይ ዕዳውን አይቀንስም። ምክንያቱም በእጁ ባለው ገንዘብ መጠቀም እስከቻለ ድረስ ዘካውን የማውጣት ኃላፊነት ስለሚኖርበት ነው። ዕዳውን የሚመልስበት ወቅት ከደረሰ ወይም ከቀረበ ግን መጠኑን ቀንሶ ሒሳቡን ያሰላል።

**2.2** ሌላ ሰው ዘንድ የዕዳ ገንዘብ ያለው ግለሰብ ደግሞ በፈለገው ጊዜ በእጁ የሚያገኘውና የሚጠቀምበት ባለመሆኑ ገንዘቡ እስኪመለስለት ድረስ ዘካ የማውጣት ግዴታ አይኖርበትም፤ በአንድ ንብረት ላይ ሁለት ዘካ አይወጣምና! ሆኖም ገንዘቡ የሚመለስበት ጊዜ ደርሶ ባለዕዳው ዕዳውን ለማስረከብ ዝግጁ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ የዘካ ሒሳቡ በባለንብረቱ ላይ የሚታሰብ ይሆናል።

### 3. ዘካና ወርሀዊ ገቢ

ለዘካ የደረሰ የንብረት መጠን ኖሮት ዓመት ሳይሞላው ሌላ ጭማሪ ያገኘ ግለሰብ ያገኘው የንግድ ትርፍ ወይም ከቀድሞ ከብቶች የተወለደ ግልገል እስካልሆነ ድረስ አዲስ የዘካ ዓመት ይጀምርለታል።

በዚህም መሠረት ገቢውን የሚያጠራቅም ደሞዝተኛ ጥርቅሙ የዘካ ኒሷብ ከደረሰበት ጊዜ አንስቶ ዓመት መቁጠር ይጀምራል። ከዚያ በኋላ በየወሩ የሚያገኘው ደሞዝ ለየብቻው ኒሷብ ባይሞላ እንኳ ዓመት ሲሞላው 1/40ኛውን (2.5%) ለዘካ ወጪ ያደርጋል። ይህ መንገድ ለእያንዳንዱ ወር አዲስ ሒሳብ በማስላት ከዓመት በኋላ በየወሩ ዘካ ማውጣት ስለሚያስፈልገው አፈፃፀሙ ለብዙዎች አሰቸጋሪ ይሆናል።

ስለሆነም ቀላልና ገር የሆነው መንገድ በዓመቱ መጨረሻ ላይ በእጅ ያለውን ገንዘብ ባጠቃላይ በማስላት 1/40ኛውን ማውጣት ነው። በዚህ ጊዜ የተወሰነው የገንዘብ መጠን ዓመት ሳይሞላው በቅድሚያ ዘካ ይወጣለታል ማለት ነው።

### የዘካ አሰጣጥን የተመለከቱ ጥቅል ነጥቦች

1. ዘካን ለዘመድ መስጠት፡- ማስተዳደሩ ግዴታ ላልሆነ ዘመድ ዘካን መስጠት ይፈቀዳል። ወጪያቸውን መሸፈን ግድ ለሚል የቅርብ ዘመዶች መስጠቱ ግን ወጪን በማስቀረት ራስን መጥቀም በመሆኑ የተከለከለ ይሆናል። በዚህም መሠረት ለወላጆች፣ ለልጆችና ለሚስቶች ዘካ መስጠት ይከለከላል።

2.የአላህ መልዕክተኛ ቤተሰቦችና ዝርያዎች፡- የዘካ ገንዘብን መቀበል አይችሉም።

3.ሙስሊም ላልሆነ ሰው ዘካ መስጠት አይቻልም። ከዘካ ውጪ ያለ ተራ ምፅዋት መስጠት ግን አይከለከልም ።

4.ዘካ ግዴታ የሆነበት ሰው ወቅቱ ከደረሰ በኋላ በቂ ምክንያት ሳይኖር ማዘግየት የለበትም።

5.የሁለት ዓመት ዘካ አስቀድሞ ማውጣት እንደሚፈቀድ የሚያሳይ ሀዲሣዊ መረጃ አለ።

6.ዘካን ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር ማሻገር፡- ይበልጥ ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ እንደሚፈቀድ በርካታ ሊቃውንት ይጠቅሳሉ።

____________*********____________

# ዘካተል ፊጥር እና አፈጻጸሙ



ዘካተል ፊጥር ከረመዳን ወር ፆም መጠናቀቅ ጋር በተያያዘ ግዴታ የሚሆን የዘካ አይነት ነው፡፡ ዘካተል ፊጥርን መስጠት እያንዳንዱ ሙስሊም ላይ በነፍስ ወከፍ ግዴታ ሲሆን፤ እያንዳንዱም አባወራ የራሱን ጨምሮ በእርሱ ስር ላሉ ቤተሰቦቹ ሁሉ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ኢብኑልሙንዚር 'አል-ኢጅማዕ' በተሰኘው ኪታባቸው ‹‹ዒልምን የተማርንባቸው ዑለማዎች ሁሉ ዘካተል ፊጥር ግዴታ መሆኑን ተስማምተውበታል›› በማለት የጉዳዩን ግዴታነት ከሚያመለክቱት ነብያዊ ሀዲሶች በተጨማሪም የኡለማዎችን አጠቃላይ ስምምነት (ኢጅማዕ) የተገኘበት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

## የተደነገገበት ጥበብ

ድሆች በበዓሉ (ዒድ) ዕለት ሰዎችን ከመለመን እንዲድኑና የእለቱ ደስታ ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም በፆም ወቅት ተከስተው ላለፉ አንዳንድ ጉድለቶች (ግድፈቶች) ማሟያ እንዲሆን ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ ዐብደላህ ኢብን አባስ እንዲህ ይላሉ፡፡‹‹የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ዘካተል ፊጥርን ለፆመኛ ለ'ለግዉ' (ጥቅም ለሌላቸው ውድቅ የቀልድ ንግግሮችና ተግባሮች) እና ለ'ረፈስ' (ፆታዊ ስሜትን ቀስቃሽ ለሆኑ ንግግሮች) ማፅጃ፤ ለምስኪኖች (ድሆች) መብል ሲሆን በግዴታ መልኩ ደንግገውታል፡፡ ስለዚህም ከኢድ ሰላት በፊት (ዘካውን በመስጠት ግዴታውን የተወጣ) ተቀባይነት ያለው ዘካን ሰጥቷል፤ ከኢድ ሰላት በኋላ ዘካውን የሰጠ ከሌላ ግዴታ ያልሆነ ሰደቃ አንዱ እንደሆነ ይታሰብለታል፡፡›› (አቡዳውድ እና ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል)

## የዘካተል ፊጥር መጠን

ኢብኑ ኡመር ሀዲስ ላይ እንዲህ የሚል መልዕክት ተላልፏል ‹‹የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ከተምር ወይም ከገብስ አንድ ‹‹ሷዕ›› በእያንዳንዱ ሙስሊም፤ ባሪያ፣ ጨዋ (ባሪያ ያልሆነ)፣ሴት፣ ህፃን፣ አዋቂ ላይ ግዴታ አድርገዋል፡፡ እንዲሁም ሰዎች ወደ (ዒድ) ሰላት ከመውጣታቸው በፊት ለሚገባቸው ሰዎች እንዲደርስ አዘዋል፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ሷዕ የመስፈሪያ አይነት ሲሆን በድሮ ጊዜ የነበረ የእህል መስፈሪያ ነው። በዘመናዊ መለኪያ አንድ ‹‹ሷዕ›› 2.04-2.5 ኪ.ግ ይመዝናል፡፡ 1 ሷዕ = 4 የሁለት ዕጅ እፍኞች ነው።

## ዘካተል ፊጥር በማን ላይ ግዴታ ይሆናል?

ዘካተል ፊጥር ግዴታ የሚሆነው ሁለት መስፈርቶችን ባሟላ ሰው ላይ ብቻ ነው፤ እነርሱም

1. ሙስሊም በሆነ

2. ዘካተል ፊጥር ማውጣት ግዴታ በሚሆንበት ቀን እና ሌሊት፤ ለራሱ እና ለቤተሰቦቹ የሚበቃ መብል ኖሮት የተረፈው እና ተጨማሪ ነገር ያለው፡፡

## ዘካተል ፊጥር የሚሰጠው መቼ ነው?

ዘካተል ፊጥርን ከ(ዒድ) ሰላት በኋላ ማዘግየት የተከለከለ ሲሆን፤ ማውጣቱ ግዴታ የሚሆንበት ወቅት የሚጀምረው ከረመዳን የመጨረሻው ዕለት ፀሀይ ከጠለቀችበት ወይም ዒድ መሆኑ ከተረጋገጠበት ሰዓት አንስቶ ነው፡፡ ነገር ግን ኢብኑ ዑመርን ጨምሮ ሌሎቹም ሰሀቦች ያደርጉት እንደነበረው ከዒድ አንድ ወይም ሁለት ቀን ቀድሞ ዘካተል ፊጥርን ማውጣት ይፈቅዳል፡፡

## ለዘካተል ፊጥር የሚሰጡ የእህል አይነቶች

ዘካተል ፊጥር ሙስሊሞች ከሚመገቡዋቸው እንደ ሩዝ፤ በቆሎ፤ ጤፍ.... ባሉ የምግብ እህል አይነቶች ነው። መልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) በሀዲስ የጠቀሷቸው የምግብ እህሎች (እንደ ገብስ፤ ተምር፤ ዘቢብ) የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ ነገር ግን የምግብ አይነቶቹ በነዚህ ላይ ብቻ እንደማይገደቡ የሻፊዒያ እና የማሊኪያ መዝሀብ ዑለማዎች ሲስማሙበት ሸይኹል ኢስላምም የመረጡት አቋም ነው፡፡

የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ከተምር ወይም ከገብስ አንድ ‹‹ሷዕ›› እንዲወጣ ማዘዛቸውን በተመለከተም እነዚህ ዑለማዎች የሚሰጡት ምላሽ ‹‹መልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እነዚህን የምግብ አይነቶች የጠቀሱት የመዲና ሰዎች በምግብነት ይጠቀሟቸው የነበሩ ከመሆናቸው አንፃር ነው፡፡ ስለሆነም የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እነሱ የሚያገኙትንና የሚመገቡትን የምግብ አይነት ነው እንዲያወጡ ያዘዟቸው›› የሚል ነው፡፡ በዚህም መሰረት በማንኛውም አካባቢ የሚኖር ሙስሊም ማህበረሰቡ አዘውትሮ ከሚመገባቸው የምግብ እህሎች ዘካተል ፊጥሩን መልዕክተኛው ሲጠቀሙበት በነበረው መስፈርያ መጠን ማውጣት ይችላል፡፡

## ዘካተል ፊጥር መሰጠት የሚገባው ለማን ነው?

በዚህ ጉዳይ ላይ ዑለማዎች ሁለት አይነት አመለካከት ያለቸው ሲሆን ሚዛን የሚደፋው ሀሳብ ለምስኪኖች እና ለድሆች ብቻ ይሰጣል የሚለው ነው፡፡ ምክንያቱም በኢብኑ አባስ ሀዲስ ላይ መልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ‹‹ለምስኪኖች መብል ...›› በማለት ዘካተል ፊጥር የተደነገገበትን አላማ ከመግለፃቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡

## ዘካተል ፊጥርን በገንዘብ ተምኖ መክፈል

ዘካተል ፊጥርን በዋጋ ተምኖ መክፈል አይፈቀድም። ምክንያቱም በኢብኑ አባስ ሀዲስ ላይ መልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ዘካተል ፊጥር የተደነገገበትን አላማ ሲገልፁ ‹‹ለምስኪኖች መብል ...›› በማለታቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አቢ ሰዒድ አልኹድሪይ እንዲህ ብለዋል "የአላህ መልዕክተኛ በነበሩበት ዘመን ዘካተል ፊጥር የምናወጣው ከምግብ አንድ ሷዕ ነበር" ብለዋል። ዘካተል ፊጥርን ከተገደበለት ጊዜ ማስቀደም ወይም ማቆየት እንደማይቻል ሁሉ የአወጣጡን አይነትም መቀየር አይቻልም። ዒባዳ ሁልጊዜ በአላህ የሚደነገግ እንጂ በአስተያየት የምንፈፅመው አይደለም። ማንኛዉም ሙስሊም ዒባዳው እንዳይበላሸበት ሊጠነቀቅ ይገባዋል። በገንዘብ መተመን በቀደምት ሰለፎች አልተፈፀመም። ከጥቂቶች በቀር አብዛኞቹ የኢስላም ሊቃውንት በገንዘብ ማዉጣትን ይቃወማሉ። አል-ኢማም ማሊክ፣ አል-ኢማም አሻፊዒይ እና አል-ኢማም አህመድ ይህ መዝሀባቸው ነው። ስለዚህም በተባለው መልኩ በእህል ያወጣ ሰው በሁሉም ስምምነት ትክክለኛ ዒባዳ ሰርቷል። እያንዳንዱ ሙስሊም በፆመበት ቦታ ዘካተል ፊጥርን ማውጣቱ ቢሆንም የሚያስፈልገው ነገር ግን ምግብ የሚቀበል ምስኪን ሰው የሌለበት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በቤተሰቦቻቸው ወይም ጓደኞቻቸው አማካኝነት ችግረኞች ወዳሉበት ቦታ መላክ ይችላሉ። በጥቅሉ ማንኛውም ሰው ኢስላምን በሚገባ ለመተግበር መሞከር ይገባዋል።

تقبل الله الصّيام والقيام وجميع الطّاعات

**(ከሸይኽ ሳሊሕ አል ዑሠይሚን (ረሂመሁላህ) ጽሁፍ የተተረጎመ)**

____________*********____________

# ነሲሓ

# አበይት



- አንድነት መተባበር እና ኺላፍ በሸሪዓዊ መርሆዎች እና  በተዛቡ ግንዛቤዎች መካከል
- የዘረኝነት ማጥ
- የኮንዶሚኒየም ቤትን በረጅም ጊዜ ክፍያ መግዛት በሸሪዓ እይታ

# አንድነት መተባበር እና ኺላፍ

## በሸሪዓዊ መርሆዎች እና በተዛቡ ግንዛቤዎች መካከል

ባለፈው እትም የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማዊ የለውጥ ጉዞ ከገጠሙት መሰናክሎች ዋነኛ የሆነውን የዑለማዎች የመግባቢያ እና የትብብር ሰነድ በአሽአሪያ/ ማትሩዲያ እና በሱፍያ አስተሳሰብ ማእቀፍ የታጠረ መሆን አለበት የሚለውን የአንዳንዶች ሙግት ትክክለኛ አለመሆኑን በመረጃ ምላሽ በመስጠት አሰባሳቢ የሆነውን የሰሐቦች፣ የታቢዒዮች እና የታላላቅ አኢማዎች መንገድ ለአንድነት የማእዘን ድንጋይ መሆኑን ጠቁመናል።

ዛሬ ደግሞ ሙስሊሞችን ሊያወዛግቡ እና አላስፈላጊ ንትርክ ውስጥ ሊከቱ በሚችሉ ጥቂት ሸሪዓዊ (ቴክኒካል) ቃላት ዙሪያ ትክክለኛውን ሚዛናዊ ግንዛቤ ለመስጠት ጥቅል ጥቆማዎችን ለማስፈር እንወዳለን።

### 1. ኢስላማዊ ወንድማማችነት ፣ አንድነት እና መተባበር

ሙስሊሞች በቁርአን እና በሱና በመዳኘት ልዩነቶችን ለማጥበብ ብሎም ለማስወገድ መጣር እንደሚገባቸው እሙን ነው። በተለይም በዑለማዎች መካከል የመግባባትና የትብብር ስሜት ሲፈጠር ለመደማመጥ፣ አንዱ የሌላውን መረጃ ለመስማት እና በሐቅ ላይ አንድ ለመሆን መንገዱን ይከፍታል። አንድነትን መጠበቅ እና ከልዩነት መራቅ ለሙስሊሙ ኡማ እጅግ አስፈላጊና በብዙ የቁርአን አንቀፆች የታዘዝነው ሸሪዓዊ ተልዕኳችንም ነው።

ኢስላማዊ ወንድማማችነትን፣ አላህን መፍራትን እና በጎ ተግባራትን መሰረት ባደረጉ የጋራ አጀንዳዎች ላይ የሚደረግ መልካም ትብብር በኢስላም ጥላ ስር ለተሰባሰቡ ሁሉ በማንኛውም ጊዜ አስፈላጊ ሸሪዓዊ ትእዛዝ ነው። በዲናዊ ምልከታቸው የተለያየ አካሄድ ያላቸው ሰዎችም በመልካም ነገር ላይ መተባበር እንዳለባቸው ስናፀናም ለአንድነት ቦታ አንሰጥም ማለት አይደለም። አላህ እንዲህ ብሏል፤

(وَتَعَاوَنُواْ عَلَى ٱلۡبِرِّ وَٱلتَّقۡوَىٰۖ وَلَا تَعَاوَنُواْ عَلَى ٱلۡإِثۡمِ وَٱلۡعُدۡوَٰنِ) المائدة 2

*{በበጎ ነገር እና አላህን በመፍራት ተረዳዱ። ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ። አላህንም ፍሩ!} [አል-ማኢዳህ 2]*

መግባባት እና መተባበር ለሙስሊሙ ያላቸው አስፈላጊነት ከፍተኛ መሆኑ እሙን ነው። በተለይም መብቶቻችንን ለማስከበር፣ በአስተዳደራዊ እኩልነት ተጠቃሚ ለመሆን እና ሃይማኖታዊ ግዴታችንንም ለመወጣት ትብብር እና የአላማ አንድነት ያስፈልገናል። የተለያየ አይነት አመለካከት ብሎም ዐቂዳ ባለበት ሁኔታ የአብሮነታችንን አስፈላጊነት የሚያጎላው የጋራ ጥያቄዎችን በጋራ ማቅረብ፣ መብቶቻችንን ማስከበር፣ እና አስተዳደራዊ ተቋማትን በጋራ ማራመድ የሚሉትን አጀንዳዎች ስናስብ ነው። ይህንን መዘንጋት ወይም በተሳሳተ ግንዛቤ መረዳት ለብዙ የአስተሳሰብ ሁከቶች ዳርጓል። መሰረታዊ ልዩነቶችን በውይይት ለማጥበብ ብሎም ለማጥፋት በቁርአን እና ሱና ጥላ ስር ተሰባስቦ አንድ ለመሆን ባይቻል እንኳ ኢስላማዊ ወንድማማችነትን መሰረት ያደረገ መግባባት እና መተባበርን ለማረጋገጥ የሚደረጉ ጥረቶች አላማ፤ የተለያዩ አመለካከት ያላቸውን ወገኖች በማቻቻል በሙስሊሙ የጋራ አጀንዳዎች ላይ በትብብር የመሥራትን ባህል ማዳበር ነው። ነገር ግን አንዳንዶች ዘንድ የጋራ ጉዳዮች ላይ ለመተባበር ሁሉም ወገን ማንነቱን በመፋቅ በአንድ አስተሳሰብ ዙርያ መታጠር ወይም ከአቋሙ በመንሸራተት ለሌላኛው ወገን አመለካከት እጅ መስጠት አለበት የሚል የግንዛቤ ግድፈት ዳብሯል። ከልዩነት ጋር መተባበር እንደማይቻል በማሰብ የአብሮነት ግዴታ ለመወጣት ሁሉም ሰው ከሚያምንበት ዐቂዳ እና መንሀጅ መንሸራተት እንደሚጠበቅበት ማሰብ ከባድ የአረዳድ ግድፈት ነው።

በአንድነት እና ትብብር ዙርያ የሚከሰት የግንዛቤ ግድፈት የሚያስከትላቸው መዘዞች ሳንካ ከባድ ለመሆኑ ባለፉት ወራት የኢትዮጵያ ኡለማዎችን የትብብር እና የመግባቢያ ሰነድ ለማዘጋጀት የተደረገው እልህ አስጨራሽ ጉዞ አይነተኛ ማሳያ ነው።

**አንዳንዶች ዘንድ የጋራ ጉዳዮች ላይ ለመተባበር ሁሉም ወገን ማንነቱን በመፋቅ በአንድ አስተሳሰብ ዙርያ መታጠር ወይም ከአቋሙ በመንሸራተት ለሌላኛው ወገን አመለካከት እጅ መስጠት አለበት የሚል የግንዛቤ ግድፈት ዳብሯል : :**

በሂደቱ ፅንፈኞች ባንፀባረቁት አቋም፤ የጋራ አጀንዳዎች ላይ ለመተባበር ሌላኛው ወገን በተውበት ወደነሱ አቋም መጥቶ ልዩነቶች ሁሉ መቀረፋቸውን እንደ መስፈርት አስቀምጠዋል።

የሱፍያ፣ የአሽዓሪያና ማትሩዲያ እምነቶች የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ገዥ እምነት ሆነው በሰነዱ ውስጥ እንዲሰፍሩ መሞገታቸውም ይህንን ስር የሰደደ የግንዛቤ ግድፈታቸውን አጉልቶ ያሳየ ነበር። የኢስላማዊ አንድነት ጥሪ አላማ፤ የተለያየ ዐቂዳና አካሄድ ያላቸውን ወገኖች አግባብቶ የጋራ በሆኑ አጀንዳዎች ላይ በመተባበር ተቋማቸውን ከተፅእኖ ነፃ ማድረግ እና መብቶቻቸውን ማስከበር እንጂ አንዱን በሌላው ስር መጨፍለቅ አለመሆኑን እያወቁ መሆኑ በእጅጉ ያስተዛዝባል።

በዚህ ረገድ ሳይጠቀስ የማይታለፈው ሌላኛው የግንዛቤ ግድፈት ከአንድነት እና ትብብር ጋር የተያያዙ ሸሪዓዊ መመሪያዎችን በተሳሳተ መልኩ በመረዳት፤ በአቋም ከኛ ከሚለዩ ሰዎች ጋር የሚደረጉ የትብብር ጥረቶችን ሁሉ በሸፍጥ፣ አድርባይነት እና በሽርክ እና ቢድዓ ላይ መስማማት አድርጎ ማሰብ ነው። ሸሪዓዊ ገደቦችን ሳይጥሱ በጋራ አጀንዳዎች ላይ ከሙኻሊፎች ጋር መተባበር ተገቢ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። ይህ የሰለፎችን መንገድ በመከተል የሚታወቁ ኡለማዎች ሁሉ የሚስማሙበት ከመሆኑም ባሻገር በበርካታ ትምህርቶች በስፋት የተዳሰሰ ጉዳይ ሆኖ ሳለ፤ ጉዳዩን ከቢድዓ አራማጆች ጋር ድንበር ያለፈ መለሳለስ አድርጎ በማቅረብ ተደናግረው የሚያደናግሩት፤ ምናልባት በዕውቀት ማነስ ወይም በፅንፈኛ መንሀጅ በመጠለፍ ሲከፉም ያረጁ የኺላፍ ሂሳቦችን ለማወራረድ ካልሆነ ሌላ ምክንያት አናገኝለትም።

### 2. ኺላፍ እና ኢንካሩ'ል-ሙንከርን በተመለከተ

ሸሪዓው በሚያዘው መሰረት ኺላፍ / ውዝግብን እንዴት እንደሚስተናገድ አለማወቅ ብዙ ቀውሶችን ያስከትላል። ብዙውን ጊዜ ለአንድነት ከሚደረጉ ጥሪዎች ጋር በተያያዘ አሳሳቢ አጀንዳ ሆኖ የሚቀርበውም ለዚህ ነው።

ሁሉንም ዲናዊ ውዝግቦች ቁርአን እና ሱናን መሰረት ባደረገ ውይይት መፍታት እንዳለብን ጌታችን አላህ አሳስቦናል፤

فَإِنْ تَنَازَعْتُمْ فِي شَيْءٍ فَرُدُّوهُ إِلَى اللَّهِ وَالرَّسُولِ إِنْ كُنْتُمْ تُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ ذَلِكَ خَيْرٌ وَأَحْسَنُ تَأْوِيلًا – سورة النساء 59

*“ …በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ፤ በአላህ እና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትሆኑ / የተከራከራችሁበትን ጉዳይ/ ወደ አላህ እና ወደ መልዕክተኛው መልሱት። ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው” / አን-ኒሳእ 59*

የኺላፍ አጀንዳዎች በይዘታቸው የተለያዩ እንደመሆናቸው የሁሉንም አይነት ኺላፎች ድንበር ባለማወቅ የሚፈጠሩ ፅንፎች ከማንም የተሰወሩ አይደሉም። ከፊሎች በመሰረታዊ የእምነት ጉዳዮች የሚነሱ ኺላፎችን ጭምር መተቻቸት እና መተራረም፤ የመቻቻል እሴትን ማጥፋት እና ፅንፈኝነት አድርገው ያቀርባሉ። ሌሎች ደግሞ መሰረታዊ ባልሆኑ የኺላፍ አጀንዳዎች ዙርያ ዘወትር የሰላ ትችቶችን ሲያራግቡ ይስተዋላል። ሁለቱም የኺላፍን አጀንዳ በአንድ ዕይታ ብቻ የቃኙ ፅንፎች ናቸው።

ሸሪዓዊ እውቅና በምንቸራቸው “ሙዕተበር” በሆኑ የኢጅቲሀድ ኺላፎች ዙርያ መቻቻል አስፈላጊና ግዴታ ነው። በመሆኑም አመለካከትን ከመግለጽ ባሻገር ለጠንካራ ትችት እና ውግዘት የሚጋብዝ ጉዳይ የለም። ይህ ማለት ደግሞ መሰረታዊ የሸሪዓ መገለጫ የሆነውን ስህተትን የማረም መርሆ / ኢንካሩል ሙነከር/ መሻር አይደለም። በሁሉም የኺላፍ ጉዳዮች ላይ ማንኛውም የዳዕዋ ሚና ያለው ግለሰብ ወይም ተቋም ትክክለኛ ብሎ የሚያምነውን አመለካከት በመረጃ መግለጽ፣ ስህተቶችንም ማረም ሃይማኖታዊ ግዴታው ነው!

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

*ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .*

የሚያውቁትን በጥሩ ዘዴ ለሌሎች ማካፈልና ከስህተት መተራረም ከዲናዊ ግዴታነቱ ውጭ ንጹህ ተፈጥሯዊ አስተሳሰብም ነው።

ኺላፍን እና ተያያዥ ጉዳዩችን አስመልክቶ የሚነሱ ኺላፎች ሊቃኙ የሚገባበትን ትክክለኛ ግንዛቤ እና የኺላፍ አይነቶችን ለመረዳት ይረዳ ዘንድ ከዚህ በታች አጠር ያለ ማብራሪያ እናስቀምጣለን።

ከፊሎቹ የኺላፍ አይነቶች በመቻቻል የምናልፋቸው የኢጅቲሀድ ውጤቶች ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ መተራረም እና መረጃ የሚደግፈውን ሐቅ መግለጽ ግድ የሚሆንባቸው ናቸው።

የኺላፍ ጉዳዮችን በሁለት ከፍለን ማየት ግድ ይለናል፤

## 1ኛ– የሚያስወግዝ ተጻራሪ ኺላፍ

በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ሸሪዓዊ ፍርድ በግልጽ በቁርአናዊና በነቢያዊ አስተምህሮቶች የተቋጨና በቀደምት ዑለማዎች ሙሉ ስምምነት (ኢጅማዕ) የፀደቀ ከሆነ፤ የትኛውንም ዓይነት ውዝግብ አያስተናግድም፤ ብይኑን ያለምንም ማንገራገር ተቀብሎ ማስተናገድም ግዴታ ነው። ይህንን እውነታ ከተረዱ በኋላ በአጀንዳው ላይ ከተመለከተው ሸሪዓዊ አስተምህሮት ጋር የሚጣረስ አቋም ማንፀባረቅ አላህ ከዘረጋልን ቀጥተኛ ጎዳና ማፈንገጥ በመሆኑ ለውግዘት ይዳርጋል፤

وَمَن يُشَاقِقِ ٱلرَّسُولَ مِنۢ بَعۡدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُ ٱلۡهُدَىٰ وَيَتَّبِعۡ غَيۡرَ سَبِيلِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ نُوَلِّهِۦ مَا تَوَلَّىٰ وَنُصۡلِهِۦ جَهَنَّمَۖ وَسَآءَتۡ مَصِيرًا
— سورة النساء ١١٥

*{(የ)ምራቻ (መንገድ) ከተገለጠለት በኋላ መልዕክተኛውን የሚፃረርና ከሙእሚኖች መንገድ ሌላ የሚከተል የመረጠውን (ጥመት) እናሸክመዋለን፤ ጀሀነምም እናስገባዋለን፤ ከመመለሻነቷ (አኳያ)ም የከፋች ሆነች!} [አን‑ኒሳእ 115]*

በእርግጥ እውነትን ፍለጋ ለተሳሳቱ ዓሊሞች የሚሰጠው ማስተካከያ ክብራቸውን በሚጠብቅ ስርዓትና ሂደት እንጂ የጥመት አራማጆች ላይ እንደሚደርሰው ውግዘት አይደለም! ሆኖም ስህተት ማንም ይሥራው ማን ሁሌም ስህተት ነው! ኡለማዎች ፍጹም አይደሉም። ሁሉም ስህተት የመደበኛ «ኺላፍ» ሚዛን ላይ አይሰቀልምና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የአሊሞችን ስህተት በመቃረም "ይህ ጉዳይ የኺላፍ አጀንዳ ነው፤ እንቻቻል፤ አንተራረም" ማለት ተገቢ አይሆንም።

የቀደምት ሰለፎችን የጋራ ኢጅማዕ ጥሰው፤ ኋላ የመጡ አመለካከቶች መሰረታቸው መልካም ኒያ እና ሀቅን የመፈለግ ኢጅቲሀድ ቢሆን እንኳ ከነሱ ቀድሞ በተዋቀረው ኢጅማዕ ይዳኛሉ። በተለያዩ ርእሶች ኢጅማዕን ተፃርረው በየክፍለ ዘመናቱ የተነሱ ሀሳቦች ሁሉ አንድን ጉዳይ የኺላፍ አጀንዳ አያደርጉም። አጀንዳው በግልጽ ቁርአናዊና ነብያዊ አስተምህሮቶች የተቋጨና በቀደምት ዑለማዎች ሙሉ ስምምነት የተዘጋ የአንድነት ርዕስ እንጂ የኺላፍ ርዕስ አይደለምና! አለዚያ ማንም ሰው በዲን ስም ያሻውን አቋም ያለተቃውሞ እንዲያራምድ ሰፊ በር መክፈት ይሆናል!

## 2ኛ– የሚያቻችል ኺላፍ (ኺላፍ ሙዕተበር)

በርዕሶቹ ላይ የሚጠቀሱት ማስረጃዎች የሚጠቁሙትን መልዕክት በተመለከተ ቀደምት የኢስላም ሊቃውንት በግንዛቤ ልዩነት የተለያየ አቋም ያንጸባረቁ ከሆነና ጉዳዮቹ በዑለማዎች ዘንድ ሸሪዓዊ ምልከታን "ኢጅቲሃድ"ን የሚያስተናግዱ መሆናቸው ከታወቀ አንድ ዓሊም ከዚህ በፊት ከነበሩት የዑለማዎች አቋሞች አንዱን ቢመርጥ፣ ብሎም ቢሳሳት ፍርዱ እንደሙሉ ጥፋት ተወስዶ አይኮነንም፤ መልዕክተኛው ﷺእንደዚህ ብለዋል፡-

إِذَاحَكَمَ الْحَاكِمُ فَاجْتَهَدَ ثُمَّ أَصَابَ فَلَهُ أَجْرَانِ وَإِذَا حَكَمَ فَاجْتَهَدَ ثُمَّ أَخْطَأَ فَلَهُ أَجْرٌ"

*«አንድ ፈራጅ ሲፈርድ (እውነታን ለመረዳት) ተጣጥሮ ትክክል ከሆነ ሁለት ምንዳ (አጅር) አለው፤ ሲፈርድ (እውነታን ለመረዳት) ተጣጥሮ ከተሳሳተ ደግሞ አንድ አጅር አለው!» [ አል‑ቡኻሪይ (7352) ፣ ሙስሊም (1716)]*

የዚህ አይነት የኺላፍ አጀንዳዎችን መሰረት በማድረግ ሰዎችን ኢላማ ማድረግ፤ ልዩነትንም ማጉላት አይፈቀድም።

ሆኖም ሐዲሱ የሚያስረዳው በዚህኛውም የኺላፍ አይነትም ቢሆን፤ ትክክለኛውን አቋም ለማወቅ ሁሉም እንደየአቅሙ በጥሩ ዘዴ መጣር እንደሚጠበቅበት ነው።

መተራረም ሁልጊዜ አስፈላጊ ቢሆንም፤ በዲን ውስጥ የሚከሰቱ የኺላፍ አይነቶች ሁሉ ግን ተመሳሳይ ብይን የላቸውም።

**የቀደምት ሰለፎችን የጋራ ኢጅማዕ ጥሰው ፤ ኋላ የመጡ አመለካከቶች መሰረታቸው መልካም ኒያ እና ሀቅን የመፈለግ ኢጅቲሀድ ቢሆን እንኳ ከነሱ ቀድሞ በተዋቀረው ኢጅማዕ ይዳኛሉ ።**

ከላይ እንደተብራራው **ከፊሎቹ የኺላፍ አይነቶች በመቻቻል የምናልፋቸው የኢጅቲሀድ ውጤቶች ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ መተራረም እና መረጃ የሚደግፈውን ሐቅ መግለጽ ግድ የሚሆንባቸው ናቸው። ስለዚህ ሁሉንም ኺላፎች ማክረርና አመለካከቶችን በማረም ረገድም ጽንፍ መያዝ አያስፈልግም። በተቃራኒው ደግሞ ግልጽ የሆኑ መረጃዎች የመጡባቸውንና በቀደምት ሊቃውንት ስምምነት የተቋጩ የኢስላም መርሆዎችን የኺላፍ አጀንዳ አድርጎ ለማሳየት መሞከርም ተቀባይነት የለዉም።***

አል ኢማም አህመድ ኢብኑ ሀንበል መሰረታዊ ባልሆኑ የኢጅቲሀድ ጉዳዮች መወዛገብ፣ በተቃረኑን ሰዎች ላይ አቋም ስለመያዝና በጥመት ስለመፈረጅ እንዲህ ብለዋል፤ «ምንም እንኳ ብንቃረነው፤ መነሻ ያለው አቋም ያንፀባረቀን ሰው አላወግዘውም» ኢብኑ ሙፍሊህ አል ፉሩዕ 1/150

ይህ ከታላቅ አሊም የተነገረ ታላቅ መርሆ ሲሆን፤ ሸይኽ አብዱሰላም ኢብኑ በርጀስ (ረሒመሁላህ) እንዲህ ያብራሩታል፤

«ይህ የኢማም አህመድ ኢብኑ ሀንበል ንግግር ሸሪዓዊ መረጃዎች ትክክለኝነቱን የሚያረጋግጡት ሲሆን፤ ፍትህዊነትን መገለጫ ያደረጉ ኡለማዎች ሁሉ የተዋቡበት መርሆ ነው። ይህንን መርሆ ተግባራዊ ማድረግ፤ ጥላቻንና ጠላትነትን ከሚያወርስ ንትርክ ሙስሊሙን ይጠብቀዋል። የእነዚህን ቃላት ማብራሪያ በሚከተሉት ነጥቦች አሳጥሮ ማቅረብ ይቻላል፤

1) የኢልም ርዕሰ ጉዳዮች የኡለማዎች ውዝግብ አይጠፋቸውም።

2) ውዝግቦች በደረጃ ይለያያሉ፤ ከፊሎቹ ጠንካራ ኺላፎች ሲሆኑ ከፊሎቹ ደግሞ ደካማ ናቸው።

3) ጠንካራ ኺላፍ የሚባለው የኢጅቲሀድ ርእስ ሲሆን ነው። ይህም ማለት የሁሉም አቋም ባለቤቶች ቦታ የሚሰጠው መረጃ ሲኖራቸው ነው። እነዚህን ርዕሶች ለይተው የሚያሳዩትም ለዚህ ብቁ የሆኑ ሙጅተሂዶች ናቸው።

ከፊሎቹ የኺላፍ አይነቶች በመቻቻል የምናልፋቸው የኢጅቲሀድ ውጤቶች ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ መተራረም እና መረጃ የሚደግፈዉን ሐቅ መግለጽ ግድ የሚሆንባቸው ናቸው።

4) ውዝግብ ሲኖር ትክክለኛውን አቋም የሚይዘው አንዱ ብቻ ነው። ነገር ግን ሁሉም ሀቅን ለማወቅ ጥረት የሚያደርጉ ሙጅተሂዶች የተናገሩት ኢልምን መነሻ በማድረግ ነው። የተከተሉትም ኢልምን ነው። ነገር ግን አንዱ ዘንድ ያለው ዕውቀት ሌላኛው ዘንድ ላይኖር ይችላል። እርሱ ያልሰማውን ሰምቶ፤ ያልተረዳውንም ተረድቶ ይሆናል።

5) በእንዲህ አይነቱ የኢጅቲሀድ ጉዳይ ላይ አንድ ሰው ቢቃረን፤ ይህ ሊዋጥልን የሚገባ ኺላፍ ነው!! እንኳን በጥመት ሊፈረጅ ቀርቶ ሊወገዝም አይገባም!!

በነዚህ አምስት ነጥቦች ኢማም አሕመድ የተናገሩትን ንግግር ታላቅነት ትረዳለህ። አንድነትን ከማስረፅና ኺላፍን ከማስወገድ አንፃር «አል ሙኽተለፉ ፊሂ ላ ዩንከር (ብዝሀ ሀሳብ የተነሳበት ጉዳይ አይወገዝም...» ወይም «ላ ኢንካረ ፊ መሳኢሊል ኺላፍ» (በኺላፍ አጀንዳ ትችት የለም) የሚል መርሆ ያቀርባሉ። ይህ መርሆ ገደብ የለሽ ገለጻ በመሆኑ ከዑለማዎች ትችቶችን አስተናግዷል። መርሆው ትክክለኛ ይሆን ዘንድ «ላ ኢንካረ ፊ መሳኢሊ 'ል‑ኢጅቲሃድ» (ሸሪዓዊ ምልከታ በሚለያይባቸው የ'ኢጅቲሀድ' አጀንዳዎች ላይ ውግዘት የለም) በሚል አርመውታል።

**ሌላኛው የግንዛቤ ግድፈት** ኺላፍን ለማስወገድ ሁሉን አቃፊነት እና ለማንኛውም ስህተት ከትችትና እርምት ይልቅ መቻል እና ለስህተቱ እውቅና በመቸር በዝምታ ማለፍ ያስፈልጋል የሚለው ነው። እውነትን መግለፅና ማስተማር አላህ በዑለማዎች ላይ የጣለው ታላቅ አደራ እንደሆነ ይታወቃል። ስለዚህ የተለያዩ አስተሳሰቦችን በተመለከተ አግባቡን በጠበቀ ሂደት ምክክርና መማማር እንጂ ሁሉንም ማቀፍና ስህተቶችን አጽድቆ ማለፍ ተገቢ አይሆንም። በዚህ ረገድ የሚደረጉ ጥሪዎች የኺላፍ አይነቶችን ከግንዛቤ በማስገባት፣ የመቻቻልን እና የመመካከርን ጣምራ ባህል የሚያዳብሩ ሊሆን ይገባል።

አላህ ቁርአን እና ሱናን መሰረት ያደረገ ዕውቀትን እንዲለግሰን፣ ባወቅነው መሥራትን በኺላፍ አጀንዳዎችም ላይ መግባባትን ይለግሰን ዘንድ እንለምነዋለን።

ወልሐምዱ ሊላሂ ረቢልዓለሚን!

___________*********___________

# የዘረኝነት ማጥ

## ከሸይኽ ኢልያስ አሕመዱ የድምጽ ትምህርት ወደ ጽሁፍ የተቀየረ

ዘረኝነት ሰዎችን በዘራቸው ወይም በጎሳቸው ላይ ተመርኩዞ መበደል ወይም የሚገባቸውን መብት መንፈግ እንዲሁም ስለነሱ ትክክለኛ ያልሆነውን ግንዛቤ አሳድሮ ማናናቅና ማጣጣልን የሚያካትት ነው። እንዲሁም ያለ አግባብ ሰዎችን በዘር መለያየት፣ አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ ማድረግም ሌላው የዘረኝነት መገለጫ ነው። ምናልባት አንዳንዶች ላያስተውሉት የሚችሉት አንድ ቁምነገር አለ፤ ይኸውም ዘረኝነት ሰዎችን በዘራቸው ብቻ ማጣጣል ወይም እንደጠላት መፈረጅ ብቻ ሳይሆን የራስን ዘር ያለ አግባብ ከፍ ማድረግ፣ ከሌሎችም የተሻለ እንደሆነ ማመንና ይህንንም መስበክ ከዚህ ከዘረኝነት መገለጫዎች ይመደባል።

ዘረኝነት የተወገዘ እና የተኮነነ እንደሆነ በኢስላም አስተምህሮት የታወቀ ነው። ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችም የዘረኝነትን አስከፊነት ይናገራሉ። ጉዳዩ ከሃይማኖት ማንነት ባሻገር ሰዎች በሰውነታቸው ብቻ የሚጠየፉት ተግባር ነው።

ዘረኝነት ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር አብሮ የሚጠቀስ ነው። ከጥንት ጀምሮ አብሯቸው የኖረ አንድ ጠንቅ ነው። ዘረኝነትን አንዳንድ ክስተቶች በሰዎች መካከል ይበልጥ ያጎላሉ። በአብዛኛው ዘረኝነት በሰዎች ስብእና ውስጥ ታምቆና ተደብቆ ይቆይና በሆኑ ምክንያቶች ሲኮረኮር ፈንድቶ ይወጣል። የሰዎች ስብእና የሚለካውም በእንዲህ አይነት የፈተና ጊዜ በሚያሳዩት አቋም ነው። በጣም የሚደንቀው በዘረኝነት የማይጠረጠሩ አንዳንድ ወንድሞችና እህቶች ነገሮች ሲጋጋሉ እነሱም በዚህ የጥፋት ባህር ውስጥ መዘፈቃቸው ነው። ሙስሊም ከመሆናቸው ጋር ችግሩን በማክሰም ፈንታ በእሳት ላይ ቤንዚን የሚያርከፈክፉ አሉ። አንዳንድ ንግግሮች ወይም ጽሁፎች የሰዎችን ማንነት ያጋልጣሉ ስብእናንም ራቁት ያስቀራሉ።

|"وكائن ترى من صامت لك معجب //
زيادته أو نقصه فى التكلم

لسان الفتى نصف ونصف فؤاده //
فلم يبق إلا صورة اللحم والدم"

|كما يقول زهير بن أبى سلمى |

የአንዳንድ ሰው ዝምታ ሊያስደንቅህ ይችል ይሆናል ነገር ግን እስኪናገር ነው፤ ልክ ሲናገር የሆነ ቃልን ሲወረውር የሰውየው ማንነት ይገለፃል። እናም አድማጩ ዘንድ ያለው ቦታ ወይ ከፍ ወይ ዝቅ ሊል ይችላል።

ዘረኝነት እጅግ የተወገዘ መገለጫ ነው። ሙስሊሞች ዘንድ ሲከሰት ደግሞ ይበልጥ የሚያሳዝንና የሚያስፀይፍ ይሆናል።

|عن الحارث الأشعري رضي الله عنه ان النبي صلى الله عليه وسلم قال من دعا بدعوى الجاهلية فهو من جُثاء جهنّم! قالوا: يا رسول الله وإن صام وصلَّى؟ قال: وإن صام وصلَّى وزعم أنه مسلم

أخرجه الإمام أحمد في مسنده وابن ابي شيبة في مسنفه وحسنه ابن كثير وغيره|

መልዕክተኛችን -ዐለይሂ ሰላቱ ወሰላም-፤ አል ሐሪሥ አልዓሽዓሪ በሚያስተላልፉት ሐዲስ ላይ *"የጃሂሊያ ጥሪን የተጣራ እሱ ከጀሀነም ክምሮች አንዱ ነው" አሉ ሶሐቦችም 'አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ቢፆምም ቢሰግድም?' አሉ የአላህ መልዕክተኛም "አዎ ቢፆምም ቢሰግድም፣ ሙስሊም ነኝ ብሎ ቢሞግት እንኳ" አሉ።*

ምክንያቱም ተግባሩ የሙስሊም አይደለምና። ይህ እንግዲህ የሚያስፈራ ዛቻ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን ይህን ርዕስ አስመልክቶ የተነገሩ ከሀያ በላይ ዘረኝነትን የሚያወግዙ ሐዲሶች አሉ። ሌላው ቀርቶ 'ፊ ሰሒሐይን' (በቡኻሪና ሙስሊም) እንደሰፈረው ጃቢር ኢብን ዓብዲላህ ባስተላለፉት ሐዲስ በአንድ ዘመቻ ላይ ከሙሀጂሮች አንድ ወጣት ሌላ የአንሷር ወጣትን በመምታቱ የተነሳ ሁለቱም የየራሳቸውን ወገን የተጣሩበትና ያነሳሱበትን ሐዲስ እናውቃለን።

**ዘረኝነት ሰዎችን በዘራቸው ብቻ ማጣጣል ወይም እንደጠላት መፈረጅ ብቻ ሳይሆን የራስን ዘር ያለ አግባብ ከፍ ማድረግ፣ ከሌሎችም የተሻለ እንደሆነ ማመንና ይህንንም መስበክ ከዚህ ከዘረኝነት መገለጫዎች ይመደባል**

ይህን የሰሙት መልዕክተኛው –ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም– የተናገሩት ንግግር ብቻውን በቂ ነበር። በሌላ ዘገባ

|أبدعوى الجاهلية وأنا بين أظهركم |

"ይሄን የጃሂሊያ ጥሪ እኔ በናንተ መሀል እያለሁ ትጠራራላችሁ ወይ?" አሉ ... ከዛ መንስኤው ምን እንደሆነ ሲጠይቁ ምን እንደተከሰተ ተነገራቸው ከዛ ...

|دعوها فإنها خبيثة |

ይህችን በጭፍን ወገንተኝነት መጠራራትን ተዋት *"እሷ በጣም ቆሻሻ ናት"* አሉ። በሌላ ዘገባ ላይ

|دعوها فإنها منتنة|

*'ተዋት እሷ ሽታዋ በጣም የከረፋ ነው'* አሉ።

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው 'ሙሐጂር' እና 'አንሷር' የሚለው ስያሜ አላህ -ሱብሐነሁ ወተዓላ- ሙዕሚኖችን ያወደሰበት ከተግባራቸው ጋር የተገናኘ ስያሜ ነው። ሙሐጂሮች ለአላህ ሲሉ፤ ተወልደው ያደጉበትን ሀገር ጥለው ወደ መዲና የተሰደዱ ናቸው። አንሷሮች ደግሞ እነዚህን ሙስሊም ወንድሞቻቸውን በአግባቡ ተቀብለው ያስተናገዱ ለኢስላም ተገቢውን እርዳታ ያደረጉ ናቸው። ነገር ግን እነዚህ የተወደሱ ትክክለኛ ሸሪዓዊ ስያሜዎች ከመሆናቸው ጋር ለጭፍን ወገንተኝነት ሲውሉ መልዕክተኛው—ዓለይሂ ሶላቱ ወሰላም- 'የድሮ የጃሂሊያ ጥሪ' ብለው ሰየሙት። ጭራሽ በብሔር እና በጎሳ ላይ ብቻ ያተኮረ ከሆነ ምን ሊባል እንደሚችል ማሰብ አያዳግትም።

፦ ብዙዎቻችን ስለዘረኝነት ብዙ ከመመከሩና የዘረኝነትን ጠያፍነት የሚያስረዱ ትምህርቶች ከመሰራጨታቸው ጋር ብዙዎች በዘረኝነት ላይ ጉዟቸውን መግፋታቸው አልፎ ተርፎም ዘረኝነታቸው ግልፅ ያልነበረ ሰዎች ዘረኝነት ከአንደበታቸው መሰማቱ፣ በጽሁፋቸው ላይ መንፀባረቁ ሊያስደንቀን ይችላል። ከዚህ ሁሉ ምክርና ተግሳፅ ጋር እንዴት የዘረኝነት አስከፊነት ይሰወርባቸዋል? ብለን ልንገረም እንችላለን።

በርግጥ መልዕክተኛው –ዐለይሂ ሰላቱ ወሰላም– ይህ አስከፊ ጠንቅ በሕዝቦች መካከል የሚቀጥል መሆኑን አስቀድመው ተንብየዋል። በግለሰብ ደረጃ ብዙዎች ከዚህ የጠሩ ቢኖሩም ከሕዝበ ሙስሊሙ መካከል እንዳጠቃላይ የሚጠፋ እንዳልሆነ የጠቆሙበት አንድ የታወቀ ሐዲስ አለ ...

|عن أبي مالك الأشعري، قال: قال رسول الله—— صلى الله عليه وسلم -: "أربع في أمتي من أمر الجاهلية لا يتركونهن: الفخر في الأحساب، والطعن في الأنساب، والاستسقاء بالنجوم، والنياحة..." رواه مسلم وغيره|

*"በኔ ተከታይ ሕዝቦች መካከል ያሉ አራት ነገሮች የጃሂሊያው ስርአት መገለጫዎች ናቸው፤ አይተዋቸውም። በዘር መኩራራት፣ በዘር ማጣጣል ..."*

'አልፈኽሩ ፊል አሕሳብ' በዘር መኩራራት ሲሉ ... በአንድ ሰው የዘር ግንድ ውስጥ በመልካም ተፅእኖው የታወቀና የተከበረ ግለሰብ ይኖራል፤ ነገር ግን የሱ ልጆች ወይም የልጅ ልጆች እኛ እኮ የእከሌ ዝርያዎች ነን ብለው መኩራራታቸው እዚህ ውስጥ ይካተታል። ልብ ሊባል የሚገባው ይህ የታወቀ ሰው ለመታወቅ የበቃው በመልካም ተግባሩ እንጂ እንዲሁ በጎሳው ወይም በብሔሩ አይደለም። ይህ ከመሆኑ ጋር ዝርያዎቹ በዚህ ነገር ሊኩራሩና ራሳቸውን ከሌላው አስበልጠው ሊያዩ አይገባም ነበር። እንኳን እነሱ ይህን መልካም ሥራ የሠራው ሰው ራሱ ሊኮፈስ አይገባውም። ከመልካም ተግባር ጋር መኩራራት የሚከለከል ከሆነ መልካም ተግባር ሳይኖር እንዲሁ በዘር ላይ ተመስርቶ መኩራራት እና ሌላውን ማጣጣል ምን ያህል የተወገዘ ይሆናል? ይህ አንደኛው ነው።

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .

ሁለተኛውን ደግሞ 'ወጦዕኑ ፊል አንሳብ' በዘር ማጣጣል ሲሉ ገለፁት። ይህ ሰዎችን በግለሰብ ደረጃ በዘራቸው ላይ ተመስርቶ ማጣጣል ሊሆን ይችላል። ከዚህ የባሰው ደግሞ በብሔር ደረጃ ወይም በጎሳ/በነገድ ደረጃ ሕዝቦችን ማናናቅ የከፋው ነው። ይህ አይነት የዘረኝነት በሽታ በየጊዜው ብቅ ብቅ እያለ ሰዎችን ማወኩ የማይቀር ነው። ነገር ግን ትልቁ ጥያቄ እኛ ከየትኛው ወገን ነን? ዘረኝነትን እያቀጣጠሉ ከሚያውኩት ወይስ ይህንን እሳት በጥበብ ከሚያከስሙት?

መልዕክተኛው –ዓለይሂ ሶላቱ ወሰላም– ይህ ነገር ወደፊትም እንደሚኖር ከመናገራቸው ጋር ሰዎች ዘንድ ይህ ጠንቅ እንዲኖር ወይም እንዲቀጥል የሚያደርገው ምክንያት ምንድን ነው? ሰዎች ዘረኝነትን እያወገዙ መልሰው ዘረኝነት ውስጥ የሚዘፈቁበት ምክንያት ምንድን ነው?

በዚህ በሽታ የተጠቁ ብዙ ሰዎች ከዚህ ችግራቸው መላቀቅ የሚያቅታቸው ዘረኝነታቸውን ስለማያውቁት ነው። በአብዛኛው ዘረኝነት ውስጥ ገብተናል ብለው አያስቡም። ምናልባት ጥቂቶቹ መገለጫዎቹን ሳያውቁ ቀርተው ይሆናል። ሆኖም ዘረኝነት ብዙዎችን ሲጠናወት እንደ አንድ የባህሪ ግድፈት ሁኖ ነው። ለምሳሌ ቁጡነት ወይም ቶሎ ቦግ ማለትና ነገሮችን ማክረር ወይም መነጫነጭ የሚስተዋልባቸው ብዙ ሰዎች ይህ ባህሪ እንዳለባቸው አይገነዘቡም። አንዳንዴም መቆጣታቸውን ባይክዱ እንኳ የተቆጡበት ምክንያት ትክክለኛ መሆኑን ተናግረው ለማሳመን ይሞክራሉ፤ ሌላኛውን ወገን ጥፋተኛ ያደርጋሉ። እናም ለዚህ ግድፈታቸው ተጠያቂ የሚያደርጉት ያነሳሳቸውን ሰው ነው።

ዘረኝነት የተጠናወታቸው ሰዎች ለምን እንዲህ ያለ ጥፋት ውስጥ እንደገቡ ቢጠየቁ የሚደረድሯቸው ምክንያቶች ይኖራሉ። ነገር ግን ከእንዲህ አይነት ስሜታዊነት ራሳቸውን አግልለው ራሳቸውን ቢፈትሹና የራሳቸው ብሔር ቢጣጣል እንደማይወዱት ሲያስታውሱ ስብእናቸውን እንደገና ሊያጠኑ ይችላሉ።

ዘረኝነትን እንደ አጸፋዊ ምላሽ ማቅረብም እንዲሁ ትልቅ ስህተት ነው። ሰዎች ዘረኛ ሁነው የነርሱን ብሔርና ቋንቋ ሲያንቋሽሹ እነርሱም በምላሹ የእነዛን ብሔርና ቋንቋ ያንቋሽሻሉ ይህ ጥፋትን በጥፋት መመለስ ነው። ስድቡንና ማንቋሸሹን የጀመሩት እነእገሌ ናቸው ማለት ከተጠያቂነት አያድንም። ሰዎችን ዘረኛ ብሎ መወረፍ ራስን ከዘረኝነት አያላቅቅም። አዎን አፀፋ ከሚሰጠው ጥፋተኛ ይልቅ ቅድሚያ የሚለኩሰው ይበልጥ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም የጎሳ ወይም የዘር ጉዳይ በቀላሉ የሚኮረኩርና ወደ ጥፋት የሚመራ ነው።

|وعن عبداللّهِ بنِ عمرو بن العاص رضي اللّه عنهما: أَن رَسُول اللّه ﷺ قَالَ: مِنَ الْكَبائِرِ: شَتْمُ الرَّجلِ والِدَيْهِ، قالوا: يَا رسولَ اللّه، وهَلْ يَشْتُمُ الرَّجُلُ والِدَيْهِ؟! قَالَ: نَعمْ، يَسُبُّ أَبا الرَّجُلِ، فيَسُبّ أَباه، ويَسُبُّ أُمَّهُ، فَيَسُبّ أُمَّهُ متفقٌ عَلَيهِ|

*መልዕክተኛው -ዓለይሂ ሰላቱ ወሰላም- "ከታላላቅ ወንጀሎች መካከል አንዱ ሰውየው ወላጆቹን መሳደቡ ነው" አሉ። ይህን ጊዜ (ሶሐቦች) 'አንድ ሰው ወላጆቹን ይሳደባል እንዴ?' አሉ። ምናሉ አሳቸውም "አዎን፤ የሌላን ሰው አባት ይሳደብና በአፀፋ የሱን አባት ይሰድብበታል። የሌላን ሰው እናት ይሳደብና የሱን እናት ይሰድብበታል" አሉ።*

ስለዚህ የመጀመሪያው ተሳዳቢ ነገሩን ያነሳሳ በመሆኑ በሱ ምክንያት የራሱ ወላጆች በመሰደባቸው ራሱ እንደሰደባቸው ተቆጠረ ማለት ነው። እናም የሌሎችን ጎሳ ወይም ብሔር ቅድሚያ የሚያንቋሽሽ ሰው በዚህ የተነሳ ሌሎቹ የእሱን ብሔር ሲያንቋሽሹ እሱ መነሻ በመሆኑ የራሱን ብሔር እንዳንቋሸሸ ነው የሚቆጠረው።

። የኢስላም አንዱ ትልቁ መርሆ አንዱ በሠራው ወንጀል ሌላው አለመቀጣቱ ነው። አላህ በቁርአኑ ...

{ ولا تزر وازرة وزر أخرى } فاطر 18

***"አንዲት ነፍስ የሌላውን ሀጢያት አትሸከምም" (ፋጢር 18) ይላል።***

**ሰዎች ዘረኛ ሁነው የነርሱን ብሔርና ቋንቋ ሲያንቋሽሹ እነርሱም በምላሹ የእነዛን ብሔርና ቋንቋ ያንቋሽሻሉ ይህ ጥፋትን በጥፋት መመለስ ነው። ስድቡንና ማንቋሸሹን የጀመሩት እነእገሌ ናቸው ማለት ከተጠያቂነት አያድንም።**

ስለዚህ አንዱ ባጠፋው ሌላው አይወቀስም። አንድ ሰው ወይም ጥቂት ግለሰቦች ባጠፉት ጥፋት አንድ ብሔር መወቀስ የለበትም። የተወሰኑ ዘረኞች በሆነ ብሔር ውስጥ ስላሉ ብሔሩ በሙሉ ዘረኛ ተደርጎ መታሰብ የለበትም። አዎን ዘረኞች በአብዛኛዎቹ ወይም በሁሉም ብሔሮችና ነገዶች ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ። ግን ሁሉንም እንደማይወክሉ የታወቀ ነው። አንዱ ስላጠፋ ሌላውን ባጠቃላይ መውቀስ ደግሞ አንዱ የማይምንነት መገለጫ ነው።

እናታችን አዒሻ –ረዲየላሁ ዓንሃ– ከመልዕክተኛው –ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም– በምታስተላልፍልን ሐዲስ ላይ ምን ይላሉ ...

|إِنَّ أَعْظَمَ النَّاسِ فِرْيَةً لَرَجُلٌ هَاجَى رَجُلًا ، فَهَجَا الْقَبِيلَةَ بِأَسْرِهَا..." روىه البخاري في الأدب والبيهقي وابن ماجة وصححه الألباتي|

"ከሰዎች ትልቁ ውሸታም ማለት አንድ ሌላ ሰው እሱን በግጥም ሲያነውረው ለአፀፋ ብሎ የዛኛውን ጎሳ/ብሔር እንዳለ የሚያነውር ነው" አሉ። ከዚህ የባሰው እጅግ አስከፊውና አስነዋሪው ነገር ደግሞ አንዱ በሰራው ወንጀል ሌሎች መገደላቸው ነው። በጭፍን ተነሳስተው ከአንድ ወገን ጥፋት ያጠፋ ወይም ሰው የገደለ ካለ እሱን ለመበቀል ሌሎች ብዙ ንፁሀንን ይገድላሉ። ጃቢር ቢን ዓብዲላህ -ﷺ- በሚያስተላልፉት ሐዲስ

መልዕክተኛችን –ዓለይሂ ሰላቱ ወሰላም- ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት የሐጀተል ወዳዕ ታዋቂ ንግግራቸው ላይ ይህን ርዕስ ትልቅ አፅንኦት ሰጥተውታል።

فَإِنَّ دِمَاءَكُمْ وَأَمْوَالَكُمْ وَأَعْرَاضَكُمْ بَيْنَكُمْ حَرَامٌ كَحُرْمَةِ يَوْمِكُمْ هَذَا، فِي شَهْرِكُمْ هَذَا، فِي بَلَدِكُمْ هَذَا

"ደማችሁ፣ ንብረታችሁና ክብረ-ስብእናችሁ በመካከላችሁ እርም ነው" አንደኛው የሌላውን ደም ሊያፈስ፣ ንብረቱን ሊወስድና ክብሩን ሊያጎድፍ አይገባም ማለት ነው። ይህን ብለው ወዲያው ምን አሉ ...

"|ألا كُلُّ شَيْءٍ من أَمْرِ الْجَاهِلِيَّةِ تَحْتَ قَدَمَيَّ مَوْضُوعٌ، وَدِمَاءُ الْجَاهِلِيَّةِ مَوْضُوعَةٌ، وَإِنَّ أَوَّلَ دَمٍ أَضَعُ من دِمَائِنَا دَمُ ابن رَبِيعَةَ بن الْحَارِثِ كان مُسْتَرْضِعاً في بَنِي سَعْدٍ فَقَتَلَتْهُ هُذَيْلٌ" رواه مسلم وغيره|

"ሁሉም የጃሂሊያ ስርአት በእግሮቼ ስር የተጣለ ነው። በጃሂሊያ የፈሰሰ ደምም ውድቅ ነው" በጃሂሊያ ጊዜ ሰዎች በጭፍን ወገንተኝነት ሲገዳደሉ ነበርና ከአሁን በኋላ ለበቀል እነሳለሁ ብሎ በንፁሀን ላይ እርምጃ መውሰድ ክልክል ነው። ይህ ጥቅል መርሆም በተግባር መዋሉን በምሳሌ ለማሳየት በአንድ ጎሳ የተገደለን ሰው በቀል ውድቅ በማድረግ በሁለት ጎሳዎች መካከል የነበረን ቁርሾና ጠብ እንደተሰረዘ አወጁ።

ስለዚህ እንዲህ ያለ የጅምላ ብቀላ ቀጥተኛ የዘረኝነት መገለጫ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ሰዎች ቢበደሉ እንኳ ዘረኝነት ውስጥ መግባት የለባቸውም፤ ያጠፋ ግለሰብ በነፍስ ወከፍ እሱ ብቻ የሚገባውን ቅጣት በፍርድ ማግኘት ይጠበቅበታል። የመንጋ ፍትህ የሚባል ነገር የለም። መንጋና ፍትህ ሆድና ጀርባ ናቸው። ሁሉም ግለሰብ ራሱን ከዘረኝነት ማጥራት ይጠበቅበታል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ራስን በፍትህ መመርመር ያስፈልጋል።

ዘረኛ የሚባለው ሰው ስለገደለ ወይም በግልፅ ስለተሳደበ ብቻ አይደለም። ይህን ከሚያደርጉ ጋራ አብሮ መሰለፍም አንድ የዘረኝነት መገለጫ ነው። መልዕክተኛችን –ዓለይሂ ሶላቱ ወሰላም- ...

| جندب بن عبد الله البجلي ان النبي صلى الله عليه وسلم قال "من قتل تحت راية عمية ، يدعو عصبية أو ينصر عصبية ، فقتلته جاهلية " أخرجه مسلم وغيره|

*"በጭፍን ወገንተኝነት ሰንደቅ /አመራር ስር/ ሆኖ የተዋጋ፣ ወደ ጭፍን ወገንተኝነት ዘረኝነት የሚጣራ፣ ጭፍን ወገንተኝነትን የሚረዳ አሟሟቱ የጃሂሊያ አሟሟት ነው"* አሉ። እንግዲህ ትልቁ ነገር አሟሟት ነው አፈፃፀሙ አላመረም ማለት ነው።

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞርለ . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . . .

በሌላ አቡ ሁረይራ - رضي الله عنه - ባወሩት ትክክለኛም ሐዲሡ ላይ መልዕክተኛው –ዓለሂ ሰላቱ ወሰላም-

|"من قتل تحت راية عمية يغضب لعصبة ..."|

በዘር የተነሳ ለዘሩ ሲል ብቻ የሚቆጣ ለሌላው ምንም ደንታ የለሽ ሁኖ የራሱ ዘር ብቻ ቱግ የሚያደርገው እናም በዚህ ላይ የሚጋደል ይህ ከኔ ኡማ/ሕዝብ ውስጥ አይካተትም። ማለትም ተግባሩ የሙስሊሞች ተግባር አይደለምና የኔ እውነተኛ ተከታይ አይደለም ማለት ነው። ምንም እንኳ በዚህ ተግባሩ ብቻ ከኢስላም ላይወጣ ቢችልም ማለት ነው። ስለዚህ በተቻለ መጠን ራሳችንን ከዘረኝነት በከፊል ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ መላቀቅ ይኖርብናል።

፨ በጥቅሉ የዘረኝነትን አስከፊነት ለመረዳት ይህ ሁሉ ምክር አስፈላጊ አልነበረም። ሌላው ቀርቶ በጎረቤት ሀገሮች ዘረኝነት ያስከተለውን አስከፊ ውጤት መመልከቱ በቂ ነው። አንዳንድ ሀገራት ሕዝባቸው በቋንቋ፣ በሃይማኖት ራሱ አንድ ከመሆኑ ጋር በዘረኝነት/ጎሰኝነት የተነሳ ተበጣብጠው ሀገራቸውን ሙሉ በሙሉ አጥተዋል። በየ ሀገራቱ ተሰደዋል። እናም የዘረኝነት ጉዳይ በተለያዩ ማህበራዊ ሚድያዎች በመሰዳደብ ብቻ የሚገደብ እንዳይመስለን። በትክክል ምድር ላይ ወርዶ ታላቅ ጦስ ሊያስከትል ይችላል። ከእንዲህ ያለ ጣጣ ራሳችንን ለመታደግ በርካታ እሳቤዎችና ምክክሮች ያስፈልጋሉ።

ምናልባት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ወደ ዘረኝነት የሚገፉፉ ስርአቶች፣ ህጎችና ልማዶች ካሉ እነዚህን በድጋሚ ማጤንና በምክክር በድጋሚ ማሻሻል ያስፈልጋል። እንዲሁም ተሰሚነት ያላቸው ሰዎች ከላይ እንደተጠቀሰው ችግሮችን የሚያባብሱ ሳይሆኑ የሚቀርፉ አስተያየቶችንና ምክሮችን ሊለግሱ ይገባቸዋል። ይህንን አስከፊ መዘዝ ለማጥፋት የተቻላቸውን አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይገባል።

በርግጥ ብዙ ሰዎች ለሌሎች ጠቃሚ ምክሮችን ሲያስተላልፉ የዘረኝነትን ጥፋትና ክፋት ለሰዎች ሲያስተምሩ ይታያል። ይህ በጣም የሚያስመሰግን ተግባር ነው። ነገር ግን ለየት ባለ መልኩ በየጎሳው በየብሔሩ ያሉ አዋቂዎች ለጎሳ አባሎቻቸው ስለዘረኝነት ክፋት በየቋንቋቸው ቢያስተምሩ ውጤቱ የበረታ ይሆናል። ቅርበት ያላቸው ሰዎች የሚሰጡት ምክር ይበልጥ ተሰሚነት ይኖረዋል። ይህ ደግሞ በመሀከላቸው ያለውን ወንድማማችነት የሚያጠናክር እንጂ የሚያላላ አይሆንም። ምክንያቱም ወዳጅ ለወዳጁ እንደመስታወት ነውና ችግሩን ነግሮ እንዲላቀቅ ይረዳዋል። ያ ካልሆነ ግን በጥንቱ የማይምነት ማህበረሰብ የነበረው ጭፍን ወገንተኝነት ከመካከላችን ሊሰፍን ይችላል። ሰዎች የራሳችን ዘር ስለሆኑ ብቻ ሲያጠፉ እያየናቸው ዝም የምንላቸው ከሆነ፣ ወደ ዘረኝነት ሲያመሩ እጃቸውን ይዘን የማንመክራቸው ከሆነ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከተጠያቂነት አንድንም። ለዚህ ነው መልዕክተኛው – ዓለይሂ ሰላቱ ወሰላም– በሚታወቀው የአነስ ኢብን ማሊክ – رضي الله عنه —ሐዲሥ ላይ ...

|عن أنس رضي الله عنه، قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: »انصر أخاك ظالـمًا، أو مَظْلومًا«، فقال رجل: "يا رسول الله، أنصره إذا كان مَظْلومًا، أفرأيت إذا كان ظالـمًا، كيف أنصره؟" قال: تَحْجُزُه، أو تمنعه من الظُّلم، فإنَّ ذلك نَصْره «رواه البخاري|

"ወንድምህን እየበደለም እየተበደለም እርዳው" አሉ ይህን ጊዜ አንድ ሶሐቢይ 'የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ከተበደለ እረዳዋለሁ ነገር ግን እሱ እየበደለ እንዴት ነው የምረዳው?' ሲላቸው እሳቸውም "ታቅበዋለህ፤ ከበደል ትከለክለዋለህ። ይህ ነው እርሱን መርዳት ማለት" አሉ።

አንድን ሰው መርዳት ማለት ከበደልና ከጥፋት እንዲቆጠብ ማገዝንም ያካትታል። በዚህ መሰረት አንድ ሰው ለጎሳው የሚሳሳና የሚጨነቅ ከሆነ ለጎሳ ወይም ለብሔር ወንድሞቹ ከሚያበረክተው በርካታ አስተዋፅኦዎች መካከል አንዱ እነርሱ ያለአግባብ ሌሎችን ሲበድሉ ወይም ራሳቸውን ከፍ አርገው ሌሎችን ሲንቁ ከዚህ ተግባር እንዲቆጠቡ መምከር ከዘረኝነት እንዲፀዱ ማስተማር ነው።

> **ሰዎች የራሳቸን ዘር ስለሆኑ ብቻ ሲያጠፉ እያየናቸው ዝም የምንላቸው ከሆነ፣ ወደ ዘረኝነት ሲያመሩ እጃቸውን ይዘን የማንመክራቸው ከሆነ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከተጠያቂነት አንድንም ።**

ስለዚህ ሁሉም ሰው ቆም ብሎ ራሱን ሊፈትሽ ይገባል። በተቻለው አቅም ይህንን ዘረኝነትን ከሚያጧጡፉ ሰዎች ራቅ ብሎ በነፃ አዕምሮው ለማሰብ ቢሞክር ወደ እውነታው ሊመራ ይችላል። ብዙ ሰዎች ከሌሎች ጋር በመሆናቸው ብቻ በነዛ ተፅእኖ ስር ይወድቃሉና። በጥቅሉ ዘረኝነትን ከሰዎች ልቦና መፋቅና ማጥፋት ባይቻል እንኳ ቢያንስ ውጤቱን መቀነስ ይቻላል።

አላህ (ሱብሐነሁ ወተዓላ) ስብእናችንን ከየትኛውም አይነት የባህሪ ግድፈት እንዲያጠራልን እና ፍትህንና እውነተኝነትን እንዲያላብሰን ልንማፀነው ይገባል። ]]]

***መፍቻ***

[[[ ]]] ... የሸይኽ ኢልያስ ንግግር መነሻና ማብቂያ

{ } .... የቁርአን አንቀጽ በዐረበኛ

| | .... ዓረብኛ ቃል በዓረበኛ ሲፃፍ

( ) ..... ወደ ፅሁፍ የገለበጠው ሰው ጭማሪ

-----------*********------------

# ከሙሽሪኮች ጋር መተባበር?

👌 ከሌሎች ጋር የሚኖረን የጋራ መተባበር የሚወሰነው በሸሪአዊ ሚዛን ነው። አላህ (ሱብሀነሁ ወተዓላ) ምዕመናን በመልካም ተግባር እና አላህን በመፍራት ላይ እንዲተባበሩ አዟል።

 አላህ እንዲህ ይላል፤

{وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَى وَلَا تَعَاوَنُوا عَلَى الْإِثْمِ وَالْعُدْوَانِ} سورة المائدة ٢

***«በበጎ ሥራና ወንጀልን በመጠንቀቅ ላይ ተረዳዱ፤ በኃጢአትና ወሰንን በመጣስ ላይ አትተባበሩ!»***

[አል-ማኢዳህ ፡ 2]

√ ቢድዓ ላይ ካሉ ሰዎች ጋር ኢስላምን በሚጠቅም ተግባር ላይ መተባበር እንደሚያስፈልግም አያጠያይቅም። ምናልባት በዚህ ምክኒያት የሚከሰቱ መጥፎ ውጤቶች (መፋሲዶች) ካሉ፤ እነርሱን ማስቀረት የሚቻልበትን መንገድ ማጤን እና ትክክለኛውን አቅጣጫ መያዝ ያስፈልጋል።

√ ግልፅ ከሆኑ ዲናዊ መረጃዎች እንደምንረዳው ፍትህንና ልማትን በሚያፋጥኑ ጉዳዮች ላይ ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች ጋር ጭምር መተባበሩ አስፈላጊ ነው።

☞ አል-ኢማም ኢብኑ'ል-ቀይ-ዩም "ሑደይቢያህ" ስምምነት ላይ ካለፉ ክስተቶች የሚቀሰሙ ቁም-ነገሮችን ሲዘረዝሩ የተናገሩት በወንድም ኢልያስ አሕመድ እንዲህ ተተርጉሟል፡- «አጋሪያን፣ የቢድዓህ ባለቤቶች፣ ጋጠ-ወጦች፣ ወሰን አላፊ አማጺያንና በደለኞች ከተከበሩት የአላህ ድንጋጌዎች አንዱን ለሚያልቁበት ጉዳይ እርዳታን በጠየቁ ጊዜ (አዎንታዊ) ምላሽ ይለገሳሉ፤ የጠየቁትም ይሰጣቸዋል፤ በዚያም ላይ እገዛ ይደረግላቸዋል፤ ምንም እንኳ ሌላን ነገር ቢከለከሉም! እናም ክህደታቸው ወይም ድንበር ማለፋቸው ላይ ሳይሆን የአላህ ድንጋጌዎችን በሚያልቁባቸው ጉዳዮች ላይ ይታገዛሉ፤ ከዚያ ወዲያ ያለውን ደግሞ ይነፈጋሉ! አላህ ዘንድ ተወዳጅ የሆነና እርሱን የሚያስደስት ነገር ላይ እገዛን የፈለገ ማንኛውም ሰው ማንም ይሁን ማን በዚህ ተወዳጅ ተግባር ላይ በሚደረግለት ትብብር የተነሳ ከዚያ የበለጠ የተጠላ ውጤት እስካልተከተለ ድረስ አዎንታዊ ምላሽ ይሰጠዋልና። ይህም እጅግ ረቂቅና ለነፍስም ከሁሉ በላይ ከባድና (ለመቀበል) አስቸጋሪ ከሚሆኑት ሁኔታዎች ይመደባል..!» ["ዛዱ'ል-መዓድ" (3/303)]

ይህንን ቁርአናዊ አካሄድ "መንሀጅ" በሀሳብ ደረጃ ብዙዎች ቢቀበሉትም በተግባር የሚሠሩበት ግን ጥቂቶች ናቸው።

አላህ ሆይ! ውዴታን ካንተ ብቻ ከሚከጅሉ ባሮችህ አድርገን! ከመሳሳት እና ከማሳሳትም ባንተ እጠበቃለሁ!

قال الإمام ابن القيم

وَمِنْهَا: أَنَّ الْمُشْرِكِينَ وَأَهْلَ الْبِدَعِ وَالْفُجُورِ وَالْبُغَاةَ وَالظَّلَمَةَ إِذَا طَلَبُوا أَمْرًا يُعَظِّمُونَ فِيهِ حُرْمَةً مِنْ حُرُمَاتِ اللَّهِ تَعَالَى، أُجِيبُوا إِلَيْهِ وَأُعْطُوهُ وَأُعِينُوا عَلَيْهِ، وَإِنْ مُنِعُوا غَيْرَهُ؛ فَيُعَاوَنُونَ عَلَى مَا فِيهِ تَعْظِيمُ حُرُمَاتِ اللَّهِ تَعَالَى، لَا عَلَى كُفْرِهِمْ وَبَغْيِهِمْ، وَيُمْنَعُونَ مِمَّا سِوَى ذَلِكَ؛ فَكُلُّ مَنِ الْتَمَسَ الْمُعَاوَنَةَ, مَحْبُوبٍ لِلَّهِ تَعَالَى مُرْضٍ لَهُ، أُجِيبَ إِلَى ذَلِكَ كَائِنًا مَنْ كَانَ، مَا لَمْ يَتَرَتَّبْ عَلَى إِعَانَتِهِ عَلَى ذَلِكَ الْمَحْبُوبِ مَبْغُوضٌ لِلَّهِ أَعْظَمُ مِنْهُ، وَهَذَا مِنْ أَدَقِّ الْمَوَاضِعِ وَأَصْعَبِهَا وَأَشَقِّهَا عَلَى النُّفُوسِ

[(زاد المعاد" (3/303"]

-----------*********------------

# የኮንዶሚኒየም ቤትን በረጅም ጊዜ ክፍያ መግዛት በሸሪዓ አይታ

✍ በሸይኽ ኢልያስ አሕመድ

ለኮንዶሚኒየም ቤቶች ግዢ አፈፃፀም የሚሰጠውን ኢስላማዊ ብይን የተመለከቱ ብዙ ጥያቄዎች መነሳታቸው የተለመደ ነው። እንደሚታወቀው ስለአንድ ነገር የሚኖረን ድምዳሜ ስለ ምንነቱ ያለን ምልከታ ላይ የሚገነባ በመሆኑ ይዘቱን መገንዘብ የመጀመሪያው እርምጃ መሆን ይኖርበታል።

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የ40/60 የቁጠባ መኖሪያ ቤቶች ልማት ፕሮግራምን አስመልክቶ በ2005 ዓመተ ልደት ያወጣውን የቤት ፈላጊዎች የምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኮንደሚኒየም አፓርትመንት ከአዲስ አበባ አስተዳደር ቤቶች ኤጀንሲ "በግዢ ከተላለፈላቸው ግለሰቦች ጋር" የሚያደርገውን "የብድር ውል ስምምነት" ናሙና ማንበብ በብዙዎች የሚፈፀመውን ክፍያ ተጨባጭ ይዘት (التكييف الفقهي) ለመረዳት የሚያግዙ በርካታ ጭብጦችን ያስገኛል። ሸሪዓዊው ብይን የሚወሰንባቸውን ጥቂቱን እንመልከት:-

1– የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቁጠባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ ከባንክ ተበድሮ ለሚገነባው የኮንዶሚኒየም ቤቶች ሽያጭ ባንኩ ኢንተርፕራይዙን ወክሎ ደንበኞችን ይመዘግባል፤ የሽያጩ ውልና ርክክብንም ያደርጋል። ሆኖም ቤቶቹን በባለቤትነት ለደንበኞች የሚሸጠው ኢንተርፕራይዝ/ኤጀንሲው እንጂ ባንኩ አይደለም።

በምዝገባ አፈጻጸም መመሪያው ክፍል 4 አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 4 ላይ "ግንባታው ሲጠናቀቅ ባንኩ በውሉ መሰረት ቤቶችን ይረከባል፣ ኢንተርፕራይዙም ያስረክባል" የሚለው በመስሪያ ቤቶቹ መካከል የሚኖረውን የኃላፊነት ድርሻን ለመለየት የተነገረ እንደሆነ ለማሳየት በክፍል 5 የተዘረዘሩትን አንቀፆች በተለይ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 9 እና 10 ላይ የሰፈረው ግልፅ ማብራሪያ ሆኖ መቅረብ ይችላል።

2- በአንድ ጊዜ መክፈል ላልቻሉ ደንበኞች ባንኩ ቀሪውን (60% ወይም 80% ወይም 90%) ይከፍልላቸዋል።

በዚህም መሰረት ባንኩ ቤት ገዢዎችን እያበደረ እንጂ እየሸጠላቸው አይደለም፤ ምክንያቱም መኖሪያ ቤቱ በባንኩ የባለቤትነት ይዞታ ስር ያልገባ ነውና።

በተጨማሪም በደንበኛውና በባንኩ መካከል ያለው ውል የብድር ውል ስለመሆኑ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የቤት ፈላጊዎች የምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 1 አንቀፅ 7፣ እንዲሁም ክፍል 5 አንቀፅ 14 ላይ በግልፅ ሰፍሯል። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አፓርትመንቱ "በግዢ ከተላለፈላቸው ግለሰቦች ጋር" የሚያደርገውን የውል ሰነድም "የብድር ውል ስምምነት" ሲል ይጠራዋል፡፡ ብሎም በክፍል አንድ አንቀፅ 1 ላይ እንዲህ ይላል:- "ባንኩ ተበዳሪው ያቀረቡትን የብድር ጥያቄ መሰረት በማድረግ ብር ........... ያበደረ ሲሆን ባንኩ እንደተበዳሪው ሆኖ የብድሩን ገንዘብ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ቤቶች ኤጀንሲ ይከፍላል።"

ስለሆነም ባንኩ ለኤጀንሲው የሚከፈለውን ሙሉ የቤት ዋጋ ለገዢው ያበድራል ማለት ነው።

3- ከዚያም ባንኩ ብድሩ ላይ የተለመደውን የወለድ ፐርሰንት ጨምሮ በማስላት ደንበኛውን በረጅም ጊዜ ክፍያ ያስከፍላል። ክፍያው እስኪጠናቀቅም የቤቱን ካርታ እንደዋስትና ይዞ ይቆያል።

ከዚህ እንደምንገነዘበው ደንበኛው በአንድ ጊዜ ክፍያም ይሁን በረጅም ጊዜ ክፍያ ዋጋውን ለመክፈል ቢስማማ ከከተማው አስተዳደር ኤጀንሲ ጋር የሚፈፀመው የሽያጭ ውል በአንድ ጊዜ ተፈፃሚ የሚጠናቀቅና የተገደበ ዋጋ ያለው ነው። ሆኖም በአንድ ጊዜ መክፈል ላልቻሉ ደንበኞች ቅድሚያ በቁጠባ ሂሳብ ካጠራቀሙት ውጭ ያለውን ቀሪ ክፍያ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በብድር መልኩ ለኤጀንሲው ይከፍልላቸውና ብድሩን በረጅም ጊዜ ከነወለዱ ያስከፍላቸዋል።

ስለሆነም የኮንዶሚኒየም ቤትን "በረጅም ጊዜ ክፍያ" የመግዛት እውነተኛ ገፅታ ከባንክ በወለድ ተበድሮ መክፈል እንጂ ሌላ አይደለም። ይህ በበርካታ አገራት የተለመደ አሰራር ነው።

> **ስለሆነም የኮንዶሚኒየም ቤትን "በረጅም ጊዜ ክፍያ" የመግዛት እውነተኛ ገፅታ ከባንክ በወለድ ተበድሮ መክፈል እንጂ ሌላ አይደለም። ይህ በበርካታ አገራት የተለመደ አሰራር ነው።**

## ሸሪዓዊ ፍርዱ

የተወሰነ መጠን ንብረትን በብድር ለሌሎች የሚያስተላልፍ አካል አምሳያውን መጠን ብቻ በመቀበል ፈንታ ማንኛውንም አይነት ጭማሪ ለማስከፈል በግልፅም ይሁን በውስጠ ታዋቂነት መስማማቱ በቁርኣን በጥብቅ የተኮነነው የጃሂሊያው አራጣ ውስጥ እንደሚገባ ምንም አይነት ውዝግብ የለም(1)

ወለድ የተከለከለ መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን መዘርዘር የዚህ አጭር ፅሑፍ አላማ አይደለም። ሆኖም በሸሪዓችን ለጉዳዩ የተሰጠው አፅእኖት እጅግ ከባድ ከመሆኑ አንፃር የተለያዩ ቁርኣናዊና ሐዲሣዊ አስረጆች ወለድን ከአጥፊ ሀጢያቶች መቁጠራቸው፤ ሌሎች ወንጀሎች ላይ ያልተጠቀሱ አስፈሪ ዛቻዎችን መግለፃቸው፤ ወለድን ብቻ ሳይሆን ወደርሱ በተዘዋዋሪ የሚያመሩ መንገዶችን መዝጋታቸው እሙን ነው።

ክልከላው የሚመለከተው ወለድን መብላትን / መውሰድን/ ብቻ ሳይሆን ማብላቱንም / መስጠትንም/ እንደሆነም ሊዘነጋ አይገባም።

عَنْ جَابِرٍ، قَالَ: »لَعَنَ رَسُولُ اللهِ -صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ- آكِلَ الرِّبَا، وَمُؤْكِلَهُ، وَكَاتِبَهُ، وَشَاهِدَيْهِ«، وَقَالَ: »هُمْ سَوَاءٌ« أخرجه مسلم.

ጃቢር እንደሚያስተላልፉት:- የአላህ መልዕክተኛ ወለድ የሚበላን፣ የሚያበላን፣ ውሉን የሚፅፈውንና መስካሪዎቹን ረግመዋል፤ እንዲሁም "ሁሉም እኩል ናቸው" ብለዋል። ሙስሊም ዘግበውታል።(2)

## ዶሩራ (ضرورة) እና ወለድ

በሸሪዓችን አስገዳጅ የችግር ሁኔታ (ضرورة) ሲኖር የተከለከሉ ተግባራት ይፈቀዱ የለ ወይ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም።

በርግጥ ይህ በጥቅሉ ትክክለኛ መርሆ ነው። ሆኖም ወለድ እጅግ የገዘፈ ሀጢያት ከመሆኑ አንፃር ሊፈቀድ የሚቻልበት አስገዳጅ የችግር ሁኔታ (ضرورة) ጭራሽ ስለመኖሩ ዑለማዎች ተወዛግበዋል።

አንዳንዶች የመረጡት የሚከተለውን ዝርዝር ነው:-

በወለድ ማበደር የሚፈቀድበት አስገዳጅ ሁኔታ ሊኖር አይችልም፤ ምክንያቱም የሚያበድረውን ገንዘብ ራሱ መጠቀም ይችላልና።

በወለድ መበደር እንደ ማበደር በጥብቅ የተከለከለ ቢሆንም በአንዳንድ አስገዳጅ የችግር ሁኔታዎች ሊፈቀድ ይችላል።(3) ሆኖም አፈፃፀሙ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይሻል። እርምነታቸው የፀና ወንጀሎች የክልከላ ገደባቸው የሚነሳው የተፈቀደ አማራጭ በማይኖርበት የዶሩራ ቅድመ ሁኔታ እንጂ ድርጊቱን መፈፀሙ አስፈላጊ (حاجة) ስለሆነ ብቻ አይደለም።

## የዶሩራ እና የሓጃ ልዩነት(4)

ዶሩራ (ضرورة) የሚባለው ክልከላውን ለመፈፀም የሚያስገድድ አጣብቂኝ ሲሆን ገደቡም ይህን ካላደረገ በእርግጠኝነት ወይም ተጨባጭነት ባለው አመዛኝ ግምት ህይወት የሚጠፋ፣ አካል የሚጎድል፣ አእምሮ የሚነካ ወይም የአልጋ ቁራኛ የሚያደርግ በሽታ አሊያም አግባብ የሌለው የረጅም ጊዜ እስር የሚከተል፣ ክብረ ስብእና በዝሙትና በመሰል አፀያፊ ተግባራት የሚጎድፍ፣ ከፍተኛ ንብረት የሚጠፋ ወይም መሰል ጉዳት የሚከተል መሆኑ ነው።(5) ሓጃ (حاجة) ግን ተግባሩን ካልፈፀሙት ችግር ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፤ ሆኖም ሊሸከሙት የሚችሉት አይነት ችግር ነው እንጂ የዶሩራ እርከን ላይ የደረሰ አይደለም።(6)

ታዲያ በአፅእኖት የተከለከሉ ከባባድ ወንጀሎችን መፈፀም የሚፈቀደው ድርጊቱ ከላይ እንደተጠቀሰው በህይወት ላይ የተጋረጠን አደጋ ለማስቀረት ብቸኛ አማራጭ በሚሆንበት ጠባብ የዶሩራ አጋጣሚዎች (ضرورة خاصة) ላይ ብቻ ነው።(7)

ወደ ቀጣይ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .

ወለድም በዶሩራ ህግ ረገድ ልክ እንደበከተ ስጋ እና መሰል ክልክላዎች ነው፤ በህይወት ላይ የተጋረጠን አደጋ ለማስቀረት እንጂ አይፈቀድም(8)

በዚህ መሰረት በኪራይ ወይም በሌሎች አማራጮች መጠለያ ማግኘት ለሚችል ሰው የቤት ባለቤት የመሆን አስፈላጊነት አስገዳጅ የሆነው የዶሩራ ክልል ውስጥ አይገባም።(9) የኪራዩ ወርሃዊ ወጪ ከኮንዶሚኒየም ውል ወርሃዊ ወጪ የበዛ ቢሆን እንኳ ተቸግሮም ቢሆን በሐላል መከራየት እየቻሉ እርግማን በሚያስከትለው የወለድ ስምምነት ውስጥ እጅን ማስገባት የሚፈቀድ ሊሆን አይችልም።

በርግጥ ሙስሊሞች አናሳ በሆኑባቸው የምእራብ አገራት በአንድ ጊዜ ክፍያ ቤት መግዛት የማይችሉ ሙስሊሞች ከኪራይ ጣጣና ከሌሎች ማህበራዊ ተፅእኖዎች ለመውጣት ከባንክ በወለድ ብድር ቤት መግዛታቸውን ከዶሩራ አንፃር ያግራሩ ፈትዋዎች ተገኝተዋል። ሆኖም እነኚህ ፈትዋዎች የተመረኮዙባቸው መሰረቶች ሲገመገሙ ከፊሎቹ በብዙኃኑ ሊቃውንት የተተቹ "መረጃዎችን" እና ባይተዋር ምርጫዎችን ያማከሉ ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ ተጨባጩን ሁኔታ የማይገጥሙ የስህተት ኢጅቲሃድ ውጤቶች እንደሆኑ በብዙ ሂሶች ተብራርቷል።(10)

አንዱና ዋነኛ ምርኩዛቸው "ሓጃ በዶሩራ ደረጃ ላይ ይቀመጣል" የሚለው የፊቅህ መርሆ ነው። መርሆው በመሰረቱ ልቅ በሆነ መልኩ ተፈፃሚ ስለመሆኑ ውዝግብ ያለ ከመሆኑ ጋር በዚህ ንዑስ ጉዳይ ላይ ይህን መደገፊያ ማድረግ መስፈርቱን ያላሟላ ዕይታ ነው። ምክንያቱም የሓጃው (የአስፈላጊነቱ) ደረጃ ሁሉም ላይ ተጋርጦ እንደደረባ ያለን አጥፊ ወንጀል የሚያስፈቅድበት እርከን ላይ የደረሰ ባለመሆኑና በርሱ ውስጥ ከመነከር የሚያብቃቁ አማራጮች በመኖራቸው ነው(11)

አዎን! ምናልባት በአንዳንድ መሰናከሎች የተነሳ መከራየት የማይችል ወይም ከአቅሙ በላይ የሆነ ሙስሊም ቢገኝና በረጅም ጊዜ የወለድ ክፍያ ከመግዛት ውጪ ያለው ብቸኛ አማራጭ መጠለያ አጥቶ ወደ ጎዳና መውጣት ከሆነ ይህ አይነቱ ያለበት አስገዳጅ ሁኔታ እንደ ዶሩራ ሊታይ ይችላል። ሆኖም በትክክል የዶሩራ እርከን ላይ መድረሱን ለማረጋገጥ ታማኝ ዓሊሞችን መጠየቅ ይኖርበታል።(12)

**እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ይነሳል:-**

በወለድ በተበደረው ገንዘብ ቤት ወይም ሌላ ንብረት ገዝቶ ያለ ሰው ጥፋቱን ለማካካስ ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?

**መልሱ:-** የመጀመሪያው እርምጃ መስፈርቱን ያሟላ ተውበት ማድረግ ነው። ታዲያ ተውበቱ ትክክል እንዲሆን በወለድ ብድር የገዛቸው ንብረቶችን ከይዞታው ማውጣት ግዴታ ይሆናል? ለሚለው ጥያቄ ብዙ ዑለማዎች ያላቸው ምላሽ እንደሚከተለው ነው:-

"የወለድ ብድር" ሲባል ተበዳሪው የተበደረው ገንዘብ ራሱ ወለድ ነው ማለት አይደለም። ወለዱ ለአበዳሪው ወደፊት የሚከፍለው ጭማሪ ነው። ስለሆነም ቤቱ በቀጥታ በወለድ ገንዘብ የተገዛ አይደለም ማለት ነው። አዎን! አንድ አራጣ አበዳሪ በሚያገኘው "ትርፍ" የሚገነባው ቤት ወይም የሚሸምተው እቃ በወለድ ገንዘብ የተሰራ ወይም የተገዛ መሆኑን እንስማማለን። ተበዳሪ የሚገዛው ቤት ግን በራሱ የሐራም ንብረት እንደሆነ አይታሰብምና ቤቱን በመሸጥም ይሁን በሌላ ሂደት መልቀቁ ግዴታ አይሆንም።

እዳውን ከነወለዱ ከፍሎ ያልጨረሰ እንደሆነ የወለዱን ጭማሪ ሳያክል የተበደረውን መጠን ብቻ ለመክፈል አበዳሪውን ማግባባት ከቻለ ይህንን ማድረጉ ግዴታ ይሆናል። አላህ እንዲህ ብሏል:-

وَإِن تُبۡتُمۡ فَلَكُمۡ رُءُوسُ أَمۡوَٰلِكُمۡ لَا تَظۡلِمُونَ وَلَا تُظۡلَمُونَ

{በፀፀት ከተመለሳችሁም ለናንተ ዋናው ገንዘባችሁ አላላቸሁ፤ አትበድሉም አትበደሉምም።}

አበዳሪው ክፍያውን ያለወለዱ ለመቀበል የተቀረውን ሙሉ ክፍያ በአንድ ጊዜ እንዲከፍለው ቢጠይቅ ሌላ የሐላል ብድር ተበድሮ አሊያም የተወሰነ ንብረቱን ሽጦም ቢሆን ክፍያውን አጠናቅቆ ከወለድ ጣጣ መውጣት ይገባዋል።

ይህንን ማድረግ ሳይችል ቢቀር ወይም የወለዱን ጭማሪ ባለመክፈሉ ለእስር ወይም ለንብረት መወረስና ለመሰል ችግሮች የሚጋለጥ ከሆነ ያለበትን እዳ ከነጭማሪው መክፈሉ ከላይ ባሳለፍነው የዶሩራ ህግ መሰረት በይቅርታ የሚታለፍ ይሆናል።

والله أعلم بالصواب

## የመፍትሄ ጥቆማ

1/ ኤጀንሲው ዋጋውን በጥቂቱ ከፍ አድርጎ ለደንበኞች ያለ አማካይ በተገደበና በማይጨምር የረጅም ጊዜ ክፍያ ( التقسيط) ቤቱን መሸጥ ይችላል።

አሊያም ባንኩ ወይም ሌላ ድርጅት ቤቱን በግዢ በይዞታው ስር አስገብቶ ባለቤት ከሆነ በኋላ ለደንበኛው በተገደበና በማይጨምር የረጅም ጊዜ ክፍያ (installment) አትርፎ መሸጥ ይችላል።

እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን ማስተዋል የግድ ነው:-

**አንደኛ:-** ይህን የረጅም ጊዜ ክፍያን በተገደበው ጊዜ መክፈል ያልቻለ ግለሰብ በምንም መልኩ የወለድ ጭማሪ ሊጫንበት አይገባም። አለበለዚያ እስካሁን የጋገርነው ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆነ ማለት ነው!

> **ወለድም በዶሩራ ህግ ረገድ ልክ እንደበከተ ስጋ እና መሰል ክልክላዎች ነው፤ በህይወት ላይ የተጋረጠን አደጋ ለማስቀረት እንጂ አይፈቀድም።**

**ሁለተኛ:-** ባንኩ ለክፍያው ማስተማመኛ የሚሆኑ ሌሎች የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላል። ከነዚህ አንዱ የዋስትና ንብረት (رهن) መያዝ ሲሆን የሚሸጠውን እቃ (ቤቱንም) ራሱ እንደ መያዣ ማድረግን የፈቀዱ ሊቃውንት አሉ። ሆኖም ደንበኛው መክፈል እንዳቃተው ከተረጋገጠ መያዣው ተሸጦ የተቀረው እዳ ከተከፈለ በኋላ ቀሪው ሊመለስለት ይገባል እንጂ ባንኩም ይሁን ሌላ አካል የመያዣውን ሙሉ ዋጋውን የመውሰድ መብት የለውም።

2/ ሽያጩ በሙራበሓ (مرابحة) መልኩም ሊፈፀም ይችላል። ይህም ማለት ቤት መግዛት የሚፈልግ ግለሰብ ሙሉ ዋጋውን መክፈል ስለማይችል ባንኩ ወይም ድርጅቱ ግለሰቡ የሚፈልገውን ቤት (ወይም ሌላ እቃ) እንዲገዛውና በረጅም ጊዜ ክፍያ አትርፎ እንዲሸጥለት በውል ደረጃ ሳይሆን በቃል ኪዳን ደረጃ ይስማማሉ። የሽያጭ ውሉ ባንኩ ቤቱን (እቃውን) ገዝቶ በይዞታው ስር ካሳደረው በኋላ የሚፈፀም መሆን አለበት፤ በይዞታ ስር ያልገባን ውስን ነገር መሸጥ ክልክል ነውና።

እዚህ ላይ ለመግዛት ቃል የገባን ደንበኛ ቃሉን እንዲያከብር የሚያስገድድ እንደ ቀብድ ያለ መስፈርት ወይም ሂደት መኖር የለበትም።(13) ካለበ ግን ቃል ኪዳኑ እንደ ሽያጭ ውል ፅኑ እንዲሆንና ማፋረስ የማይቻልበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ ስለሚያደርገው ግብይቱ ገና ቤቱ በሻጩ ይዞታ /ባለቤትነት/ ስር ሳይገባ እንደተፈፀመ ያህል ታስቦ የተከለከለ ይሆናል።

ባንኩ /ድርጅቱ/ ቤቱን ከገዛ በኋላ ለመግዛት ቃል የገባው ደንበኛ ቃሉን ቢያፈርስ ለሌላ ደንበኛ መሸጥ ይችላል፤ ወይም ቀድሞውኑ ቤቱን ሲገዛ በተገደበ የጊዜ ወሰን ውስጥ ለሻጩ መመለስ የሚያስችል ምርጫ (خيار الشرط) እንዲኖረው ቅድመ ሁኔታን ማስቀመጥ ይችላል።

በመጨረሻም ሙስሊም ባለሀብቶች በሐላል ገደቦች ተወስነው በእንዲህ ያለ መስክ መዋእለ ንዋያቸውን ማዋላቸው ለችግሩ መፍትሄ የሚያበጅ አንድ እርምጃ ከመሆኑ አንፃር እቅዳቸው (ኒያቸው) ካማረ ከዓለማዊ ትርፍ ባሻገር ለአኺራቸው ስንቅ የሚሆን ምንዳም እንደሚያተርፉበት አያጠራጥርም።

والله أعلم

## የግርጌ ማስታወሻዎች

(1)الإشراف لابن المنذر (6/142)، والإحماع له ص 55، المحلى لابن حزم (8/77)، الكافي لابن عبد البر ص 318، والاستذكار له (6/ 513 و 516) ، المغني لابن قدامة (6/436) ، تفسير القرطبي (3/241)

(2) صحيح مسلم (1598)

(3)فتوى " مجمع البحوث الإسلامية " بالقاهرة في مؤتمره الثاني المنعقد في شهر محرم 1385 هـ ( مايو 1965م )

(4) ينظر للتوسع في الفرق بينهما: "الحاجة الشرعية حدودها وقواعدها" لـ أحمد كافي ص 36 - 48

(5) نظرية الضرورة الشرعية" ( ص 67 ، 68 )، "المنثور في القواعد" للزركشي (2/319)

(6) المنثور في القواعد" للزركشي (2/319)، والأشباه والنظائر للسيوطي (1/ 213)، وحقيقة الضرورة الشرعية وتطبيقاتها المعاصرة د. محمد الجيزاني ص- 47

(7) "المفصل في القواعد الفقهية" ص 268 – 269، د. يعقوب الباحسين، و"فقه النوازل للأقليات المسلمة" 2/868

(8) مجموع فتاوى ومقالات الشيخ ابن باز ( 19/301)

(9)ينظر قرار رقم: (52/1/6) لمجلس مجمع الفقه الإسلامي الدولي المنعقد في دورة مؤتمره السادس بجدة من 17-23 شعبان 1410 الموافق 14 – 20 آذار (مارس) 1990م ، بشأن التمويل العقاري لبناء المساكن وشرائها، مجلة المجمع (العدد الخامس، ج4 ص2773 والعدد السادس ج1 ص81)

(10) انظر كُتيب "وقفات هادئة مع إباحة القروض الربوية لتمويل شراء المساكن في الغرب" د. الصاوي، و"فقه النوازل للأقليات المسلمة" تأصيلا وتطبيقا د. محمد يسري إبراهيم 2/851 - 893

(11) "المفصل في القواعد الفقهية" د. يعقوب الباحسين، ص 268 – 269، و"ضوابط الحاجة التي تنزل منزلة الضرورة" مجلة جامعة دمشق للعلوم الاقتصادية والقانونية – المجلد 26- العدد الأول - 2010 ص- 683 – 687، و"فقه النوازل للأقليات المسلمة" 2/868

(12) قرارات وتوصيات المؤتمر الثاني لمجمع فقهاء الشريعة بأمريكا (ص- 100)، و"وثائق النوازل" (فقه النوازل – الإصدار الثاني) د. الجيزاني 4/2361 وثيقة رقم 692

(13)ينظر: قرار مجمع الفقه الإسلامي بجدة، قرار رقم: 40 -41 (2/5 و3/5)، والمعايير الشرعية لهيئة المحاسبة والمراجعة للمؤسسات المالية الإسلامية، رقم 8 ص- 205

∞∞∞∞≅≅≅≅∞∞∞∞

# ነሲሓ ቤተሰብ

⇒ ጤናማ ትዳር

⇒ የልጆችዎን በራስ መተማመን ስነ-ልቦና ለመገንባት የሚረዱ ነጥቦች

⇒ ቤተሰቦቼ አስገድደው ሊድሩኝ ነው ምን ላድርግ?

⇒ ከእጹብ ድንቆች ማህደር

⇒ አርዓያዎቻችን





# ጤናማ ትዳር

የ ትዳር ህይወት ጤናማ እንዲሆን ሦስት መሠረታዊ ነጥቦች ያስፈልጋሉ። የሡከነ እና ለተጣማሪዎቹ ሠላማዊ ህይወት የሚመግብ ትዳር እነዚህን ሦስት መሠረታዊ ነገሮችን ሟሟላት አለበት።

## 1. ለጤናማ ትዳር የሚያስፈልጉ ነጥቦች

### ▪ ሙገሳና አክብሮት

ጤናማ የትዳር ህይወት ብዙ ጥረት ይፈልጋል። ጤናማነቱ እያበበና እያደገ እንዲሄድ ደግሞ ጥረቱ መቋረጥ የለበትም። ይህም ሆኖ ፈተናዎችና ችግሮች ማጋጠማቸው አይቀርም። በትዳር ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለማለፍ ደግሞ በባልና በሚስት መካከል መከባበር መኖር አለበት። ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው የሚለዋወጡት አክብሮትና ሙገሳ ከፍተኛ የስነ-ልቦና ጥንካሬን ይፈጥርላቸዋል። በመሀላቸውም ጠንካራ መተማመን ያብባል። በዚህ ታግዘው ከችግሮቻቸው በአላህ ፈቃድ ሊወጡ ይችላሉ። ሙገሳና አክብሮት መለዋወጥ ለትዳር ህይወት ጤናማነት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። ባለትዳሮች ችላ ሊሉት አይገባም። የትዳር ጤናማነትም ይጠቁማል።

### ▪ ለትዳር አጋር መልካም መመኘት

ለትዳር አጋሩ መልካም መመኘት የማይወድ ሰው አለ የሚለውን ለማመን ይከብዳል። ነገር ግን በአሳዛኝ ሁኔታ ጤንነቱን ባጣ የትዳር ህይወት ውስጥ ይህን አይነት ችግር ሊከሰት ይችላል። በትዳር ተጣማሪዎች መካከል ጥላቻና ሌላውን የመጉዳት ስሜት ሊኖር አይገባም። ይህ ስሜት ካለ ትዳሩ በሽተኛ ነው። በጣም አደገኛም ስለሆነ አስቸኳይ ህክምና ያስፈልገዋል።

### ▪ ምስጢር ከቤት አለማውጣት

የቤት ውስጥ ምስጢሮች ሾልከው በየስፍራው የሚገኙበት ትዳር ጤናማ አይደለም። ጤናማ ሊሆንም አይችልም፤ ጤንነቱን ለማስመለስም ይከብደዋል። ጤናማ የትዳር ህይወት ለትዳር ውስጥ ምስጢሮች ከፍተኛ ትኩረትና ጥንቃቄ ይሠጣል። የቤት ችግሮች ምንም ያህል ቢገዝፉ አደባባይ አያወጣቸውም። የቤት ምስጢርን መጠበቅ ትዳሩ ጤናማ መሆኑን ከማሳየቱም ባሻገር በባልና በሚስት መካከል ያለውን ጠንካራ ትስስር ያሳያል። ኢስላም የቤት ውስጥ ምስጢሮች መጠበቅና ባልና ሚስት ጋር መቅረት እንዳለባቸው የጠበቀ መርህ አስቀምጧል። ይህ መርህ በትዳር ውስጥ በተግባር መተርጎም አለበት። የሡከነ ትዳር ለማግኘትም መሠረታዊ ነጥብ ነው።

## 2. ትዳርን የሚያናጉ አራት ምክንያቶች

በርካታ ጉዳዮች ለትዳር መፍረስ ምክንያቶች ይሆናሉ። በተለይ አራት ምክንያቶች በትዳር ውስጥ ከተከሠቱ በትዳሩና በፍቺ መካከል የሚኖረው ርቀት ቅርብ ይሆናል። የትዳርን ውድቀት ያፋጥናሉ። የሚከተሉት ናቸው።

### ▪ ንቀት

አንድ ሙስሊም በፍጹም ሙስሊምን ሊንቅ አይገባም:: ንቀት አንድን ሰው ለጀሀነም ሊዳርግ የሚችል በቂ መጥፎ ተግባር ነው። ንቀት የትዳርን ህይወት የመበጥበጥና የማፍረስ ዓቅሙ ከፍተኛ ነው። ጥላቻን ይወልዳል። መርዝ ያመነጫል። ንቀት በቃላት ብቻ ሳይሆን በፊትና በእንቅስቃሴም የሚገለጽ ስሜት ነው። በየትኛውም መንገድ መወገዝ አለበት።

### ▪ ትችት ( የመረረ ነቀፌታ)

በትዳር ውስጥ ብዙ ችግሮች ሊከሠቱ ይችላሉ። በዚህ ወቅት ስርዓት ባለው መንገድ ቅሬታን ማሠማት ችግር አይኖረውም። ሆኖም ግን ቅሬታን በመረረ ትችት መግለጽና ስህተቱንና ስህተት ፈጻሚውን ደባልቆ በኃይለ ቃል መንቀፍ ለትዳር አጋር መጥፎ መልዕክት ያስተላልፋል። ለምሳሌ ሚስት የቤት ቆሻሻዎችን ወደ ውጪ ሳታወጣ ቀረች «ረስታ» ሲሆን። ተንኮለኛ ስለሆንሽ ነው ያላወጣሽው የሚል ስህተቱን ሳይሆን ራሷን (ስህተቱ ላይ ሳይሆን ስህተት ፈጻሚ ላይ) ያነጣጠረ ቅሬታ መሠንዘር በትዳር ህይወት ውስጥ ችግር ይፈጥራል። በተደጋጋሚም ሲከሠት ትዳሩ የፍቺ በር ማየት ይጀምራል።

### ▪ ራስን መከላከል

ችግሩ የእኔ አይደለም፤ የአንቺ ነው። ይህ አገላለጽ በውስጡ ራስን የመከላከልና ሌላውን በጅምላ የማውገዝ ድባብን ይዟል። አለመግባባትን ያባብሳል። በመጨረሻም ወደ ፍቺ በር ያደርሳል። ስለዚህ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ራስን መከላከያ ድንበር ማስመር ብቻ ሳይሆን የትዳር አጋርን ስሜት መረዳት ይበልጥ ጠቃሚ ይሆናል። ሌላውን በማውገዝና ራስን በማጽዳት የትዳር ዘለቄታ ማረጋገጥ አይቻልም።

> ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው የሚለዋወጡት አክብሮትና ሙገሳ ከፍተኛ የስነ-ልቦና ጥንካሬን ይፈጥርላቸዋል። በመሀላቸውም ጠንካራ መተማመን ያብባል።

## 3. የባልሽን ልብ ለመያዝ የሚጠቅሙ ነጥቦች

የትዳር ህይወትን በኢማን ያበበ ጣፋጭ ለማድረግ የትዳር ክህሎቶችን ማወቅ ያስፈልጋል። ወደ አዲስ የትዳር ህይወት እግሯን ያስገባች ወጣት የትዳር ክህሎቶችን በተለይም የትዳር አጋሯን ልብ መቆጣጠር የምትችልባቸውን ባህሪያት ጠንቅቃ ማወቅ አለባት። በርግጥ የትዳር ህይወት ክህሎቶችን ማወቅ አዲስ ትዳር ውስጥ የገቡ ወጣት ሴቶችን ብቻ ሳይሆን በትዳር ውስጥ ያሉትን ሁሉ ይመለከታል።

### ▪ ጓደኛው ሁኚ

ባልሽ ሚስቱ ብቻ ሳይሆን ጓደኛውም እንድትሆኚ ይፈልጋል። ልቡን በእጅሽ ለማስገባት ከማንም በላይ የሚቀርበው ጓደኛ ሁኚለት፣ ሁሉንም ጉዳዩቹን ተካፈይው። ችግሮቹን አድምጪው። ለርሱ ችግር መጨነቅሽንና በችግሩ ፊት አብረሽው እንደምትቆሚ አስረጅው። ጓደኝነታችሁ የጠለቀ እንዲሆን በምድር ላይ የሚያስፈልግሽ ብቸኛው ሰው እርሱ እንደሆነ እንዲሠማው አድርጊው፣ ጓደኛሞች የሚያደርጉትን ሁሉ አብራችሁ አድርጉ።

### ▪ እናቱን ሁኚለት

እንደ እናቱ ተንከባካቢ ሁኚለት፤ እንደ አባት አሳቢ ይሆንልሻል፤ ልቡን አሳልፎ ይሰጥሻል። ህፃን መሆን ሲያምረው እቀፊው። እናት ለልጇ የምትሠጠውን እንክብካቤ ስጪው። አርፍዶ ሲገባ መጨነቅሽን አሳይው። ዓለሙን ሁሉ ሁኚለት፣ በሚወዳቸው ትናንሽ ነገሮች ላይ ሳይቀር ትኩረት አድርጊ። እንክብካቤሽና የምታሳይው አሳቢነት ልቡን ይቆጣጠረዋል። ከአንቺ መለየት ከእናቱ እንደመለየት ይከብደዋል።

### ▪ ከግትርነት ራቂ

ወንድ ልጅ ግትርና ጨቅጫቃ ሴትን አይወድም። በንዝንዝ ህይወቱን ወደ እስር ቤት የምትለውጥበትን ሴትን አይወድም። ግትርነት እና ጭቅጭቅ የትዳር ሠላምን ያናጋል። በምትነጋገሩበት ወቅት ስህተቱን ብትነግሪው ችግር የለውም። በፍጹም ግን ክብሩንና ወንድነቱን አትፈታተኚው። የምትፈልጊውን የማሟላት ብቃት እንደሌለው እንዲሰማው አታድርጊ። ከዚህ በኋላ ልቡ ውስጥ ቦታ አይኖርሽም። የወንድ ልጅ ልብ የሚቆስለው በፍጥነት ነው። ከዚያ በኋላ ለማከም ያስቸግራል።

### ▪ ንፁህ ልብ ይኑርሽ

ባል ንፁህ ልብ ያላት ሚስቱን እስከ ዕድሜው መጨረሻ ከመውደድ አይቆጠብም። ረሡል (የአላህ ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን) የመጀመሪያ የህይወት አጋራቸውን ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድን ምን ያህል ይወዷትና ከህልፈቷ በኋላም ምን ያህል ያስታውሷት እንደነበረ አስታውሺ። ለኸዲጃ ካላቸው በጣም ብዙ የውዴታ ምክንያቶች አንዱ ኸዲጃ ንፁህ ልብ ያላት ምርጥ ሴት መሆኗ ነው። በተንኮል ልቧን ለሞላች ሚስት ልቡን አሳልፎ የሚሠጥ ባል የለም። ሚስቱን መጀመሪያ ላይ የሚወድ ቢሆን እንኳ ተንኮለኛ ልብ ካላት በሂደት እየጠላትና ልቡን ከእርሷ እያራቀ ይሄዳል። ቀስ በቀስም አንዲትም ደቂቃን ቢሆን ከእርሷ ጋር ለማሳለፍ ይጠላል። ስለዚህ የባልሽን ልብ ለመቆጣጠር ንፁህ ልብ ይኑርሽ።

### ▪ ቀልድ እወቂ

ባልሽ ፈገግ እንዲል ቀልድ ንገሪው። በራስሽ ላይ ፣ በርሱ ላይ ለጨዋታ የሚሆን ቀልድ ፍጠሪ ቀኑን ብሩህ አድርጊለት፤ ልቡን አሳልፎ ይሠጥሻል። ጭንቀቱን ቀላል ስላደረግሽለት ያመሰግንሻል፤ ከልቡ ይወድሻል። ባሎች ቀልድ የሚችሉ ሚስቶችን ይወዳሉ።

### ▪ በዓይኖችሽ አናግሪው፤

ዓይን የልብ መስተዋት ነው። አንደበትሽ ሳይናገር በዓይኖችሽ ብቻ ምን ያህል እንደምትወጂው ንገሪው። ዓይኖችሽ ወደ ዓይኖቹ ፍቅርሽን ያደርሱልሻል። የዓይኖችሽ መልዕክቶች ከአንደበትሽ በበለጠ ወደ ባልሽ ልብ በፍጥነት ይደርሳሉ። ልቡንም ይቆጣጠሩታል። ተፅዕኖአቸውም ከባድ ነው። ዓይኖችሽን መናገር ያስቻላቸው አላህ የተመሠገነ ይሁን።

------------*********------------

# የልጆችዎን በራስ የመተማመን ስነ - ልቦና ከመገንባት የሚረዱ ነጥቦች ...

ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ነው:: የአላህ ሰላም እና እዝነት የነብያት መደምደሚያ በሆኑት መልዕክተኛው ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን:: አላህ ምድር ላይ ከሚለግሰን ጸጋዎች መሀከል የልጅ ስጦታ አንዱ ነው። ለዚህም ጸጋ ከምስጋና ጋር በጥሩ ተርቢያ ማሳደጉ የወላጅ ሀላፊነት ነው። ለልጆች በራስ የመተማመን ስነ ልቦናን ለመገንባት የሚያስፈልጉ ነገሮች ማወቁ ጠቃሚ ይሆናል። ከነሱም ውስጥ :-

✓ በአላህ ላይ መመካትን አስተምረው፣ በራስ የመተማመን ስሜቱ በአላህ ላይ ከሚኖረው መደገፍ የመነጨ መሆን እንደሚገባው አስረዳው።

✓ በዋነኝነት አላህን እንዲወድ አድርገው፣ ኢማን በልቡ ውስጥ ለማስገባት ጥረት አድርግ ::

✓ ከቁርዓን ጋር ያለው ግንኙነት የጠበቀ እንዲሆን አድርግ ::

✓ ሶላትን አስተምረው አብሮህ እንዲሠግድ አድርግ::

✓ ዘወትር ዱዓ ማድረግ እንደሚኖርበት አስተምረው። ሲጨንቀው ወደ አላህ መሸሸ እንዳለበት አስረዳው:

✓ ስለ ሶሀቦች የህይወት ታሪክ መጻሕፍትን አንብብለት ፤ ምን ያህል መንፈሰ ጠንካራና መልካም ሰዎች እንደነበሩ አስተምረው::

✓ መጻሕፍትን እንዲያነብ አበረታታው። በንባብ በሚያገኘው ዕውቀት በራስ የመተማመን ስነ ልቦናው እንዲዳብርለት አድርግ ።

✓ ስለ ዓላማው ፤ ስለ ህልሙ፣ ስለምኞቱ አዋራው። ሐሳብህን አካፍለው።

✓ ስለራስህ አጫውተው። በአባቱና በእናቱ ደስተኛ ልጅ እንዲሆን አድርግ።

✓ ሐሳቡን እንዴት መግለጽ እንደሚችል አስተምረው ሐሳቡን ያለፍርሃት መግለጽ እንዲችል አደፋፍረው ስርዓትን አስተምረው

✓ ሐሳብህን አካፍለው፤ የርሱንም ሐሳብ ጠይቀው ሀሳቡ ከዲን የወጣ እስካልሆነ ድረስ ተቀበለው::

✓ ጥያቄ እንዲጠይቅ አበረታታው የሚሠነዝራቸውን ጥያቄዎች «ምን አይነት ጥያቄ ነው» የሚል መልስ በመስጠት አታሸማቅቀው፤ ከተሳሳተ ስህተቱን አስረዳው

✓ ጥያቄዎቹን መልስለት፣ ልጅ ነው ብለህ ቸል አትበለው ::

✓ እሺ ማለት ብቻ ሳይሆን የማይስማማውና የማይወደው ነገር ሲኖር እንዴት እንደሚል አስተምረው ::

✓ በራሱ ምርጫውን እንዲወስንና አቋም የመያዝ ክህሎቱን እንዲያዳብር ድጋፍ አድርግለት ::

✓ አላህ ብዙ፣ ችሎታዎችን እንደለገሰው ንገረው፣ ተፈላጊ እና ቦታ የሚሠጠው እንደሆነ እንዲሠማው አድርገው ::

✓ኃላፊነቶችን እንዲወስድ አድርግ::

> **ስለሶሀቦች የህይወት ታሪክ መጻሕፍትን አንብብለት ፤ ምን ያህል መንፈሰ ጠንካራና መልካም ሰዎች እንደነበሩ አስተምረው::**

✓ ሲወድቅ ራሱን ችሎ እንዴት መነሳት እንዳለበት አስተምረው::

✓ በቤት ውስጥ ዐቅም በፈቀደ መጠን የራሱ ክፍል፣ የራሱ ቦታ እንዲኖረው አድርግ::

✓ ቢያንስ ብቻውን ቢሆን ለራሱ ምግብ ማቅረብ የሚችልበትን ያህል ማብሰል አስተምረው ::

✓ የራሱን ክፍል፣ የራሱን ልብሶች፣ እንዲሁም የራሱን የትምህርት መገልገያዎች ራሱ እንዲያስተካክልና በስርዓት እንዲይዝ አስተምረው ::

✓ እርሱን በተመለከተ በምትወስዳቸው ውሳኔዎች ላይ አማክረው፤ ሐሳቦችንና ፍላጎቶቹን አዳምጥ። እርሱ ምን ያውቃል ልጅ ነው ብለህ ፍላጎትህን ብቻ ልትጭንበት አትሞክር።

✓ አንድ ነገር እንዲፈፅም ስትፈልግ ቀጥተኛ ትዕዛዝ አታድርግበት ከተመቸህ ይህን እቃ ታቀብለኛ? እቃዎችህን በስርዓት ብታስቀምጣቸው ጥሩ ነው! ይህን የመሠሉ አገላለጽ ተጠቀም::

✓ ሥራዎችን ሲያጠናቅቅ አወድሰው። የማበረታቻ ሽልማቶች ስጠው::

✓ ልጅህን በሰዎች ፊት አሞግሠው ::

✓ ልጅህ ጥሩ ነገር ሲሠራልህ ፣ ያዘዝከውን ሲፈጽም “አመሰግናለሁ” በለው::

✓ ትላልቅ ጥሪዎች ሲኖሩህ ቁም ነገር ያላቸው ከፍተኛ ቦታዎች ስትሄድ በቻልከው አቅም አብሮህ እንዲሆን አድርገው። ከሁሉም በላይ ልጅህን ይዘህ ልትሄድ የሚገባው ትልቅና ቁም ነገር ያለው ቦታ መስጅድ ነው።

✓ ልጅህ ልጅነቱን እንዲያጣጥም ዕድል ስጠው ልጅነቱን እንዲኖር ፍቀድለት::

✓ ጥሩ ጓደኞች እንዲያፈራ ድጋፍ አድርግለት። በጓደኞቹ ፊት አትውቀሰው ክብር ስጠው::

✓ ከሌሎች ልጆችና ከወንድሞቹ/ ከእህቶች ጋር በጋራ መሥራትን አስለምደው፣ በቡድን ውስጥ እንዴት ኃላፊነቱን እንደሚወጣ አሳየው::

✓ በሰዎች ፊት አትናገር አትበለው፣ ሀሳቡን በማቋረጥ አታሸማቅቀው።

✓ ራሱን ማክበርና ሰዎችን ማክበር እንዴት እንደሚችል አስተምረው ::

✓ የተለያዩ ምክንያቶች በመደርደር ከሰዎች አታርቀው። ሰዎችን መቅረብ የሚወድ አድርገው ::

✓ ልዩና አስደሳች ስጦታዎችን ባልጠበቀው ሠዓትና ቦታ ስጠው።

✓ የገባህለትን ቃል አክብር፣ ቃልህን ማክበር የማትችልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ቀደም ብለህ አስረዳው፣ ይቅርታም ጠይቀው::

✓ ጥፋት ስትፈጽምበት ይቅርታ ጠይቀው::

✓ ዘወትር ዱዓ አድርግለት። አላህን መልካሙን መንገድ እንዲያመላክተው ከክፋት ሁሉ እንዲጠብቀው በወላጅ ልብ ተማፀንለት። ሁሉም መሆን የሚችለው በአላህ ሀይልና ፍቃድ ብቻ ነው።

___________*********____________

# ካውንስሊንግ

## ካስገድዳው ኪዳኑኝ ነው ምን ካድርግ ?

ቤተሰቦቼ በጋብቻ ሊያስገድዱኝ እየሞከሩ ስለሆነ ከወላጆቼ ጋር እየተጋጨሁ ነው። ልጁን አልወደድኩትም። የወላጆቼን ሀቅ ማጓደል ያስፈራኛል። ቢሆንም የማልወደውን ህይወት መጀመር አልፈልግም። ጋብቻውን ባልቀበል ተጠያቂነት ይኖርብኛልን? ተጨንቄያለሁና ምክራችሁን ለግሱኝ።

::::::::::::::::::

**ምላሽ፡-** የቤተሰብን ምክር እና ተሞክሮ በትኩረት አድምጦ ውሳኔ ላይ ከመድረስ በፊት እንደ ደጋፊ ሀሳብ መመልከት ተገቢ ነው። ይህ ማለት ግን የአንቺ ውሳኔ በነሱ ስሌትና ምርጫ ብቻ የተገደበ ነው ማለት አይደለም። ምርጫውና የመጨረሻ ውሳኔው ያንቺ ብቻ ነው።

ሆኖም ግን የቤተሰብ ምርጫም መልካም ሊሆን ይችላልና መለስ ብለሽ የጠላሽው በምን ምክንያት እንደሆነ አስተውይ። በወላጅ በኩል ወደ ትዳር መሄድ ኋላ ቀርነት ነው ከሚል መነሻ ብቻ ከሆነ ተሳስተሻል። ካለሽበት ዕድሜና ካለሽ የህይወት ተሞክሮ አንፃር ያዩብሽ የብስለት ማነስ መጥፎ ሰው ላይ እንዳይጥልሽ ከመስጋት ሊሆን ይችላል።

መልካም ሰው በመምረጥ ልጅን ወደ ትክክለኛ ምርጫ ማመላከት ከተከበሩ የጨዋ ማህበረሰብ እሴቶች የሚቆጠር ነው። በወላጆችሽ በኩል የቀረበልሽን ሰው የጠላሽው በዲናዊ እንከኖቹ ምክንያት ከሆነ ግን፤ ዲን የህይወት መሰረት ነውና ለአፍታም እንዳታመነቺ። ሸሪዓን እስካልተፃረረ ድረስ ሌሎች መስፈርቶችንም ማስቀመጥ አትከለከይም።

☞ ወላጆች ልጃቸውን አስገድደው መዳራቸው ሀራም ነው። የኢስላም ሊቃውንት እንዳብራሩት ተከታዩ ሀዲስ ለዚህ መረጃ ነው።

لَا تُنْكَحُ الْبِكْرُ حَتَّى تُسْتَأْذَنَ) رواه البخاري ومسلم )

*«ልጃገረድ ፍቃድ ሳትጠየቅ አትዳርም!» ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል*

ማስገደድ የሚቻል ቢሆን ፍቃድ መጠየቋ ምንም ትርጉም አይኖረውም ነበር። ይህ ላላገባችዋ ልጃገረድ ከሆነ አግብታ የፈታችውን – ባለ ተሞክሮ ሴት– ልትማከር እንደሚገባ ኡለማዎች ያሰምሩበታል። እንደዚሁ ወላጆች ወንድ ልጃቸውንም ማስገደድ አይፈቀድላቸውም።

አል ኢማም አል–ቡኻሪ ይህንን ሀዲስ በኪታባቸው ሲያሰፍሩ የሰጡት ርእስ [አባትም ይሁን ሌላ (ወሊይ) ልጃገረድንም ይሁን አግብታ የፈታችን ሴት በፍላጎቷ ካልሆነ በቀር መዳር እንደማይችል የሚገልፅ ክፍል] የሚል ነው።

አላህ ሴት ልጅ የለገሰው አባት፤ ልጁ የወደደችው ባል አቻዋና መሰረታዊ መስፈርቶችን ያሟላ እስከሆነ ድረስ ጌታውን ሊፈራና ፍላጎቷን ሊያሟላ ይገባዋል።

ያልወደደችውን ሰው መርጦላት እንድታገባ ቢያስገድዳት አላህ ዘንድ ያስጠይቀዋል። ወላጆቹ ካለፍላጎቱ ቢድሩት ምን አይነት ምላሽ ሊኖረው እንደሚችል ራሱን ሊጠይቅ ይገባል። እውን ምርጫቸውን ሳይወድ በግድ ተቀብሎ ትዳር ይመሰርት ነበርን??

አባት ልጁን የሚድረው ለራሷ ጥቅም ነው። ኑሮዋም የራሷ ነው። ስለዚህ ለማትፈልገው ሰው መዳሩ ህይወቷን ማበላሸት ይሆናል። አብዛኛውን ጊዜ በግዴታ የተመሰረተ ትዳር ለውድቀት የቀረበ ነው።

> **እንዲትን ሴት ከምትጠላው ሰው መዳር የሸሪዓ መሰረታዊ መርሆዎችን ከመፃረሩም ባሻገር ጤናማ አዕምሮም የሚቀበለው አይደለም።**

ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ እንዲህ ብለዋል፡- *«አንዲትን ሴት ለምትጠላው ሰው መዳር የሸሪዓ መሰረታዊ መርሆዎችን ከመፃረሩም ባሻገር ጤናማ አዕምሮም የሚቀበለው አይደለም። በአላህ ይሁንብኝ፤ ካለፍቃዷ አንድን ነገር እንድታከራይም ይሁን እንድትሸጥ ሊያስገድዳት አይችልም። የማትወደውን እንድትመገብ፣ እንድትጠጣ ወይም እንድትለብስም ማስገደድ አይችልም። ታዲያ ከማትወደው ሰው ጋር በትዳር እንድትጣመርና ዘወትር አብራው እንድትኖር እንዴት ያስገድዳታል?? አላህ በባለትዳሮች መካከል ፍቅር እና መተዛዘንን ደንግጓል። ነገር ግን ይህ ትዳር የተመሰረተው እየጠላችው፣ እየሸሸችው ከሆነ ምን አይነት ፍቅርና መተዛዘን ሊመሰረት ይችላል?» አል ፈታዋ 32/25*

ከዚህ በመነሳት፤ አንድ ሰው የወላጆቹን ምርጫ ባይቀበል ወላጆቹን እንደበደለ አይቆጠርም። ፍላጎታቸውን ባለማሟላቱም ወቀሳ የለበትም።

ይህንን በማስመልከት ኢብኑ ተይሚያህ እንዳሉት ...

وليس للأبوين إلزام الولد بنكاح من لا يريد، فإن امتنع لا يكون عاقاً، كأكل ما لا يريد الاختيارات" (ص 344) .

*«ወላጆች ልጃቸውን በጋብቻ የማስገደድ መብት የላቸውም። ጋብቻውን ባይቀበል ወንጀለኛ አይሆንም።» አል–ኢኽቲያራት ገፅ 344*

ወላጆች ለልጆቻቸው አዛኝ እንዲሆኑ፣ ሰዎች ያልኩትን ሁሉ ሊታዘዙኝ ይገባል ከሚል ኩራት በአላህ እንዲጠበቁ ይመከራሉ። በቤተሰብ ውስጥ ይህን መሰል አለመግባባት ሲከሰት ለልጃቸው ሀሳብ ቦታ በመስጠት በሰከነ መንፈስ መመካከር ይገባል።

ውዷ እህታችን... ለወላጆችሽ ለስላሳ ሁኚ። ሀሳብሽን በጥበብ ግለጪ። ድምፅሽን ከፍ ከማድረግም ይሁን ከኩርፊያ ተቆጠቢ። ሸይጧን ይህንን መነሻ በማድረግ በመካከላችሁ ያለውን ክፍተት ሊያሰፋ ያሴራልና ጆሮ እንዳትሰጭው። በእጅጉ ጠንቃቃ ሁኚ። ነገሩ ካቅምሽ በላይ ከሆነ ለቤተሰብ ቅርብ የሆኑ አስተዋይ ሰዎች ጣልቃ ገብተው ወላጆችሽን እንዲያሳምኑልሽ ጥረት አድርጊ።

ከዚህ ሁሉ ጥረት በኃላ አሻፈረኝ ካሉ የመታዘዝ ግዴታ የለብሽም። በደሉ ከነሱ በኩል ነውና አንቺን አይጎዳሽም። ነገር ግን ሀቃቸውን አለማጉደልን እና በመልካም መኗኗርን የዘወትር ልማድሽ አድርጊ። እንኳን በጋብቻ በእምነት የሚፃረሩን ወላጆች እንኳ በዚህ መልኩ እንድንንከባከብ ታዘናል።

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

(وَإِنْ جَاهَدَاكَ عَلَى أَنْ تُشْرِكَ بِي مَا لَيْسَ لَكَ بِهِ عِلْمٌ فَلَا تُطِعْهُمَا وَصَاحِبْهُمَا فِي الدُّنْيَا مَعْرُوفًا) لقمان/15 .

«ለአንተ በእርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር በእኔ እንድታጋራ ቢታገሉህም አትታዘዛቸው፡፡ በቅርቢቱም ዓለም (በዱንያ) በመልካም ሥራ ተወዳጃቸው፡፡ ወደእኔም የተመለሰን ሰው መንገድ ተከተል፡፡ ከዚያም መመለሻችሁ ወደእኔ ነው:: ትሠሩት የነበራችሁትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፡፡» ሉቅማን 15

አላህ መልካሙን ሁሉ ይግጠምሽ!!

**© ተንቢሀት ካውንስሊንግ**
http://www.facebook.com/tenbihat

------------*********------------

# ከእጹብ ድንቆች ማህደር

✍ ኡሙ ዐብዲላህ ነፊሳ ሙሐመድ

## መርየም ቢንት ዒምራን የጨዋነት ተምሳሌት

ስለዚህች እንቁ እንስት የነብዩ ዒሳ (ዐለይሂ ሰላም) እናት መርየም ጨዋነቷንና ጥብቅነቷን አስመልክቶ አላህ (ሱብሃነሁ ወተአላ) በተከበረው ቃሉ ቁርአን ውስጥ በተደጋጋሚ አውስቷታል፡፡ አላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) እንዲህ ይላል ፡-

﴿ وَمَرْيَمَ ابْنَتَ عِمْرَانَ الَّتِي أَحْصَنَتْ فَرْجَهَا فَنَفَخْنَا فِيهِ مِن رُّوحِنَا
وَصَدَّقَتْ بِكَلِمَاتِ رَبِّهَا وَكُتُبِهِ وَكَانَتْ مِنَ الْقَانِتِينَ ﴾

*"የዒምራንን ልጅ መርየምንም ያቺን ብልቷን የጠበቀቺውን (ምሳሌ አደረገ)። በርሱም ውስጥ ከመንፈሳችን ነፋን። በጌታዋ ቃላትና በመጻሕፍቱም አረጋገጠች ከታዛዦቹም ነበረች"* አተህሪም 12።

በስሟም ራሱን የቻለ ምእራፍ ሰይሞላታል። ምእራፍ መርየም። ኢስላም ለሴት ልጅ ከሰጠው ክብርም ይህ በዋነኝነት ተጠቃሽ ነው። ምክንያቱም በፈጣሪ ንግግር ውስጥ በክብር መወሳቷ የተፈጠረችለትን አላማ ይዛ ከተጓዞች ከመምጠቅና ከፍ ማለት የሚያግዳት ነገር እንደሌለ ያረጋግጣል፡፡ የመርየምም ታሪክ ይህንን በጉልህ ያስቀምጣል። አላህ (ሱብሃነሁ ወተአላ) እንዲህ ይላል:-

﴿ وَاذْكُرْ فِي الْكِتَابِ مَرْيَمَ إِذِ انتَبَذَتْ مِنْ أَهْلِهَا مَكَانًا شَرْقِيًّا [١٦]
فَاتَّخَذَتْ مِن دُونِهِمْ حِجَابًا فَأَرْسَلْنَا إِلَيْهَا رُوحَنَا فَتَمَثَّلَ لَهَا بَشَرًا سَوِيًّا
[١٧]قَالَتْ إِنِّي أَعُوذُ بِالرَّحْمَٰنِ مِنكَ إِن كُنتَ تَقِيًّا ﴾

*«በመጽሐፉ ውስጥ መርየምንም ከቤተሰቧ ወደ ምሥራቃዊ ስፍራ በተለየች ጊዜ (የሆነውን ታሪኳን) አውሳ፡፡ ከእነርሱም መጋረጃን አደረገች፡፡ መንፈሳችንንም (ጂብሪልን) ወደ እርሷ ላክን፡፡ ለእርሷም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመሰለላት፡፡«እኔ ከአንተ በአልረሕማን እጠበቃለሁ፡፡ ጌታህን ፈሪ እንደሆንክ (አትቅረበኝ)» አለች፡፡* (መርየም:16-18)

እንግዲህ አንቺ ውዲቷ እህቴ ይህንን ገጠመኝ በጥሞና አስተንትኚው። እጅግ በጣም ያማረ ውበት፣ የሰው ዘር ውልብ እንኳ የማይልበት ብቸኝነት፣ ታዲያ በዚህ አጓጊ እና ገፋፊ ሁኔታ ላይ በጣም ያማረና የተዋበ ሰው ከተፍ ሲል። ምን ይፈጠራል ተብሎ መቼም አይጠየቅም፣ ለማንም ግልጽ ነውና። አጋጣሚው ተገኝቶ አይደለም ሳይገኝ ለማግኘት እራሱ ስንት ከንቱ መሰዋዕትነቶች ይከፈላሉ፡፡ነገር ግን የተፈጠሩለትን አላማ በወጉ የተገነዘቡ ንጹህ የአላህ ባሮች ይህን ረመጥ ሳይቃጠሉ ይወጡታል። ይህንም ገድል ከዚህች ብርቅዬ እንስት ታሪክ የምናገኘው ነው፡፡

የተሟላ ጨዋነትና ድካውን የደረሰ ንፅህና።

-----------*********------------

## አሲያ ቢንት ሙዛሃም የእምነትና የፅናት ተምሳሌት

የተንጣለሉ ህንጻዎች፣ አቤት የሚሉ አገልጋዮች፣ ዘብ የቆሙ ጠባቂዎች በቁጥጥሩ ስር የነበሩት የፊራዓውን የንግሥና ተቋዳሽና ውድ ባለቤቱ ነበረች አሲያ። ዳሩ ግን የአላህ ምድር መሰሎችን በመያዝ አናሳ የሆነው ጣኦትና በዳዩ ባለቤቷ በአማኞች ላይ የሚያዘንበው የግፍ አለንጋ እረፍት ነሳት ፡፡ በገዛ ግዛቱ ላይ ሆኖ የሚያደርገው በአላህ ላይ የመካድ ስንኩል ጉዞው አንገሸገሻት።

﴿ فَقَالَ أَنَا رَبُّكُمُ الْأَعْلَىٰ ﴾

{አለም እኔ ታላቁ ጌታችሁ ነኝ}። አል ናዚዓት 24

**"አላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) ጀነት ውስጥ ያለውን ቤቷን አሳያት። እርሷም ፈገግ አለች። ከዚያም ሞተች"**

በመጨረሻም የሴት ልጁ ፀጉር አበጣሪ የነበረችውን አማኝ በአሰቃቂ ሁኔታ ከልጆቿ ጋር ዘግናኝ የበደል ጅራፉን አሳረፈባቸው። ዓይኗ እያየ ልጆቿን በማምጣት እፊቷ አረዳቸው። ከእምነቷም እንድትመለስ ጥያቄ አቀረበላት። ጀግናዋ አማኝ ወይ ፍንክች። "የኔም ያንተም ጌታ አላህ ነው" ስትል ብቻ ነበር የምትመልስለት። እርሱም እኩይና አብሪታዊ ድርጊቱን ፈፀመባት። እንደፀናች ጌታዋን ተገናኘች። ባጭሩ ከተፍሲር ኢብኑ ከሢር ምእራፍ አል ቀሰስ 11 ላይ የተወሰደ።

ታዲያ በዚህ ጊዜ አሲያ ባሏ የሚሰራው ኢ-ሰብአዊ ድርጊት የመጨረሻ ደረጃ አደረሳት። የጀግናዋም እንስት እምነትና ፅናት አስደመማት። እርሷም በብቸኛው ፈጣሪዋ አመነች። ዳሩ ግን ይህ ጣኦት ይህን የባለቤቱን ሁኔታ ሲደርስበት ለእርሷም የሚመለስ አልሆነም። ምክንያቱም በሚለፍፈው የፈጣሪ ነኝ አምልኩኝ ዝማሬው ላይ አውዳሚ ቀስት ማሳረፏን በቅጡ ተገንዝቦታል። ይህን አባባሉን አላህ (ሱብሃነሁ) ወተዓላ ምእራፍ አል ቀሰስ ላይ ጠቅሶታል።

﴿وَقَالَ فِرْعَوْنُ يَا أَيُّهَا الْمَلَأُ مَا عَلِمْتُ لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرِي_﴾

*{ፈርኦንም እናንተ ጭፍሮች ሆይ! ከእኔ ሌላ ለእናንተ አምላክን ምንም አላውቅም አለ}*
አል ቀሰስ 38

ስለዚህም በአላህ ላይ መካድን አሻፈረኝ ካለች መሰሎቿ የተቋደሱት ግፍ እንደማያልፋት ዘተባት። ነገር ግን እንቁዋ በእንቁ ነገር እንጂ የማትረታ በመሆና በአቋሟ ፀናች። ፊርዓውንም አሽከሮቹን አዘዘ። እጅና እግሯ ተጠፍረው የቅጣቱ አለንጋ ይወርድባት ጀመር። ከክቡር አካሏ ደም ዘነበ። ቅጣቱ ጠናባት። ወደ ሞት ተቃረበች። በዚህ ጊዜ ዓይኗን ወደ ሰማይ ከፍ በማድረግ በጸሎቷ የጌታዋን (ሱብሃነሁ ወተአላ) በሮች አንኳኳች።

አላህ (ሱብሃነሁ ወተአላ) ይህንን አስደማሚ ትእይንት እንዲህ ሲል በተከበረው ቃሉ ቁርአን ውስጥ ዘክሮታል :-

﴿ وَضَرَبَ اللَّهُ مَثَلًا لِّلَّذِينَ آمَنُوا امْرَأَتَ فِرْعَوْنَ إِذْ قَالَتْ
رَبِّ ابْنِ لِي عِندَكَ بَيْتًا فِي الْجَنَّةِ وَنَجِّنِي مِن فِرْعَوْنَ وَعَمَلِهِ
وَنَجِّنِي مِنَ الْقَوْمِ الظَّالِمِينَ_﴾

*«አላህ ለእነዚያ ለአመኑትም የፈርኦንን ባለቤት ምሳሌ አደረገ፡፡ «ጌታዬ ሆይ! አንተ ዘንድ በገነት ውስጥ ለእኔ ቤትን ገንባልኝ፡፡ ከፊርዓውን እና ከሥራውም አድነኝ፡፡ ከበደለኞች ሕዝቦችም አድነኝ» ያለችውን፡፡»* (አት ተህሪም:11)

ይህንን አንቀጽ አስመልክቶ ኢብኑ ከሢር (አላህ ይዘንለትና) እንዲህ ብሏል:-

"አላህ (ሱብሃነሁ ወተአላ) ጀነት ውስጥ ያለውን ቤቷን አሳያት። እርሷም ፈገግ አለች። ከዚያም ሞተች።"

ኡለማዎችም ይህንን አስመልክተው የሚከተለውን ብለዋል።

طلبت الجار قبل دار

*"ከቤት በፊት ጉርብትናን ጠየቀች"* ተፍሲር ኢብኑ ከሢር ምእራፍ አት ተህሪም ላይ።

እንግዲህ አንቺ ውዲቷ እህቴ! ከዚህች እንቁ ጀግና አማኝ ሴት ብዙ የምትወስጂው ቁም ነገር አለ። ያ ሁሉ ግፍ ሲወርድባት ከእምነቷ ፍንክች አላለችም። ታዲያ እኛ ዛሬ ስንቶቻችን ነን ገና ለገና በመገናኛው ብዙኋን ነጻነት፤ መሰልጠን ወዘተ እያሉ እምነትን ሲያንቋሽሹ ሌላም ሌላም የጨኸታቸው ሰለባ ሆነን ከኢማን አድማስ የተሰፈነጠርነው? በእውነቱ እነዚህን እንስቶች አርአያ ማድረግ ግድ ይለናል፡፡

-------*********------------

# አርዑያዎቻችን

✍ ሙሐመድ ኢብራሂም ዐሊ

## ሸይኽ ሙሐመድ ሸይኽ

ሰውቁ ዐሊም ፈቂህ ኡሱሊ ነሕዊይ ሸይኽ አቡ-ዓብደልጀሊል ሙሐመድ ቢን ዓሊ ቢን አደም ቢን ሙሳ አል-ኢትዮቢ (ሐፊዘሁላህ) በወዳጆቻቸው ዘንድ ሸይኽ ሙሐመድ ሸይኽ በመባል ይታወቃሉ።

### ▪ ትውልድና ትምህርት

ሸይኹ የተወለዱት በሰሜኑ የሐገራችን ክፍል በቀድሞው የወሎ ክፍለ ሀገር ወረሂመኑ አውራጃ በ1366 ዓ.ሂ አቅራቢያ ነበር። የሸሪዓ ዕውቀትን 'አሊፍ' ብለው አባታቸው ላይ ቁርአን በመቅራት በመጀመር ሸይኽ ሙሐመድ ገዩ (ረሂመሁላህ) ዘንድ አክትመዋል። በመቀጠልም ከአባታቸው ሸይኽ ዓሊ አደም ሙሳ (ረሂመሁላህ) እና ከሌሎችም ታዋቂ መሻይኾች እንደ ነሕው፣ ሶርፍ፣ በላጋ፣ ኡሱል፣ መንጢቅ፣ ሐዲስ፣ ፊቅህ እና ሌሎችም ዘርፎች ላይ የጠለቀ ዕውቀትን በወቅቱ አሉ ከተባሉ የሀገራችን መሻይኾች ተምረዋል።

ሸይኹ በኢትዮጵያ ሳሉ ከቁርአን ባሻገር እንደ አልፊየቱ ኢብን ማሊክ እና አልፊያ አ'ሱዩጢ ያሉ ብዙ መትኖችንና ግጥሞችን በቃላቸው ሀፍዘዋል። እንዲሁም ከተለያዩ መሻይኾቻቸው ለብቁነታቸው ምስክርነት/ሸሀዳ ተችሯቸዋል።

### ▪ ስደት

ከዛም ሸይኽ ሙሐመድ ሸህ በወቅቱ የነበረውን የኮሚኒስት መንግስት (ደርግ) በመሸሽ ወደ መካ-ሳዑዲ ዓረቢያ ተሰደዱ። ይሁንና በጉዟቸው ወቅት በእጃቸው የያዙት 'ሸሀዳ' ባለመኖሩ በተማሪነት መካ በሚገኝ መድረሳ የተወሰነ ጊዜ ቆይተው ነበር። ቀጥሎም በወቅቱ በሸይኽ ኢብን ባዝ ወደሚመራው ዳረል ሐዲስ አቅንተው ለመማር ፈተና ቢወስዱም ያመጡት ውጤት በወቅቱ የዳረል ሐዲስ አመራሮችን አስደምሞ ለመማር የመጡትን ሸይኽ መምህር እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ከዛ ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ በዳረል ሐዲስ እና በመስጂድ አል-ሐረም ለአያሌ ዓመታት ራሳቸውን ለዒልምና ለፈላጊዎቹ ሰጥተው በማስተማር ላይ ይገኛሉ።

### ▪ ጉዞ ከአሸዓሪያ ወደ አህሉ-ሱና

ሸይኽ ሙሐመድ ሸህ ከልጅነታቸው አንስቶ ለሐዲስ ትልቅ ፍቅር እንዳላቸው ይገልፃሉ። በተማሪነት ወቅታቸውም እንደሌሎች ሰዎች ባደጉበት የሐነፊያ መዝሀብ ከመገደብ ይልቅ ሐዲስ የሚደግፈውን አካሄድ ይመርጡ እንደነበር ይናገራሉ። ሸይኹ ወደ መካ ከተሰደዱ እና ዳረል ሐዲስ ከገቡ በኋላ የእነ ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ፣ ኢብኑል ቀይም አልጀውዚ እና ሸይኹል ኢስላም ሙሀመድ አብዱልወሀብ ኪታቦችን ሲያገላብጡ በሀገራቸው ሳሉ ከተማሯቸው የዓቂዳ ትምህርቶች ጋር የሚጣረሱ ነገሮች እንዳገኙ ያወሳሉ። እናም ቀድሞም ያደርጉት እንደነበረው ሁሉ ትክክለኛ መረጃ ያለውን ሲፈትሹ አሁን ያነበቧቸው ኪታቦች ትክክል ሁነው ማግኘታቸውን ይናገራሉ።

ሸይኹ መካ ከመጡ በኋላ የተለያዩ ዓሊሞችን ኪታብ አገላብጠው የያዙትን አቋም ሲናገሩ ... "በሀገሬ ሳለሁ ከአሸዓሪይ መሻይኾቼ የተማርኩትን እና አምንበት የነበረውን ዓቂዳ በመተው ራቅኩት" ይላሉ።

ሸይኽ ሙሐመድ ሸህ አስከትለውም "አባቴን ለመጠየቅ ወደ ሀገሬ የሄድኩ ጊዜ አንድ ሰው 'አንተ ወሀቢይ ሁነሀል' አለኝ። 'የለም፡ እኔ መረጃውን ነው የምከተለው፤ እንደምታውቀው ወደ መካ ከመሄዴም በፊት ትክክለኛውን መረጃ ነበር የምከተለው' አልኩት። 'አዎ እሱን አውቃለሁ ግን ማጥበቅ ላይ ጨምረኻል' አለኝ።

> **"በሀገሬ ሳለሁ ከአሸዓሪይ መሻይኾቼ የተማርኩትን እና አምንበት የነበረውን ዓቂዳ በመተው ራቅኩት"**

እኔም 'ምነው ኢማሙ ሻፊዒ በሒጃዝ እና ዒራቅ ሳሉ አንድ መዝሀብ (አቋም) እንደነበራቸውና ወደ ግብፅ ሄደው ብዙ ማስረጃን ያገኙ ጊዜ የቀደመውን መዝሀባቸውን እንደተዉ እና አዲስ መዝሀብ እንደመሰረቱ አታውቅም እንዴ? ልክ እንደዚሁ እኔም ከሀገሬ ሰዎች የተሰወረን ማስረጃ ያገኘሁ ጊዜ ተከተልኩት፤ የሚያስይዘውንም ሠራሁበት፤ ይህ ዕድሜ ልኬን የምሄድበት አካሄድ ነው ኢንሻአላህ' አልኩት" ይላሉ ሸይኽ ሙሐመድ ዓሊ አደም አል-ኢትዮቢ [ይህ ንግግራቸው ከዌብ ሳይታቸው https://www.aletioupi. Com የተወሰደ ነው]

### ▪ *ሥራዎቻቸው*

ሸይኽ ሙሐመድ አል-ኢትዮቢ በተለያዩ ዘርፎች በርካታ መጻሕትን ፅፈዋል። በተለይ በሐዲስ ዘርፍ ያበረከቷቸው ኪታቦች ጎልተው ይወጣሉ ከነዚህም የሰሒሕ ሙስሊም ሸርሕ የሆነውን *البحر المحيط الثجاج شرح صحيح مسلم بن الحجاج* በሀምሳ ሙጀለድ/ቅፅ ሲያዘጋጁት፣ የሱነን አነሳዒ ሸርሕን *ذخيرة العقبى في شرح المجتبى* በአርባ ሁለት ሙጀለድ/ቅፅ ፅፈውታል። እነኝህ ሸርሖች የሸይኹን የዒልም ምጥቀት ለዓለም ያሳዩ ህያው ምስክሮች ሁነው ይታያሉ።

እንዲሁም በሐዲስ እና በሌሎችም ዘርፎች ከ30 በላይ ኪታቦችን ያሳተሙ ሲሆን ለህትመት የቀረቡ እና እያጠናቀቋቸው ያሉ ከ10 በላይ ኪታቦችም አሉ።

### ▪ ምስክርነት በሌሎች አንደበት

ዕውቁ የሐዲስ ሊቅ ሸይኽ አልባኒ (ረሂመሁላህ) ስለነሳኢ ሸርህ -ዘኺረቱል ዑቅባ ሲናገሩ "ይህን የመሰለ የነሳኢ ሸርህ አላውቅም" ብለው ነበር።

የየመኑ ኮኮብ ሸይኽ ሙቅቢል አልዋደዒ (ረሂመሁላህ) ስለዘኺረቱል ዑቅባ "ይህ ኪታብ የሐፊዝ ኢብን ሐጀር 'ፈትሑል ባሪ' አይነት ነው ... ዕውቀት ፈላጊዎች ይህንን ታላቅ ኪታብ ለማግኘት እንዲጥሩ እመክራለሁ። በዚህ ዘመን ያለ ሙሐዲስ ሁሉም ይህን የመሰለ ሸርህ እንዲያመጣ እጠይቃለሁ" ብለው ነበር።

ሸይኽ ረቢዕ ቢን ሐዲ (ሐፊዘሁላህ) ደግሞ ሸይኽ ሙሐመድ ሸይኽ ***'በሁሉም ዘርፍ ዓሊም ናቸው'*** ሲሉ መስክረዋል።

ሸይኹ እንዲህም ተገጥሞላቸዋል ...

يا سائلي عن عالم الأحباش ...... اسمع مقالي سمع ذي إنعاش

فالولوي إمام أهل زمانهم ...... من غير ما شك ولا إغباش

جمع العلوم أصولها وفروعها ....... مع نظمها في غاية الإدهاش

بحر بعيد غوره ونطاقه ....... قد عم كل السهل والأحراش

تعريف الشاعر لشيخ با "علم الأحباش" لأن الشيخ جاء من بلد الحبشة، الحبشيين يسمون (أحيان بلأحباش

ሸይኽ ሙሐመድ ዓሊ አደም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሸሪዓን ዕውቀት በማስተማር ብዙ መሻይኾችን አፍርተው በመላው ዓለም አሰራጭተዋል፤ አላህ ምንዳቸውን ያብዛላቸው - ዕድሜያቸውንም ያርዝመው። ሰሞኑን ባጋጠማቸው ህመም ሳቢያ ከሚሰጡት ደርስ ቢስተጓጎሉም አዛኙ አላህ እኚህን ታላቅ የዒልም ባህር ዓፊያቸውን መልሶላቸው ወደሚወዱት መስክ እንደሚመለሱ ባለሙሉ ተስፋ ነን። አላህ ከዒልማቸው የምንጠቀም ያድርገን!

አሚን

ሸዕባን 1440

___________*********___________

# ነሲሓ ብዕር

- ኢስላም ልዩ ነው !
- በአላህ ስሞችና ባህሪዎች ዙሪያ አስፈላጊና መሰረታዊ ህጎች
- አቡበክር አስሲዲቅ
- የህፃናት አመጋገብ
- የቁርኣንና የተውሒድ ቁርኝት
- ፈታዋ



# ኢስላም ልዩ ነው!

✍ ኡስታዝ ጣሃ አሕመድ

ስለ ኢስላም መልካምነት ለማውሳት እና ሁሉንም ለመዘርዘር ፈፅሞ ይህ አጭር ፅሁፍ ይበቃል የሚል ሀሳብ እንደይማኖር ግልፅ ነው። ምክንያቱም ኢስላም የወዲህኛውንም ሆነ የወዲያኛውንም ዓለም ህይወት ሁለንተናዊ በሆነ መልክ የሚዳስስ ከጥበበኞች ሁሉ ጥበበኛ፣ ለባሮቹ መልካሙን ሁሉ ከሚያውቀው አምላክ አላህ የተደነገገ ሃይማኖት ነው። ስለሆነም በሁሉም የህይወት መስኮች የኢስላማዊ ድንጋጌዎችን መልካምነት የሚገልፁ ነገሮች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው። በዚህ አጭር መልዕክት እነዚያን ሁሉ ለማሳየት መሞከር የማይታሰብ በመሆኑ የተወሰኑትን ብቻ ለመጠቆም ተሞክሯል።

1/ኢስላም የሰው ልጅን ፍጡራንን ከማምለክ (ከሽርክ) ጽልመት ፈጣሪን ብቻ ወደ ማምለክ ብርሃን አምጥቶታል።

2/ኢስላም የተከታዮቹን የህይወት መንገድ ቀይሯል ዓረቦች (ከመልዕክተኛው መላክ) በፊት በማይምነት፣ በኋላ ቀርነት እና የጎሳ ቁርቁስ ጫፍ የደረሱ ነበሩ።

3/ኢስላም ሴት ልጅን በህይወት እያለች ከመቀበር፣ ከመውረስ እንዲሁም ሌሎች መብቶቾ መከልከል እና የመሳሰሉ በማህበረሰቡ ሲደርሱባት ከነበሩት አሰቃቂ በደሎች ታድጓታል።

4/ኢስላም ከተከታዮቹ መንፈሳዊና አካላዊ ፅዳትን ይፈልጋል።

5/ኢስላም በመላው ፍጡራን የሰው ልጆችም ይሁን እንስሳት አልያም እፅዋት ላይ ድንበር ማለፍን ይከለክላል።

6/ኢስላም  የሰው ልጆችን ከእሳት ቅጣት ለመታደግ ወደ አላህ ሃይማኖት ኢስላም የመጥራት ሀላፊነት ተከታዮቹን ያሸክማቸዋል።

7/ኢስላም የሰው ልጆች አእምሮ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ ከሚችሉ እንደ አስካሪ እና አደንዛዥ ነገሮች ይከለክላል።

8/ኢስላም የሰው ልጅን ክብር እና ዘር ይጠብቃል። ስለሆነም ከዝሙት ይከለክላል።

9/ኢስላም የሌሎችን ንብረት ይጠብቃል። ስለዚህም ስርቆትን ይከለክላል።

10/ኢስላም ገንዘብን ይጠብቃል ስለሆነም እቃን በማከማቸት እንዲወደድ ማድረግን ይከለክላል።

11/ኢስላም ማህበራዊ ዋስትና እንዲኖር ይፈልጋል። ስለዚህም ዘካን ግዴታ ያደርጋል። በበጎ ፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ምፅዋትንም ያበረታታል።

12/ኢስላም የአላህ ባሮችን ወደ ዘራቸው ሳይመለከት ነጭ እና ጥቁር ብሎ ሳይለያይ በእኩልነት ይመለከታል።

13/ኢስላም ተከታዮቹ በሁሉም የቀንና የለሊቱ ክፍለ ጊዜያት ከጌታቸው ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው አምስቱ ሰላቶችን ግዴታ ያደርግባቸዋል።

14/ሙስሊም ምንዳ የሚያገኝባቸው መንገዶች ገደብ የላቸውም። ከጌታው ምንዳን ከጅሎ በሚሠራቸው መልካም ነገሮች ሁሉ ምንዳን ያገኛል።

15/ኢስላም ለመላው የሰው ልጆች ንስሃ የመግቢያን (ተውበት ማደረጊያን) በር ክፍት አድርጓል። ይህ ደግሞ ለሰው ልጆች ዘንድ በስነ-ልቦና መረጋጋትን እና ንስሃ ለመግባት መነሳሳትን ይፈጥራል።

16/አንድ ሙስሊም የሚፈፅማቸው በጎ ሥራዎች የተወሰኑ ወንጀሎቹ እንዲማሩ ምክንያት ይሆናሉ።

17/የኢስላም ገራገርነት እና በተለያዩ የዕውቀት ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች ሊረዱት መቻሉ ሰዎች ያለምንም ግራ መጋባት ወደ ኢስላም ፊታቸውን እንዲያዞሩ አድርጓል።

18/የኢስላም ግትር አለመሆን እና ከአዳዲስ ግኝቶች ጋር መስማማት መሰረቱን ጠብቆ እንዲቆይ አድርጎታል።

**ኢስላም የአላህ ባሮችን ወደ ዘራቸው ሳይመለከት ነጭ እና ጥቁር ብሎ ሳይለያይ በእኩልነት ይመለከታል።**

19/ ኢስላም ትክክለኛው ከአላህ የመጣ እና ለመላው ፍጡራን እርሱ የመረጠው እምነት ነው።

20/የኢስላም ተከታዮች አላህ በነብዩ ላይ እንዳወረደው ከመበረዝ የተጠበቀ ሰማያዊ መጽሐፍ ባለቤት በመሆን ብቸኛ ናቸው።

21/ የመጨረሻው ነብይ (ሙሐመድ የአላህ ሰላት እና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) ተከታዮቹ ንግግሩን ተግባሩን እና እጅግ ጥቃቅን ሊባሉ የሚችሉ ዝርዝር የህይወት ታሪኩን ሳይቀር ትኩረት በመስጠት ያጠኑለት ብቸኛው ነብይ ናቸው። የእርሳቸው ፈለግም በኢስላማዊ ድንጋጌ ውስጥ እንደ ሁለተኛ ምንጭ ይቆጠራል።

22/ሌሎች የአላህ ነብያት መልዕክታቸው በተወሰኑ ሕዝቦች እና ጊዜያት የተገደበ ሲሆን የነብዩ (ሙሐመድ-የአላህ ሰላት እና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) መልዕክት ግን ለመላው የሰው ልጅ እና እስከ ዕለተ ትንሳኤ (ቂያማ) ድረስ ነው።

23/ኢስላም በምድር ከሚገኙ ሃይማኖቶች ሁሉ ተከታዮቹ ፈጣሪያቸውን እርሱ ባወረደው መመሪያ መሰረት የሚያመልኩበት ብቸኛው ሃይማኖት ነው።

24/ኢስላም ለደካሞች እና ምስኪኖች እንድናዝን ያዘናል።

25/ኢስላም በማህበራዊ ግንኙነት በመስጅድ ውስጥ እና ከዚያም ውጭ ባሉ የተለያዩ የብዙኋን መገናኛ ስፍራዎች ድሀና ሀብታምን በእኩልነት ይመለከታል። ስለሆነም አንድ ባለሀብት ድሀን ከተቀመጠበት አስነስቶ በቦታው ሊቀመጥ አይገባውም።

26/ኢስላም ሙስሊሞች ነፍሳቸውን እንዴት መቆጣጠር እንደሚችሉ እና ድሆች በማጣት ምን ያህል እንደተቸገሩ እንዲሰማቸው ከዚያም ባሻገር ለመመፅዋት እንዲያነሳሳቸው በማሰብ ፆምን ግዴታ ያደርግባቸዋል።

27/ኢስላም የሰው ልጅን ሰብእና ከፍ ያደርጋል። ስለሆነም የሰው ልጅ ዱንያን መሰብሰብ የመጨረሻ ግቡ አድርጎ እንዳይመለከት ያስተምረዋል።

28/ኢስላም ግዴታ የሆነውን ምፅዋት ከመስጠት ውጪ በሌሎች የምፅዋት አይነቶች ሙስሊም በሆኑና ባልሆኑ ሰብአዊ ፍጡራን መካከል ልዩነት አያደርግም። ይልቁን ለእንስሳት የሚመፀወቱ ምፅዋቶችም እንኳ ምንዳ እንዳላቸው ያስተምራል።

29/ኢስላም ለጎረቤት ሙስሊም ባይሆን እንኳ ታላቅ ቦታን ይሰጠዋል።

30/ኢስላም ታላላቆቻችንን እንድናከብር ለታናናሾቻችን እንድናዝን ያስተምረናል።

31/ኢስላም ወላጆች ሙስሊሞች ባይሆኑ እንኳ ታላቅ መብት እንዳላቸው ያረጋግጣል።

32/ኢስላም ህፃናት ከመወለዳቸው በፊት ጀምሮ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ያስገድዳል።

33/ኢስላም የሙታኖችን መብት እንድናከበር ያሳስባል።

34/ኢስላም በሁሉም የአላህ ነብያት እንድናምን እና ሁሉንም እንድናከብር ያስገድደናል።

በመጨረሻም ከዚህ በላይ ያሳለፍናቸው ጥቂት ገለፃዎች ከኢስላም መልካምነት መገለጫዎች አንፃር ባህርን በጭልፋ እንደሚባለው ቢሆንም ነገር ግን አላህ ልቦና ለሰጠው ግን በቂ ጥቆማ እንደሚሆን እናምናለን::

አላህ ሀቅን አይተው ከሚከተሉት ሀስትን አይተው ከሚርቁት ያድርገን።

አሚን!!

------------*********------------

ቅጽ 1 ቁጥር 2 | ግንቦት 2011

# በአላህ ስሞችና ባህሪዎች ዙሪያ አስፈላጊና መሰረታዊ ህጎች

ምስጋና ለዓለማት ጌታ እጅግ በጣም ሩህሩህና እጅግ በጣም አዛኝ ለሆነው ለአላህ የተገባ ነው። ታላቅ እና ምሉዕ የሆኑ ባህሪዎች ለአላህ ተገቡ። ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው እንደሌለ እንመሰክራለን። ሙሀመድም ﷺ የአላህ ባርያና መልዕክተኛ ናቸው። የአላህ ሰላምና እዝነት በእርሳቸው በቤተሰቦቻቸው እና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን፡፡

**ተውሂዱል አስማኢ ወሲፋት** ማለት፤ "አላህን በስሞቹና በባህሪዎቹ አንድ ማድረግ" ሲሆን፤ በቁርዓንና በሐዲስ የተረጋገጡትን የአላህን ያማሩ ስሞችና የላቁ ባህሪዎች ተቀብሎ ማጽደቅ፣ በውስጣቸው ያዘሉትን ትክክለኛ መልዕክት ለአላህ ማረጋገጥ እንደዚሁ አላህ እና መልዕክተኛው ውድቅ ያደረጓቸዉን ባህሪዎች ውድቅ ማድረግ፤ አላህ በስሞቹና በባህሪዎቹ ምንም አምሳያና አጋር የሌለው ብቸኛ አምላክ መሆኑን ማመንን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

## ሦስቱ ወርቃማ መርሆዎች

በዚህ ርዕስ ላይ የአህሉሱና አቋም ሦስት አጠቃላይ መርሆዎችን መሰረት ያደረገ ነው። እነዚህ መርሆዎችም በአላህ ስሞችና ባህሪዎች ዙሪያ የተስተካከለ አቋም እንዲኖር ይረዳሉ፡፡

### የመጀመርያው መርህ

**ሁሉም የአላህ ባህሪዎች ከፍጡራን ባህሪዎች ጋር ፍጹም እንደማይመሳሰሉ በማመን አላህን ማጥራት "ተንዚህ" ፡፡**

ለዚህ መርህ ማስረጃ ከሚሆኑት ውስጥ የሚከተለው የአላህ ቃል አንዱ ነው።

*‹‹የሚመስለው ምንም ነገር የለም፡፡ እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው፡፡›› (አል ሹራ 11)*

ይህ አንቀፅ የሚያስረዳው በየትኛውም ሁኔታ በፍጡራንና በፈጣሪ መካከል መመሳሰል እንደሌለና አላህ መስሚያና መመልከቻ እንዳለው ነው፡፡ መስሚያና መመልከቻ የብዙ ፍጡራን መገለጫዎች ቢሆኑም ነገር ግን የአላህ መስሚያና መመልከቻ ከፍጡራኑ ጋር አይመሳሰልም፡፡ በመስሚያና በመመልከቻ አምሳያ እንደሌለው ሁሉ በሌሎችም ባህሪያቱ አምሳያ የለውም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

*"አላህ የዛችን በባሏ ነገር የምትከራከርህንና ወደ አላህ ሰሞታ የምታሰማውን (ሴት) ቃል በእርግጥ ሰማ። አላህም በንግግር መመላለሳችሁን ይሰማል። አላህ ሰሚ ተመልካች ነውና" (አል ሙጃደላህ 1)*

ኢብኑ ከሢር ይህን አንቀፅ ለማብራራት ከቡኻሪና ከአህመድ የተዘገበውን የዓኢሻ ሀዲስ ጠቅሰዋል፡፡ ዓኢሻ እንዲህ ብለዋል "መስሚያው ድምፆችን ሁሉ ያካለለ የሆነው ጌታ ምስጋና ይገባው፡፡ ተከራካሪዋ ከነብዩ ጋር ስትነጋገር አቅራቢያዋ ሆኜ መስማት ተሳነኝ አላህ ግን ሰምቶ ይህን አንቀፅ አወረደ፡፡"

### ሁለተኛው መርህ

**አላህ ራሱን በሰየመባቸው ስሞችና በገለፀባቸው ባህሪዎች፤ እንዲሁም መልዕክተኛው ﷺ አላህን በሰየሙባቸው ስሞችና በገለፁባቸው ባህሪዎች፤ ከአላህ ታላቅነትና ልዕልና ጋር በሚሄድ መልኩ ማመን፡፡**

**የአላህን ባህሪዎች ምንነትና ሁኔታ አይነቶችን ለማወቅ መጣር ከግድግዳ በስተጀርባ ያለን ነገር ለማየት ወይም በጣም ሩቅ የሆነን ድምፅ ለመስማት እንደመሞከር ነው፡፡**

### ሦስተኛው መርህ

**ፍጡራን የአላህን ባህሪዎች «ከይፊያ» ማወቅ ስለማይቻሉ፤ ይህንን ለማወቅ የሚኖርን ውስጣዊ ጉጉትና መቋመጥ መግታት፡፡**

ለዚህ መርህ ማስረጃ ከሚሆኑት ውስጥ የሚከተለው የአላህ ቃል አንዱ ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

*«በስተፊታቸው ያለውን በስተኋላቸውም ያለውን ሁሉ ያውቃል፡፡ በእርሱም ዕውቀትን አያካብቡም፤ (ሙሉ በሙሉ አያውቁትም) ፡፡» (ጣሀ 110)*

የሚከተለው የአላህ ቃልም ሌላው ማስረጃ ነው፡-

*‹‹ዓይኖች አያዳርሱትም፤ እርሱ ግን ዓይኖችን ያዳርሳል» (አል አንዓም 103)*

አንዳንድ ዑለማዎች ይህን አንቀፅ ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ ‹‹ይህ የሚጠቁመው የእርሱን ታላቅነትና ከሁሉም የበላይ መሆኑን ነው፡፡ ከታላቅነቱ የተነሳ እርሱን አካብቦ ማዳረስ አይቻልም፡፡ ማዳረስ ወይም በዕውቀት ማካበብ ማለት ከማየት ያለፈ ነገር ነው፡፡ ጌታ የትንሳኤ ዕለት ይታያል፤ ነገር ግን በዕይታ አይዳረስም፤ ልክ አላህን በስሞቹና በባህሪያቱ ማወቅ እንደሚቻል፤ ሆኖም ግን፤ አላህን ሙሉ በሙሉ አካልሎ ማወቅ እንደማይቻለው ማለት ነው፡፡››

አስተዋይ ሰው አዕምሮ መሻገር የማይችለው ድንበርና ዓይንም ይሁን ጆሮ ማለፍ የማይችሉት ገደብ እንዳላቸው ሊገነዘብ ይገባል፡፡ የአላህን ባህሪዎች ምንነትና ሁኔታ አይነቶችን ለማወቅ መጣር ከግድግዳ በስተጀርባ ያለን ነገር ለማየት ወይም በጣም ሩቅ የሆነን ድምፅ ለመስማት እንደመሞከር ነው፡፡

ለምሳሌ፤ «አላህ ከዓርሽ በላይ ነው» ስንል የተነገረንን ተቀብለን እና አጽድቀን ከማለፍ ውጭ የአላህ ከዓርሽ በላይ መሆን "ኢስቲዋዕ" ማለት እንዲህ ነው ወይም እንዲያ ነው በሚል ስለሁኔታው "ከይፊያ" የሚሰጥ አስተያየት አይኖረንም። ለኛ አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ አላህ በነገረን መልዕክተኛውም ﷺባስተማሩን ነበር። እነዚህን ሦስት መሠረቶች ያረጋገጠ በአላህ ስሞችና ባህሪዎች ትክክለኛ የሆነውንና ከጥንት ጀምሮ የኖሩ ታላላቅ የኢስላም ሊቃዉንት ያፀደቁትን እምነት አረጋግጧል ማለት ነው፡፡

## አምስቱ መሰረታዊ የሆኑ ህጎች

### የመጀመሪያው መሰረታዊ ህግ

**ስለ አላህ ባህሪዎች መናገር ስለ ተቀደሰው የአላህ "ዛት" እንደመናገር ነው (አንድ አይነት ናቸው)።**

ይህም ማለት፤ ሁሉም እንደሚስማማው አላህ ከማንም "ዛት" ጋር የማይመሳሰል "ዛት" አለው። ልክ እንደዚሁ በቁርአንና ሀዲስ የፀደቁ ባህሪያዎቹ የፍጡራን ባህሪዎችን አይመሳሰሉም፡፡ በመሆኑም የአላህ ዛትንና የአላህ ባህሪን ከፍጡራን ዛትና ባህሪ ጋር አለመመሳሰልን ይጋራሉ፡፡

ይህ መሠረት ዛትን እያፀደቁ ባህሪን የሚቃወሙ ሰዎችን ለማሳመን ወሳኝ ነጥብ ነው፡፡ ምክንያቱም ለአላህ ዛትን ማፅደቅ ሁሉም የሚስማማበት እና ውዝግብ የሌለበት ጉዳይ ነው። ይሁንና ማንም ሰው፤ "ፍጡራን ዛት ስላላቸው 'አላህ ዛት አለው' ማለት ማመሳሰል 'ተሽቢህ' ነው" ብሎ አያውቅም፡፡ ምክኒያቱም ዛት የሚለውን ደካማ ወደ ሆነው ሰው የተባለ ፍጡር ስናስጠጋውና ወደ ኃያሉና የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ወደሆነው አላህ ስናስጠጋው ፍጹም የተለየ መልዕክት እንዳለው ሁሉም ሰው ይገነዘባል።

ወደ ቀጣዩ ገጽ ዞሯል . . . . . . . . .

ካለፈው ገጽ የቀጠለ . . . . . . . . .

## ሁለተኛው መሰረታዊ ህግ

**ስለተወሰኑ የአላህ ባህሪዎች መናገር ስለሌሎቹ ባህሪዎች እንደመናገር ነው**

ባህሪዎችን በመቀበልም ይሁን ባለመቀበል ስለከፊል የአላህ ባህሪዎች መናገር ስለሌሎችም እንደመናገር ነው:: ይህ መሰረት ከፊል ባህሪዎችን አፅድቀው ሌሎችን የሚቃወሙ ቡድኖችን ግዴታ ውስጥ ያስገባል:: አንድ ሰው፤ ለአላህ መስማት “ሰምዕ” ፣መመልከት “በሰር”፣ ህያው መሆን “ሀያት” ፣ ዕውቀት “ዒልም”፣ ችሎታ ‘ቁድራህ’ እና ሌሎችንም ባህሪዎች አፅድቆ በትክክለኛ ትርጉሞቻቸው እየተረጎመ ሌሎች እንደ መውደድ “ሙሀባህ”፣መቆጣት “ገደብ”፣ እዝነት ‘ረህማህ’፣ ከዓርሽ በላይ መሆን ‘ኢስቲዋዕ’፣ እና የመሳሰሉትን ደግሞ ቀጥተኛ ትርጉሞቻቸውን የማይቀበል እና የማያጸድቃቸው ከሆነ፤ እርስ በእርስ የሚጋጩ ቀመሮችን ተጠቅሟልና ስህተት ውስጥ ነው። ይህንን ሰው እንዲህ ልናስረዳው እንችላለን፤ “ባፀደቅካቸውና በተቃወምካቸው ባህሪዎች መካከል ምንም ለውጥ የለም፤ ምክንያቱም ስለ አንዱ ባህሪ የምትናገረውን ስለሌላውም ልትናገረው ትችላለህ::

ህይወት፣ ዕውቀት፣ ችሎታ፣ መስማትና መመልከትን ስታጸድቅ በእነዚህ ባህሪዎች ከሚገለጹ ፍጡራን ባህሪዎች ጋር የማታመሳስል ከሆነ፤ ያስተባበልካቸውንም ባህሪዎች በዚሁ መልኩ ከፍጡራን ባህሪዎች ጋር ሳታመሳስል ማጽደቅ ትችላለህ። ይህንን የማታደርግ ከሆነ ግን አቋምህ የተምታታ ይሆናል።” ይህ መሰረታዊ ህግ እጅግ ጠቃሚ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።

## ሦስተኛው መሰረታዊ ህግ

**የስሞችና የቃላት መመሳሰል የይዘት መመሳሰልን ግድ አይልም**

አላህ በቁርዓን ላይ ራሱን ከሰየመባቸው ስሞች አንዳንዶቹን ባርያዎቹንም ገልጿል። ለምሳሌ፤ አላህ እራሱን ህያውነትን የሚያሳየውን “አል-ሀይ” የሚለውን ስያሜ ሰጥቷል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

*‹‹አላህ ከእርሱ በቀር በሀቅ የሚመለክ ሌላ አምላክ የለም:: ሕያው በራሱ የተብቃቃ ነው::›› (አል በቀራህ 255)*

ባሮቹንም እንዲሁ ህያውነትን በሚያሳየው ተመሳሳይ ቃል ገልጿቸዋል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

*‹‹ሕያውን ከሙት ያወጣል፤ ሙትንም ከሕያው አውጪ ነው::›› (አል አንዓም 95)*

ይሁንና ሁለቱ ህያውነቶች ግን ፍጹም ይለያያሉ። በተመሳሳይ መልኩ አላህ ለጀነት ሰዎች ስለተዘጋጁ ብዙ ጸጋዎች ነግሮናል። ለምሳሌ፤ ስለ መብሉና መጠጡ፤ በውስጧ ውኃ፤ ወተት፣ ማር፣ ስጋ፣ የተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ እና ሌሎችም ጸጋዎች ነግሮናል። ስለ ወንዞቿ፣ የመኖሪያ ህንጻዎቿ እና ሌሎችንም ነግሮናል። ነገር ግን ማንኛውም ሰው ይህንን ሲሰማ ዱንያ ላይ ካሉ ጸጋዎች ጋር ስማቸው ስለተመሳሰለ፤ ይህ መመሳሰል ደግሞ ጸጋነታቸውን ስለሚያጠፋ እነዚህን ነገሮች አልቀበልም አይልም። ስማቸው ስለተመሳሰለም ዱንያ ላይ ካሉ ጸጋዎች አይለዩምም አይልም።

ታላቁ ሰሀብይ ዐብዱላህ ኢብኑ ዓባስ እንዲህ ብለዋል፤

عن ابن عباس رضي الله عنهما قال: "ليس في الجنة شيء مما في الدنيا إلا الأسماء".

*‹‹ጀነት ውስጥ ዱንያ ላይ ካለው ነገር ምንም የለም፤ ከስም መመሳሰል በስተቀር»*

ይህ የስም መመሳሰል ሃሳብን ለመረዳት ከማገልገሉ ያለፈ ብዙ ትርጉም የለውም። በምድር ያሉ እና በጀነት ያሉ ጸጋዎች በስም አንድ ቢሆኑም ፍጹም የማይመሳሰሉ ከሆነ፤ በመካከላቸውም ያለዉን ልዩነት ከአላህ በስተቀር ማንም አያውቅም።

**ለአላህ የሚገቡ ባህሪዎች በአእምሮ በማሰላሰል የምንደርስባቸው ስላልሆኑ የአላህን ስሞችንና ባህሪዎችን በማፅደቅ ረገድ በቁርዓንና በሐዲስ ጥቅሶች ብቻ መገደብ የግድ ነው፡፡**

## አራተኛው መሰረታዊ ህግ

**ሁሉም የአላህ ስሞች እጅግ ያማሩ ውብ ናቸው**

አላህ እንዲህ ይላል፡-

*‹‹ለአላህም መልካም ስሞች አሉት:: ›› (አል አዕራፍ 180)*

በእነዚህ ስሞች የሚሰየመው ያማረውና የላቀው አላህ ስለሆነ፤ ስሞቹ የተሟሉና የተዋቡ፣ በምንም መልኩም ጉድለት የሌለባቸውና ጉድለትን የማይጠቁሙ ናቸው::

ለምሳሌ፡- “አል ሐይ” (ህያው) ከአላህ ስሞች ውስጥ አንዱ ሲሆን የሚያመለክተውም ሁልጊዜ ዘውታሪ የሆነውን እና ከዚህ ቀደምም ሆነ ወደፊት መወገድ የማይገጥመውን የተሟላ ህይወት ይጠቁማል::

ህይወት ደግሞ እንደ ዕውቀት፣ ችሎታ፣ መስማትና መመልከት የመሳሰሉትን የተሟሉ ባህሪዎች ያካትታል::

## አምስተኛው መሰረታዊ ህግ

**የአላህን ስሞችና ባህሪያዎች ያለማስረጃ ማፅደቅ አይፈቀድም**

አህሉሱና ወልጀማዓህ፤ አላህ እርሱን የሰየመባቸውን በቁርዓንና በሱና የተረጋገጡ ስያሜዎች እና ባህሪዎች ሁሉ ይቀበላሉ። የአላህን ስሞችና ባህሪዎች “ተውቂፊይ” ናቸውና ያለማስረጃ ማጽደቅ አይፈቀድም። በሰዎች አስተያየት የማይጸድቁና የማይሻሩ በመሆናቸው ምንም ሳይጨመርና ሳይቀነስ በቁርአን ወይም በሀዲስ በተረጋገጡት ስሞችና ባህሪዎች ብቻ ማመን ግዴታ ይሆናል::

ለአላህ የሚገቡ ባህሪዎች በአእምሮ በማሰላሰል የምንደርስባቸው ስላልሆኑ የአላህን ስሞችንና ባህሪዎችን በማፅደቅ ረገድ በቁርዓንና በሐዲስ ጥቅሶች ብቻ መገደብ የግድ ነው:: ማንም ሰው መረጃን ሳይከተል “ይህ የአላህ ስም ነው” ወይም “ይህ የአላህ ስም አይደለም” ማለት አይችልም። ይህ ስለ አላህ የማያውቁትን መናገር አላህ ከሽርክ ጋር አቆራኝቶ የጠቀሰው ከባድ ወንጀል ነው።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿قُلْ إِنَّمَا حَرَّمَ رَبِّيَ الْفَوَاحِشَ مَا ظَهَرَ مِنْهَا وَمَا بَطَنَ وَالْإِثْمَ وَالْبَغْيَ بِغَيْرِ الْحَقِّ وَأَنْ تُشْرِكُوا بِاللَّهِ مَا لَمْ يُنَزِّلْ بِهِ سُلْطَانًا وَأَنْ تَقُولُوا عَلَى اللَّهِ مَا لَا تَعْلَمُونَ﴾ الأعراف:33

*«ጌታዬ እርም ያደረገው መጥፎ ሥራዎችን፣ ከርሷ የተገለጸውንና የተደበቀውን ሀጢኣትንም፣ ያላግባብ መበደልንም፣ በርሱም ማስረጃ ያላወረደበትን በአላህ ማጋራታችሁን፣ በአላህም ላይ የማታውቁትን መናገራችሁን ብቻ ነው» በላቸው::»* (አል አዕራፍ 33)

በሌላም አንቀጽ እንዲህ ይላል፡-

*‹‹(የሰው ልጅ) መስሚያ፣ ማያም፣ ልብም እነዚህ ሁሉ (ባለቤታቸው) ከእነሱ ተጠያቂ ነውና፤ ለአንተም በርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር አትከተል::››* (አል ኢስራእ 36)

ይህ አቋም የታላላቅ የኢስላም መሪዎች አቋም ነው:: አንድን ነገር አውቀነው ልንገልፀው ይቻለን ዘንድ ሦስት መንገዶች አሉ::

- ያንን ነገር በማየት ስለእርሱ ማወቅ፤
- አምሳያውን በመመልከት ስለእርሱ ማወቅ፤
- እርሱን ከሚያውቀው አካል ትክክለኛ መረጃን በመውሰድ ስለእርሱ ማወቅ፤

ጌታችን አላህን ስላላየነው፤ አምሳያም ስለሌለው፤ ስለ ባህሪዎቹ ያለን ዕውቀት በሦስተኛው መንገድ ላይ ብቻ የተገደበ ነው። ስለ አላህ ባህሪዎች ከማንም ይበልጥ የሚያውቀው አላህ ራሱ ነው። ከአላህ ቀጥሎ ደግሞ በወህይ ያስተማራቸው የአላህ መልዕክተኛ ናቸው። ስለዚህም፤ አላህ የሚገለፀባቸውን ስሞችና ባህሪዎች የምናውቀው ከአላህና ከመልዕክተኛው ንግግር ብቻ ነው።

-----------**********-----------

# አቡበክር አስሲዲቅ ؓ

✍ ኑርሁሴን ጋሹ (ኑጋ)

አሰላሙ አለይኩም ወረህመቱላሂ ወበረካቱሁ ውድ የነሲሓ መጽሔት ታዳሚያን! ባለፈው እትም ስለ ሰሓቦች ልቅናና ደረጃ፣ ልንሰጣቸው ስለሚገባው ክብር እንዲሁም እነሱን አሳንሶ መመልከትና ክብራቸውን በየትኛውም መልኩ መዳፈር ያለውን ከባድ አደጋ አይተን ነበር።

በዛሬው ፅሁፌ ደግሞ ከነዚሁ ብርቅዬ ትውልዶች ውስጥ ታላቁን ሰው፣ የዚህን ኡመት በላጭ፣ የነብዩን ﷺየቅርብ ወዳጅና ምትክ የነበረውን ታላቅ ሰሓብይ ይዤላችሁ ቀርቤያለሁ። እነሆ እርሱም አሚሩል ሙእሚኒን ወኸሊፈቱ ረሱሊላህ ﷺአቡበክር አስሲዲቅ ነው።

ዓኢሻ ؓ እንዳወሩት ነብዩ ﷺወደ መስጂደል አቅሷ የሌሊት ጉዞ (ኢስራእ) ባደረጉ ዕለት ሰዎች በጉዳዩ ላይ ይነጋገሩ ጀመር፤ ወሬውንም ወደ አቡበክር ؓ ይዘው በመምጣት *“ታያለህ! ጓደኛህ ሌሊቱን ወደ በይተል መቅዲስ ደርሼ መጣሁ ብሎ ይሞግታል”* አሉት፤ አቡበክርም ؓ *“በእርግጥ እንዲህ አለን?”* ሲል መልሶ ጠየቃቸው፤ *“አዎን”* አሉት፤ “ብሎት ከሆነ በእርግጥ እውነቱን ነው!” በማለት በነብዩ ﷺያለውን ሙሉ እምነት አስረግጦ አስመሰከረ። ሰዎቹም በዚህ ሳያበቁ “ሌሊቱ ሳይነጋ ሄጄ ተመለስኩ እያለም ታምነዋለህን?” በማለት እምነቱን መፈታተን ቀጠሉ፤ አቡበክር ؓ የሰጣቸው ምላሽ ግን የእርሱን ብስለት፣ የአስተሳሰብ ምጥቀትና የእምነት ጽናት ያሳየ፤ በአንጻሩ የነርሱን የአስተሳሰብ ድክመትና የአምላክ ሁሉን ቻይነትን አለመገንዘብ ያሳየ ነበር። “ከዚህ ከምትሉት ሩቅ በሆነ ነገርም አምኜዋለሁ! በቀንና በሌሊት ከሰማይ መልዕክት እንደሚመጣለት አምኜ ተቀብዬዋለሁ!” በማለት መለሰላቸው። (ሲልሲለቱ አስሰሒሓ 306) ይህ ነው አቡበክር አስሲዲቅ ؓ ፤ መልዕክተኛውን ﷺበሁሉ ነገር እውነተኛ መሆናቸውን የመሰከረ ፤ የዚህ ዑመት በላጭና ምርጥ ሰው! አላህም عز وجل በዚህ እውነት ባይነቱ በቁርአን ውስጥ አወድሶታል፡-

*{የ በእውነት የመጣውና እርሱንም እውነት ያለው፤ እነዚህ በእርግጥ አላህን ፈሪዎች ናቸው።}(አዝ ዙመር 33)*

“በእውነት የመጣው” የተባሉት መልዕክተኛው ﷺ ሲሆኑ “እርሱንም እውነት ያለው “ የተባለው አቡበክር አሲዲቅ ؓ ነው። አቡበክር አስሲዲቅ የሰሓቦች ሁሉ በላጭና ምርጡ ነው። ዑመር ؓ *“አንተ ሰይዳችን (በላጫችን) እና ከመካከላችን ምርጡ ነህ፤ መልዕክተኛው ﷺዘንድም ከኛ በላይ ተወዳጁ ነህ”* ብሎታል (ቡኻሪ)። አቡበክር ؓ ከወንዶች ሁሉ መጀመሪያ እስልምናን የተቀበለ ሲሆን ገንዘቡን በአላህ መንገድ አብዝቶም ያወጣ ነበር። ጀግና ከተባሉ ሰሓቦችም ነው፤ ፍልሚያው በተጋጋለበት ጦርነት ወቅት ብርቱ እንደነበረ ታሪክ የዘገበለት ጀግና ነው። ወህይን ይጽፉ ከነበሩ ሰሓቦችም አንዱ ነው። ቁርአንን በአንድ ጥራዝ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲሰበሰብ ያዘዘውም እርሱ ነው፤ ጀነት ከተመሰከረላቸው አስሩ ሰሓቦች የመጀመሪያው ነው፤ ነብዩ ﷺዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ የነበረውም እርሱ ነው፤ መልዕክተኛው ﷺዘንድ የነበረውን ቦታ ያህል ማንም አልነበረውም። ኢብኑ ዑመር ؓ እንዳሉት *“ነብዩ በመካከላችን በነበሩበት ዘመን (ነብዩ ﷺዘንድ) አንዳችንም የአቡበክርን ያህል አንሆንም ነበር”* ብሏል (ቡኻሪ)።

**ነብዩ በመካከላችን በነበሩበት ዘመን (ነብዩ ﷺዘንድ) አንዳችንም የአቡበክርን ያህል አንሆንም ነበር”**

ልክ ነው!! ልቡ ለነብዩ ልብ ቅርብ የነበረና ንግግሩ የመልክተኛውን ንግግር የሚገጥም ሰሓባ ነበር፤ ለዚህም ነው ነብዩ “ﷺ*ከኡመቴ ወዳጅ (ኸሊል) መያዝ ቢፈቀድልኝ ኖሮ አቡበክርን ባደረግኩት ነበር”* ሲሉ የተደመጡት (ቡኻሪ)። ከመካ ወደ መዲና በተሰደዱ ጊዜም ነብዩ ﷺየጉዞ ጓደኛቸው ይሆን ዘንድ የመረጡት ብቸኛው ሰሓባ አቡበክር ؓ ነበር።

አላህም عز وجل ይህን የሁለቱን የስደት ጉዞ ዘወትር ይወሳ ዘንድ በቁርአኑ አኖረው።

*{የሁለት ሰዎች ሁለተኛ ሆኖ (መልዕክተኛው ሲሰደድ) በዋሻ ውስጥ ሆነው ሳለ! (መልዕክተኛውም (ﷺለጓደኛው (አቡበክር) “አትዘን አላህ ከኛ ጋር ነውና!” ባለው ጊዜ .....}* (አት ተውባህ 40)

አቡበክር አስሲዲቅ ؓ መልዕክተኛውን ﷺ ከራሱና ከልጆቹ በላይ ይወዳቸው ነበር፤ መልዕክተኛውም ﷺለስደቱ ጉዞ እርሱን በመረጡት ጊዜ ማንም ያላገኘውን እድል ባለቤት መሆኑን አረጋገጠ። በጉዞ ላይ ሳሉ አንዳንዴ ከመልዕክተኛው ፊትፊት አንዳንዴ ከኋላ በመሆን ይጓዝ ነበር፤ መልዕክተኛውም ﷺጠየቁት *“አቡበክር ሆይ ስለምን አንዳንዴ ከፊቴ አንዳንዴ ከኋላዬ ሆነህ ትጓዛለህ?”* እርሱም *“የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ! ከኋላችን እንደሚከተሉን ሳስብ ከኋላዎት እሆናለሁ፤ መንገዱን ሳስብ ደግሞ ከፊቶት ሆኜ እሄዳለሁ”* በማለት መለሰ ። ነብዩም“ ﷺ *አቡበክር ሆይ! አንዳች ነገር ቢመጣ እኔን ከሚነካኝ አንተን ቢያገኝህ ትወዳለህን?”* ሲሉ ጠየቁት *“አዎን ያ ረሱለሏህ! በእውነት በላከዎት ጌታ ይሁንብኝ አንዲትም ነገር ብትሆን እርስዎን ከምትነካ እኔን ብታገኘኝ እመርጣለሁ!”* በማለት መለሰ። *ዋሻው ዘንድ በደረሱ ጊዜም አቡበክር መልዕክተኛውን“ ﷺ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ይቆዩኝ! ዋሻው (ከአውሬ) ነጻ መሆኑን አረጋግጬ ልመለስ”* በማለት አረጋግጦ መልዕክተኛውን ወደ ዋሻው አስገባቸው። (አልሙስተድረክ) ሰለሏሁ አላ ሙሐመድ ወረዲየ ዐን አቢበክር!! በመጨረሻም የዚህን ድንቅ ስብዕና ባለቤት ከመልዕክተኛው ﷺጋር ያሳለፉትን አንዲት ክስተት በማስታወስ ጽሁፌን ላገባድድ። በእርግጥም አቡበክር ؓ በኸይር ሥራ ተሽቀዳዳሚ ወደ ጀነት የሚያስገቡ ሥራዎችን በመሥራት አቻ የሌለው ሰሓባ ነበር። ከዕለታት በአንዱ ቀን መልዕክተኛው ﷺሰሓቦችን ጠየቁ፡- *“ከናንተ ውስጥ ዛሬ የጾመ ማን ነው ?”* ከሰሓቦች መካከልም አቡበክር ؓ *“እኔ!”* በማለት መለሰ። ቀጥለውም *“ዛሬ ጀናዛ የሸኘ ከናንተ ውስጥ ማን ነው?”* አሁንም አቡበክር ؓ *“እኔ!” “ከናንተ ውስጥ የተራበን ምስኪን ያበላ ማን ነው?”* አሁንም ከመካከላቸው አቡበክር ؓ *“እኔ”! “ከናንተ ውስጥ ዛሬ የታመመን ሰው የጠየቀ ማን ነው?”* አሁንም ብቸኛው ሰው እርሱ ነበር *“እኔ!”* አለ። መልዕክተኛውም“ ﷺ*እነዚህ ነገሮች በአንድ ሰው ላይ አይገኙም ጀነት ቢገባ እንጂ!!”* በማለት መሰከሩለት (ሙስሊም)።

ይህ የነብዩ ﷺ ወዳጅና ጓድ ከመልዕክተኛው ﷺ ጋር የነበረው ቆይታ በአንድ ጽሁፍ የሚገባደድ አይደለም። ይልቁንም ታሪኩ ከመልዕክተኛው ﷺ ጎን እስከተቀበረበትና ከሞታቸው በኋላም የሁለቱ ጓደኝነት እስከቀጠለበት ዕለት ድረስ ቢዘረዘር የማያልቅ ቢሆን እንጂ ! በጀነትም ጉርብትናቸው ይቀጥላል ኢን ሻአ አላህ! መልዕክተኛው ﷺ*ሰው ከሚወደው ጋር ነው”* ብለዋልና! በቀጣይ ፅሁፍ የዚህን ታላቅ ሰው የኸሊፋነት ዘመንና በዘመኑ የተከሰቱ ታላላቅ ክስተቶችን እንዳስሳለን እስከዛው ድረስ ሰላም ቆዩልኝ።

ምንጭ ፡- “ሁቅባህ ሚን አት-ታሪኽ” ሸይኽ ዑሥማን አል ኸሚስ

------------*********------------

ቅጽ 1 ቁጥር 2 | ግንቦት 2011

# አል ዐፊያ

ዶ/ር ዐብዱልከሪም ግርማ

## የህፃናት አመጋገብ

ባሳለፍነው እትም የጤና አምዳችን ላይ እንዳወሳነው አንድ ህፃን ልጅ የእናት ጡት ወተት ብቻ እስከ ስድስት ወር ሊያገኝ እንደሚገባ አውስተን ነበር። ከስድስት ወር ጀምሮ ግን ቀስ በቀስ ተጨማሪ ምግቦችን መውሰድ ይኖርበታል። ይህም የህፃኑ የእድገት ፍላጎት በእናት ጡት ወተት ብቻ ስለማይሟላ ነው። በተጨማሪም አንድ ህፃን አንድ ዓመት ሲሞላው ከሰውነቱ ሀይል ግማሽ ያህሉን ከምግብ ማግኘት ስለሚኖርበት ነው።

ህፃኑን ምግብ ለማስጀመር የተሻለው አማራጭ ስድስት ወር ሲሆን ባደጉት ሀገራት የሚኖሩ ህፃናት ለኢንፌክሽን የመጋለጥ እድላቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ከአራት ወር ጀምሮ ምግብ ሊጀምሩ ይችላሉ። እንደኛ ሀገር ባሉ ታዳጊ ሀገራት ሁኔታ ግን ህፃናቱን ከኢንፌክሽን ለመከላከል የተሻለው አማራጭ ከስድስት ወር እንዲጀምሩ ማድረግ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ።

ህፃናት ምግብን ሲጀምሩ በፈሳሽ መልክ በተዘጋጁ ምግቦች ቢጀምሩ ይመከራል። ይህም ምግቦቹን በቀላሉ ለመዋጥ እንዲቻላቸው እና በትንታ እና መሰል ችግሮች እንዳይጎዱ ያደርጋል። ከፈሳሽ ምግቦች በመቀጠል ግማሽ ፈሳሽ ወይም በወፍራሙ በውሀ የተለወሱ ምግቦችን በማላመድ ወደ ጠጣር ምግቦች መውሰድ ይቻላል። ሆኖም ጠጣር ምግቦችን የሚወስዱ ህፃናት ቢያንስ በትክክል መቀመጥ የሚችሉና አንገታቸውን በአግባቡ መቆጣጠር የሚችሉ መሆን አለባቸው። አንገታቸውን በትክክል መቆጣጠራቸው የአየር እና የምግብ ቧንቧቸው በአግባቡ እንዲለይ ስለሚያደርግ ከትንታ ይታደጋቸዋል።

ህፃናት ምግብ ሲጀምሩ በቅድሚያ ከጥራጥሬ አይነቶች እና ከተፈጨ ስጋ ቢጀምሩ ይመከራል። ይህ አይረን እና ዚንክ የተባሉ ንጥረ ነገሮችን እንዲያገኙ ስለሚረዳቸው ተቅማጥና ደም ማነስን ሰውነታቸው እንዲከላከል ይረዳል። በመቀጠል ወደ አትክልትና ፍራፍሬ መውሰድ ይቻላል። ምን ጊዜም ህፃናት የሚመገቡት ምግብ ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ ቫይታሚን ሲ ያለው ቢሆን ይመረጣል። ህፃናት የሚያገኙት አንድ አራተኛ ወይም ሩብ ኃይል ስብ ነክ ከሆኑ ምግቦች እንዲሆን ይመከራል። በመሆኑም እንደ እንቁላልና ስጋ ያሉ ስብ ነክ ምግቦችን እንዳይመገቡ መከልከል የለብንም።

አጀማመራቸውን በተመለከተ ህፃናት እያንዳንዱን አይነት ምግብ ለየብቻ ቢቀምሱና ለ15 ጊዜ ወይም ከ3 እስከ 5 ቀን ቢደጋግሙት ይመረጣል። ይህም የምግብ አይነቱን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚቀበለው ሰውነታቸው ለቀጣይ ህይወቱ ምግቡን እንዲወደውና እንዲላመደው ያደርጋል። በሌላ በኩል ሰውነታቸው የማይስማማውና አለርጂ የሆነው ምግብ የትኛው እንደሆነ ለመለየት ያመቻል። ይህ ካልተቻለ ግን በጥቅሉ የጥራጥሬ ምግቦችን በማስቀደም ሌሎች አይነቶችን እያስከተልን መመገብ እንችላለን።

የህፃናት ምግቦች ላይ ጨው እና ስኳርን ማድረግ አይመከርም። ጨው እና ስኳር በባህሪያቸው ምግቦችን ስለሚያጣፍጡ የህፃናቱን የምግብ ጣዕም ልኬት በማዛባት የሚጣፍጥ ካልሆነ ሌሎች ምግቦችን እንዳይበሉ ያግዳቸዋል። በዚህም የተለያዩ አይነት ምግቦችን እንዳይወስዱ የጣዕም ልኬታቸውን ከፍ በማድረግ ይከላከላቸዋል። ከዚህም በላይ በቀሪው ዕድሜያቸው የምግብ ጣዕም ልኬታቸው እንደተዛባ እንዲቀር ያደርጋቸዋል።

**ህፃናት ምግብን ሲጀምሩ በፈሳሽ መልክ በተዘጋጁ ምግቦች ቢጀምሩ ይመከራል ። ይህም ምግቦቹን በቀላሉ ለመዋጥ እንዲቻላቸው እና በትንታ እና መሰል ችግሮች እንዳይጎዱ ያደርጋል ።**

ህፃናት ምግብ ጀመሩ ማለት ጡት ያቆሙ ማለት አይደለም። ከላይ እንደጠቀስነው ህፃናት በአንድ ዓመታቸው ግማሽ የሰውነት ሀይላቸውን ከምግብ ቀሪውን ግን ከጡት ማግኘት ይኖርባቸዋል።

ህፃናት የንግግር ችሎታቸው እንዲዳብር ምግቦችን ሲወስዱ በማንኪያ እንዲመገቡ ማድረግ ይመከራል። ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ጠንካራና ጥሬ የሆኑ ምግቦች ለመታነቅ እና ትንታ ስለሚያጋልጣቸው እንዳይወስዱ ይመከራል። እንደዚሁ ማር ከሱ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ኢንፌክሽን ስላለ ከአንድ ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት አይመከርም።

በአላህ ፈቃድ በቀጣይ እስክንገናኝ ሰላም

------------*********------------

## የቁርኣንና የተውሒድ ቁርኝት

አቡ ፈውዛን አሕመድ

ብቸኛው አምላካችን አላህን ያለ ምንም አጋር ማምለክ ወይም በሌላ አገላለፅ ፈጣሪያችንን ከፍጡራን ነጥሎ እሱን ብቻ መገዛት በአጭሩ ሲነገር ተውሒድ አል ዒባዳ ወይም አህዳዊ አምልኮ በመባል ይገለፃል።

ዒባዳ ወይም አምልኮ በበርካታ መንገድ ይገለፃል። እንደምሳሌነት በስግደት፣ በልመና፣ በስዕለት ወይም ነዝር፣ በቁርባን ወይም እርድ፣ በስጋት ወይም ፍራቻ፣ በክጃሎት ወይም ተስፋ ማድረግ፣ በፍቅርና በመታዘዝ እና በመሳሰሉት በርካታ መንገዶች የሚፈፀም ነው። ታዲያ ከነዚህ በአንዱም ቢሆን ለፈጣሪ ብቻ ተገቢ በሆነ መልኩ ለፍጡራን ኣለማድረግን ያቀፈ መገለጫዎች ኣሉት።

ይህ ርዕስ ማብራርያ እንደሚያስፈልገው የታወቀ ጉዳይ ነው። ከዚያ በማስቀደም ግን በቀጥታ በቁርኣን ሆነ በሀዲስ የተሰመረበትና ትኩረት የተሰጠበት መሆኑን ከሚያሳይ የሰለፎች ንግግር መካከል የኢብኑል ቀይዩም ረሂመሁላህን ላካፍላችሁ።

«የቁርኣን አንቀፆች በሙሉ ተውሒድን ያቀፉ፣ ያጎሉና ወደዚያ ጥሪ ያደረጉ ናቸው። ቁርኣን ስለ አላህ ስሞች፣ ባህሪዎችና ተግባራት የሚነግረን ዕውቀታዊ መረጃ ሰጪ የሆነ የተውሒድ ክፍል ነው።

ቁርኣን ያለ ምንም አጋር አላህን ብቻ እንድናመልከውና ከሱ ውጭ ያሉትን አማልክት ሁሉ እንድንርቅ ጥሪ የሚያደርግልንና ፍላጎታችንን የምናንፀባርቅበት የተውሒድ ክፍልም ነው። ቁርኣን ትዕዛዝና ክልከላን የሚያንፀባርቅ የከለከለንን በመተው ሆነ ያዘዘንን በመፈፀም ረገድ አስገዳጅ የሆነ መመርያና የተውሒድን ሀቆችና ማሟያዎች እንድንፈፅም የሚመክረን መርህ ነው።

ቁርኣን አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ ተውሒድን ላነገቡና መመርያውን ለሚታዘዙ ሰዎች በዱንያ ላይ እና በመጨረሻው ዓለም የሚያደርግላቸውን ክብር በተመለከተ ስለ ተውሒድ ሰዎች ምንዳ የሚነግረን የመረጃ ክፍል ነው። ቁርኣን ሽርክ ላይ በመዘፈቅ ከተውሒድ አንጋቢነት ውጭ የሆኑ ሰዎችን በተመለከተ በዱንያ ሳሉ ከቅጣቱ የሚያቀምሳቸውን እንዲሁም በመጨረሻዋ ዓለም ስለ ደገሰላቸው የስቃይ ሁኔታ የሚያሳውቀን የመረጃ ክፍል ነው።»

مدارج السالكين 3 / 450

ባጠቃላይ «ቁርኣን ሙሉ በሙሉ ስለ ተውሒድና መብቶቹ ብሎም ስለሚገኝበት ምንዳ እንዲሁም ስለ ባዕድ አምልኮ ምንነት፣ ስለ አጋሪያኑና ምንዳቸው ሁኔታ ሁሉ የሚያሳውቀን የመመርያ መጽሐፍ ነው።»

مدارج السالكين 3 / 450

------------*********------------

# ፈታዋ

## ቀደምት አበዎች (ሰለፎች) ቁርኣንን አስመልክተ ያላቸው እምነት

ጥያቄ 60/ የተከበሩ ሸይኽ! ሰለፎች ቁርኣንን አስመልክቶ ያላቸው እምነት ምንድን ነው?

መልስ 60/ ሰለፎች ቁርኣንን አስመልክቶ ያላቸው እምነት ልክ እንደ ተቀሩት የአላህ ባህሪዎች እና ስሞች ነው። እምነታቸውም በቁርኣንና በመልዕክተኛው ﷺ

ሐዲስ ላይ የተመሰረተ ነው። ሁላችንም እንደምናውቀው ቁርኣንን አላህ ቃሉ ወይም ንግግሩ እንደሆነ ገልፆታል። ከርሱም ዘንድ የተወረደ ነው። ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይላል፡-

*“ከአጋሪዎችም አንዱ ጥገኝነትን ቢጠይቅ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው፡፡ ከዚያም ወደ መጠበቂያው ስፍራ አድርሰው፡፡” [አተውባ :6]*

“የአላህ ቃል” የሚለው ያለምንም ጥርጥር የተከበረው ቁርኣን ነው የተፈለገበት።

እንዲህም ይላል፡-

*“ይህ ቁርኣን በእስራኤል ልጆች ላይ የእነዚያን እነርሱ በእርሱ የሚለያዩበትን አብዛኛውን ይነግራል፡፡”*

[አን ነምል፡76]

ቁርኣን ቃሉም ትርጉም የአላህ ነው። በሐቂቃው ተናግሮበታል። ለታማኙ ጂብሪል ምላሱ ላይ አደረገለት። ጂብሪል ደግሞ ግልፅ በሆነ ዓረብኛ ቋንቋ ዓለማትን ያስጠነቅቅ ዘንድ በመልዕክተኛው ﷺ

ቀልብ ላይ አወረደው። ሰለፎች ቁርኣን ከአላህ ዘንድ በሃያ ሦስት ዓመት ውስጥ የርሱ ጥበብ እንደሚያስፈረደው ተከፋፍሎ እንደወረደ ያምናሉ።

ከዚያም በመቀጠል ቁርኣን በሰበብና ያለሰበብ ይወርዳል። ይህም ማለት አንዳንድ የቁርኣን አንቀፆች ወይም ሱራዎች እንዲወርዱ የሚያደርጋቸው ሰበቦች ይኖራሉ። ሌሎቹ ደግሞ ያለምንም ሰበብ ይወርዳሉ። አንዳንዱ ደግሞ መልዕክተኛውና ባልደረቦቻቸው ከኖሩበት ዘመን ቀደም ብሎ ያለውን የሚተርክ ይሆናል። አንዳንድ አንቀጾች ደግሞ ከጅማሪው የአላህን ህግጋት ሊያብራሩ ይወርዳሉ። ይህን አስመልክቶ የዕውቀት ባለቤቶች እንደጠቀሱት።

ሰለፎች ቁርኣን ጅምሩ ከአላህ ሲሆን ወደሱም ይመለሳል ይላሉ። ሰለፎች ቁርኣን ላይ ያላቸው እምነት ይህን ይመስላል።

አላህ ቁርኣኑን አስመልክቶ በከባባድ መገለጫዎች እንደገለፀው ከሁላችንም የሚሰወር አይደለም። ቁርኣኑ ሐኪም (ጥበበኛው)፣ ከሪም (ቸር)፣ መጂድ (የላቀው) ሲል ይገልፀዋል። በዚህ መልኩ ቃሉን አላህ ይገልፀዋል። ቁርኣንን አጥብቆ ካልያዘው ሰው ይልቅ በደንብ አጥብቆ ለያዘው፣ በመልዕክቱም ውጫዊና ውስጣዊ ተግባሩን በቁርኣን ያነፀ እነዚህ ባህሪያት ለርሱ የተገቡ ናቸው። ማለትም ልቅናን ፣ ታላቅነትን፣ ጥበብን፣ አሸናፊነትንና ስልጣንን አላህ ለርሱ ያደርግለታል።

ሙስሊሞች የአላህን ውዴታ እንዲያገኙ፣ የበላይነት፣ ደስታና ልቅና እንዲኖራቸው፣ በምዕራቡና በምሥራቁ ዓለም የበላይ እንዲሆኑ ስል በዚህ መድረክ መላው ሙስሊምን መሪም ሆነ ተማሪ፣ ዑለማም ሆነ ተራውንና ሰፊውን ማህበረሰብ ውስጣቸውንም ሆነ ውጫቸውን በቁርኣን በማነፅ ቁርኣንን አጥብቀው ይይዙ ዘንድ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

> **ቁርኣን ቃሉም ትርጉም የአላህ ነው ። በሐቂቃው ተናግሮታል ። ለታማኙ ጂብሪል ምላሱ ላይ አደረገለት ። ጂብሪል ደግሞ ግልፅ በሆነ ዐረብኛ ቋንቋ ዓለማትን ያስጠነቅቅ ዘንድ በመልዕክተኛው ﷺቀልብ ላይ አወረደው ።**

## ጉልህ የሆኑ የቁርአን ንባብ ደንቦችና ስርአቶች

ጥያቄ 61/ የተከበሩ ሸይኽ! ጉልህ የሆኑ የቁርኣን ንባብ ደንቦችና ስርኣቶች ምን ምንድን ናቸው?

መልስ 61/ ቁርኣንን የሚያነብ ሰው ከትልቁ (ጀናባ)ና ከትንሹ (ውዱን ከሚያበላሹ) ሐደስ ጠሃራ ሊሆን ይገባል። ጀናባ ላይ ሆኖ አንድ ሰው ቁርኣንን ማንበብ አይፈቀድለትም። በ ሐዲስ ላይ እንደመጣው ጁኑብ ላይ የሆነ ሰው እስኪታጠብ ቁርኣንን ማንበብ ይከለከላል። የወር አበባ ላይ ያለች ሴት ቁርኣንን ማንበብ ትችላለችን? የሚለውን ርእስ አስመልክቶ የዕውቀት ባለቤቶች የተለያየ አቋም አላቸው።

ሁለት የተለያየ አቋም ያሏቸው ሲሆን ከነሱም መካከል ቁርኣን መቅራት ትችላለች ያሉ አሉ። ምክንያቱም ቁርኣን መቅራቷን የሚከለክል ግልፅ የሆነ የሐዲስ ማስረጃ የለምና። በሸሪዓችን ደግሞ አንድ ሰው ከጅማሬው ጫንቃው ከግዴታ የጠራ ነው፤ አለማስገደድ፤ እንደገናም ባንድ ነገር ላይ አለመከልከል ነው መሰረቱ። አንዳንድ ዑለማዎች ደግሞ ሐይድ ላይ ሆኗ ቁርኣንን መቅራት አትችልም የሚል አመለካከት አላቸው። ምክንያቱም እንደ ጀናባ ትጥበት ይኖርበታል። እንዲሁም ሐይድ ላይ ያለችን ሴት ቁርኣንን መቅራት የሚከለክሉ ከመልዕክተኛው ﷺሐዲስ ተዘግበዋል። እኔ

በዚህ ላይ ያለኝ አቋም መቅራት ብቻ ከሆነ አላማዋ ባትቀራ ይሻላል ባይ ነኝ። ነገር ግን ቁርኣን ካልቀራሁ እረሳዋለሁ የሚል ስጋት ካላት አሊያም አስተማሪ በመሆኗ ቁርኣን ተማሪዎቿና ልጆቿን ለማስቀራት፣ወይም ተማሪ በመሆኗ ቁርኣን ማሰማት ካለባት እና ለመሳሰሉት ጉዳዮች መቅራቷ ችግር የለውም። በተጨማሪም እለታዊ አዝካር ውስጥ ለምሳሌ አያቱል ኩርሲይ ብትቀራ ችግር የለውም። ይህ አቋም ለሐቅ የቀረበ ነው የሚል እምነት አለኝ። በጥቅሉ ሐይድ ላይ ያለችን ሴት አስመልክቶ ቁርኣን መቅራቷ ወሳኝ ከሆነ መቅራት ይፈቀድላታል። ሆኖም መቅራቷ ወሳኝና አስፈላጊ ካልሆነ መቅራት የለባትም።

እንደዚሁም አንድ ቁርኣን የሚቀራ ሰው ቁርኣንን በሚያነብበት ጊዜ የሚያነበውን የቁርኣን የላቀ መልዕክት ይረዳ ዘንድ ልቡን ጥዶ ማንበብ ይጠበቅበታል። አንቀፆቹ በውስጣቸው የያዙዋቸውን መልዕክቶች ታሪኮች፣ ዜና እና ህግጋትን ሁሉንም በእኩል ማስተንተን ይኖርበታል። ምክንያቱም ቁርኣን የወረደው ለዚህ ጥበብ ነውና።

*“ (ይህ) ወዳንተ ያወረድነው ብሩክ መጽሐፍ ነው፡፡ አንቀጾቹን እንዲያስተነትኑና የአእምሮ ባለቤቶችም እንዲገሰጹ (አወረድነው)፡፡ “[ሷድ ፡29]*

የሰው ልጅ ልቡ ዝንጉ ሆኖና ልቡ ተጥዶ (እያስተነተነ) ቁርኣንን ሲያነብ በሁለቱ መሀከል ከፍተኛ ልዩነት ያስተውላል። ቁርኣንን በማስተንተንና በማስተዋል ሲቀራ ይበልጥ ተጠቃሚ ይሆናል። በዚህ መልኩ ቁርኣን ማንበብ ልቡ ውስጥ ጠንካራ ኢማን እና እርግጠኝነት፣ የአላህ መጽሐፍ በውስጡ የሚያካትታቸውን ህግጋት መፈፀምና መታዘዝ ላይ ጠንካራ ተፅእኖ ያሳድራል።

ቁርኣን ሲነበብ ሊጠበቁ ከሚገቡ ስርኣቶች መካከል፡- ሲነበብ በርጋታ ሊሆን ይገባል፣ አንዳንድ ፊደላት እስኪሳቱ ወይም ቃላቶች እስኪሰወሩ ድረስ በፍጥነት መቀራት አይኖርበትም። እንዲያውም በዝግታና በእርጋታ መቀራት አለበት። ነገር ግን ፊደላት ሳይጣሉ፣ ኢድጋም መደረግ የሌለበትን ኢድጋም ሳያደርጉ እና የመሳሰሉት ህግጋት ሳይጣሱ አንዳንዴ መፍጠን ችግር የለውም።

ምንጭ ፡ —

ነሲሓ የፈትዋ ማዕድ ድረገፅ ጥያቄ የሸይኽ ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አል ኡሰይሚን ፈትዋዎች ቁ.60 እና 61

http://www.nesiha.info

___________*********___________

# الأمر بالمعروف والنهي عن المنكر سفينة النجاة للمجتمع

الحمد لله والصلاة والسلام على رسول الله، أما بعد:

فإن من أهم الواجبات الإسلامية التي يترتب عليها صلاح المجتمع وسلامته ونجاته في الدنيا والآخرة، الأمر بالمعروف والنهي عن المنكر، وذلك هو سفينة النجاة، كما ثبت في صحيح البخاري عن النعمان بن بشير –رضي الله عنه– قال سمعت رسول الله ﷺ يقول: مثل القائم على حدود الله والواقع فيها كمثل قوم استهموا على سفينة، فأصاب بعضهم أعلاها وبعضهم أسفلها، فكان الذين في أسفلها إذا استقوا من الماء مروا على من فوقهم، فقالوا: لو أنا خرقنا من نصيبنا خرقًا ولم نؤذ من فوقنا قال النبيﷺ: فإن يتركوهم وما أرادوا هلكوا جميعًا، وإن أخذوا على أيديهم نجوا ونجوا جميعًا.

فتأمل أيها المسلم هذا المثل العظيم من سيد ولد آدم، ورسول رب العالمين، وأعلم الخلق بأحوال المجتمع وأسباب صلاحه وفساده، تجده واضح الدلالة على عظم شأن الأمر بالمعروف والنهي عن المنكر، وأنه سبيل النجاة، وطريق صلاح المجتمع، ويتضح من ذلك أيضًا أنه واجب على المسلمين وفرض عليهم القيام به؛ لأنه هو الوسيلة إلى سلامتهم من أسباب الهلاك، وقد أكثر الله سبحانه في كتابه الكريم من ذكر الأمر بالمعروف والنهي عن المنكر، وذكر أن أمة محمد ﷺ هي خير الأمم بسبب صفاتها الحميدة، التي من أهمها قيامها بالأمر بالمعروف والنهي عن المنكر، كما قال عز وجل: كُنْتُمْ خَيْرَ أُمَّةٍ أُخْرِجَتْ لِلنَّاسِ تَأْمُرُونَ بِالْمَعْرُوفِ وَتَنْهَوْنَ عَنِ الْمُنْكَرِ وَتُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ [آل عمران:110].

وتأمل أيها المسلم الذي يهمه دينه وصلاح مجتمعه كيف بدأ الله سبحانه في هذه الآية بذكر الأمر بالمعروف والنهي عن المنكر قبل الإيمان، مع كون الإيمان شرطا لصحة جميع العبادات يتبين لك عظم شأن هذا الواجب، وأنه سبحانه إنما قدم ذكره لما يترتب عليه من الصلاح العام.

وقال عز وجل: وَالْمُؤْمِنُونَ وَالْمُؤْمِنَاتُ بَعْضُهُمْ أَوْلِيَاءُ بَعْضٍ يَأْمُرُونَ بِالْمَعْرُوفِ وَيَنْهَوْنَ عَنِ الْمُنْكَرِ وَيُقِيمُونَ الصَّلاةَ وَيُؤْتُونَ الزَّكَاةَ وَيُطِيعُونَ اللَّهَ وَرَسُولَهُ أُولَئِكَ سَيَرْحَمُهُمُ اللَّهُ إِنَّ اللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٌ [التوبة:71].

فانظر يا أخي كيف بدأ في هذه الآية بذكر الأمر بالمعروف والنهي عن المنكر قبل الصلاة والزكاة، وما ذاك إلا لما تقدم بيانه من عظم شأنه وعموم منفعته وتأثيره في المجتمع، وتدل الآية أيضًا على أن الأمر بالمعروف والنهي عن المنكر من أخص أخلاق المؤمنين والمؤمنات، وصفاتهم الواجبة التي لا يجوز لهم التخلي عنها أو التساهل بها، والآيات في هذا المعنى كثيرة.

وقد ذم الله سبحانه من ترك هذا الواجب من كفار بني إسرائيل ولعنهم على ذلك، فقال سبحانه في كتابه المبين من سورة المائدة: لُعِنَ الَّذِينَ كَفَرُوا مِنْ بَنِي إِسْرَائِيلَ عَلَى لِسَانِ دَاوُدَ وَعِيسَى ابْنِ مَرْيَمَ ذَلِكَ بِمَا عَصَوْا وَكَانُوا يَعْتَدُونَ ۝ كَانُوا لا يَتَنَاهَوْنَ عَنْ مُنْكَرٍ فَعَلُوهُ لَبِئْسَ مَا كَانُوا يَفْعَلُونَ [المائدة:78، 79] وفي هذه الآية إرشاد من الله سبحانه لأمة محمد ﷺ إلى أن سبب لعن كفار بني إسرائيل وذمهم هو عصيانهم واعتداؤهم، وأن من ذلك عدم تناهيهم عن المنكر فيما بينهم؛ لتحذر هذه الأمة سبيلهم الوخيم، ويبتعدوا عن هذا الخلق الذميم، ويتضح من ذلك أن هذه الأمة متى تخلقت بأخلاق كفار بني إسرائيل المذمومة استحقت ما استحقه أولئك من الذم واللعن؛ لأنه لا صلة بين العباد وبين ربهم إلا صلة العبادة والطاعة.

فمن استقام على عبادة الله وحده وامتثال أوامره وترك نواهيه، استحق من الله الكرامة، فضلًا منه وإحسانًا، وفاز بالثناء الحسن والعاقبة الحميدة، ومن حاد عن سبيل الحق استحق الذم واللعن وباء بالخيبة والخسران، وقد صح عن النبي ﷺ أنه قال: من رأى منكم منكرا فليغيره بيده، فإن لم يستطع فبلسانه، فإن لم يستطع فبقلبه، وذلك أضعف الإيمان رواه مسلم –رحمه الله– في صحيحه.

وروى مسلم أيضًا عن ابن مسعود –رضي الله عنه– قال: قال رسول اللهﷺ: ما من نبي بعثه الله في أمة قبلي إلا كان له من أمته حواريون وأصحاب يأخذون بسنته ويقتدون بأمره، ثم إنها تخلف من بعدهم خلوف يقولون ما لا يفعلون ويفعلون ما لا يؤمرون، فمن جاهدهم بيده فهو مؤمن، ومن جاهدهم بلسانه فهو مؤمن، ومن جاهدهم بقلبه فهو مؤمن، وليس وراء ذلك من الإيمان حبة خردل.

فاتق الله أيها المسلم في نفسك، وجاهدها لله واستقم على أمره، وجاهد من تحت يديك من الأهل والذرية وغيرهم، وَأْمُر بالمعروف وانه عن المنكر حسب طاقتك في كل مكان وزمان، عملا بهذه الأدلة الشرعية التي ذكرتها لك آنفًا، وتخلق بأخلاق المؤمنين واحذر من أخلاق الكافرين والمجرمين، واحرص جهدك على نجاتك ونجاة أهلك وإخوانك المسلمين، كما قال عز وجل: وَأْمُرْ أَهْلَكَ بِالصَّلاةِ وَاصْطَبِرْ عَلَيْهَا [طه:132].

وقال سبحانه:

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا قُوا أَنْفُسَكُمْ وَأَهْلِيكُمْ نَارًا وَقُودُهَا النَّاسُ وَالْحِجَارَةُ عَلَيْهَا مَلائِكَةٌ غِلاظٌ شِدَادٌ لا يَعْصُونَ اللَّهَ مَا أَمَرَهُمْ وَيَفْعَلُونَ مَا يُؤْمَرُونَ [التحريم:6]

وروي عن النبي ﷺ أنه صعد المنبر فحمد الله وأثنى عليه وقال: يا أيها الناس، إن الله يقول لكم مروا بالمعروف وانهوا عن المنكر قبل أن تدعوني فلا أجيبكم، وتسألوني فلا أعطيكم، وتستنصروني فلا أنصركم أخرجه ابن ماجه وابن حبان في صحيحه، وهذا لفظ ابن حبان.

والمعروف يا أخي هو كل ما أمر الله به ورسوله، والمنكر هو كل ما نهى الله عنه ورسوله، فيدخل في المعروف جميع الطاعات القولية والفعلية، ويدخل في المنكر جميع المعاصي القولية والفعلية، ثم اعلم يا أخي أن كل مسلم راع على من تحت يده ومسئول عن رعيته، كما ثبت في صحيح البخاري –رحمه الله– عن ابن عمر–رضي الله عنهما–عن النبي ﷺ أنه قال: كلكم راع وكلكم مسئول عن رعيته، فالإمام راع ومسئول عن رعيته، والرجل راع في أهل بيته ومسئول عن رعيته، والمرأة راعية في بيت زوجها ومسئولة عن رعيتها، والعبد راع في مال سيده ومسئول عن رعيته، ثم قالﷺ: ألا فكلكم راع ومسئول عن رعيته.

فاتق الله يا عبدالله وأعد جوابًا لهذا السؤال قبل أن ينزل بك من أمر الله ما لا قبل لك به، والله المسئول أن يهدينا جميعًا صراطه المستقيم، وأن يوفقنا وسائر المسلمين للقيام بأمره، والثبات على دينه، والتآمر بالمعروف، والتناهي عن المنكر، والتواصي بالحق والصبر عليه بصدق وإخلاص، إنه ولي ذلك والقادر عليه، وصلى الله وسلم على عبده ورسوله نبينا محمد وآله وصحبه ومن اهتدى بهداه.

**نشرت بمجلة الجامعة الإسلامية بالمدينة المنورة في العدد الرابع السنة الأولى ربيع الأول سنة 1389هـ. (مجموع فتاوى ومقالات الشيخ ابن باز 3/ 264)**

# Ibsa Gbaabaa Waa’e Sommana

بسم الله الرحمن الرحيم

 Galatni Rabbii guddaatiif ha itau. Salaatniif nagaan Rabbi ergamaa isaa kan ta'an nabiyyii keenya Muhammad errattiif ahlii(maatii) isaanii akkasumas hiriyoota (sahaaboota) isaanii errati habu'u .

 Ergaan kanaa gadi ibsamu waahee sooma RAMADAANAA, maalummaa isaa, seera isaa tiif sooma ilaalchisuudhaan Akkaataa nama soomuudhaaf dirqamamuu fi waan sooma keenya balleessuu danda'u, akkasumas waan matadurее kanaan walitti dhufu ilaalchisuudhaan gargaarsa Rabbii tiin ergaa xiqqoo isinii dhiheessinaa.

 sooma jechuun ganama subhii (fajrii) dhaan dura jalqabee hamma biiftuun seentutti (magriiba itti) waan sooma balleessu erraa of eeguudhaan Rabbii jecha Ibaadaa dalaga erra oolu.

 Baatii (ji'a) Ramadaanaa soomuun amuuda (arkaana) Islaamaa guguddaa keessaa isa tokko.

Ergamaan Rabbii Muhammad akkana jedhani « Islaamni amuudoota waan shan erraa uumame. Jerris: -Allah (Rabbiin) male kan dhugaatti gabaramu hin jiru jedhanii fi Muhammadis ergamaa Rabbiiti jedhanii SHAHAADAA bahuu, SALAATA seeraan salaatuu, ZAKAA seeraan kennuu, RAMADAANA soomu, fi HAJJII gochu dhaaf gara mana Rabbiin keenya ijaarsise (ka'ibaa bira) makkaah dhaquu. »Hadiisa kana imaam Bukhaarii fi imaamu Muslim itu katabe.

 Waan Sooma Keenya Balleessan keessaa

 Soomaan tokko waan sooma isaa balleessu IRRAANFII dhaan yokin WALLAALUMAAN akkasumas DIRQAMAAN yoo dalage (hojjate) soomni isaa HIN BADU.

Qur'aanni Rabbi keenyaas akkana jedha: - [...(jedhaa) Yaa Rabbii keenyaa ! waan irraanfanneefi dogongorree dalagnetti nu hin qabin. ]

{ Qalbiin isaa iimaanaan kan guutame ta'ee (afaaniin waan Rabbi erraa isa baasu jecha kufrii) nama dirqamamee haasa'e male }

 Muslimni tokko yoo haasaa waan jeche kufri ta'e afaani bahe nama irraanfatee yokin wallaaluu dhaan yokin immoo dirqqamaan yoo ta'e male Rabbittii bahun isaa hin hafu.

 Ragaa kanaan nammi sababa sadan kana keessaa tokkoon Sooma balleesse itti hin gaafatamu Jedha.

{ Waan dogongortaniif balleessi isin erra hin jiru. Waan beekaa dalgdanitti immoo balleessi isin erra jira...}

 kanaafu namni sooma erra jiru tokko irranfatee yoo nyaates yoo dhuges soomni isaa hin badu.

 Biiftuun waan seente (waan dhihe) se'ee yokin immoo waan hin ifne ( lafti ammallee halkani) jedhee yoo waa nyaate yokin dhuge soomni isaa hin badu. Kunis waan wallaalumaan dalagameefi.

 Afaan lulluqqataa yemmuu jiru yoo diqqoo bisaan liqimse waan inni barbaade hin dalgne gatii ta'eef soomni isaa hin badu.

 Nammi sooma erra jiru tokko rafiitii keessa wamti namni ittiin uumamu (maniyyi, sperm) cidhaan isaatiin yoo bahe soomni isaa hin badu. Kunis waan inni barbaacha ofiitiin hin dalagneefi.

Wamti sooma keenya balleessanu waan seddeeti

1 Abbaan manaa fi haati manaa waliin quunnamuu (wal-qunnamti saala).

Namni soomni Ramadaanaa dirqamaa itti ta'e soomaa jiru guyyaa soomaatti haadha manaa ofiitii wojjin akkasumas abbaa manaa ofii wojjin wal-quunnamtii saala dalaguun sooma jeraa balleessa.

 Kanaafuu sooma guyyaa sana bade yaroo biraa eddoo busuun dirqama. Kanaa wojjinis eddo buusaa kam bira dabaluunis erraa eegama.

 Kunis nama gabrummaa keessa jiru gabrummaa erraa bilisa baasuu. Yoo hin arganne immoo

 Baatii(ji'a) lama guutuu walitti aansuudhaan soomuu. Yoo hin dandeenye immoo rakkataa muslimootaa (miskiina) jaatama tokkoon tokkoon jeraa nyaata yeroo tokkoo nyaachisuudha.

2 cidhaan ofiitti bubu'uu dhaan yokin niitiif namtichi waliin xabachuu dhaan, wal xuxxuquu dhaan akkasumas wal dhungachu dhaaf waan fafakkaatuun fer-ijaa (sperma) of keessaa baasuun sooma cabsa.

3 Waan xuuxamu waan akka tamboo, sujaaraa fafakkaatuufi waanuma ilma namaa miidhu nyaachuunis dhuuguunis sooma ballessa

4 waan eddo nyaataa bu'uu danda'anu Waan akka lilmoo(marfee) giidoo namaa kennuu fudhachuun, waraanamuun sooma balleessa.

Qorichoota(dawaa) waan haala nyaata hin qabne fudhachuun dhowwaa hin qabuu.

Yollee mi'aan qorichachaa kokkee keessaa itti beekmellee sooma hin balleessu.

5 Dhiiga fudhachuu Namni sooma erra jiru tokko dhukubssatee jennaan mana yaalaatti yoo dhiigni kennamee fi soomni isaa hin bada.

6 Dhiiga baatii baatii dhaan (ji'atti) gennootatti dhufuu (xurii Laguu) fi Dhiigni yeroo dahaa (dhiiga dahaa) yoo itti dhufe sooma soomuun hin dhowwama , soomas hin balleesa

7 Waagmtii (hijaamaa) Dhiiga dhukkubaa of keessaa gadi naquu (baasuun) soomaa balleessa.

 Hata'u male waan akka ilkkaan buqqifachuu, dhiigni funyaaniin bahuu (finiinsaa) kun hijaamaa waliin wan wal hin fakkaaneef barbaacha ofiitiinis waan hin baanef sooma hin cabsu.

8 Barbaacha ofiitiin quba afaan kaa'atanii of balaqqamsiisuun (hoqqaasisuun) sooma hin cabsa.

 Kanaan achi ituu hin barbaadin yoo hoqqaasise soomni hin badu .

والله أعلم وصلى اللهم على نبينا محمد وعلى آله وصحبه وسلم

Source:- Written by sheikh muhammed bin salih Al’usaimeen (rahimehullah)

Translated by AbuFawzaan Ahmad

------------*********____________

# ሓጺር መብርሂ ብዛዕባ ጾም

بسم الله الرحمن الرحيم

***ብሽም ኣላህ ኣል ራህማን ብጣዕሚ ራህራሀ ዝኾነ***

ምስጋና ነዚ ዓለም ኩሉ ዝፈጠረ ኣላህ ግቡእ'ዩ። ሰላትን ሰላምን ኣብ ልዕሊ ነቢዩና ሙሓመድ፤ ስድረኦምን ከምኡ 'ዉን ሰሓባታቶምን ካብ ኣላህ ይውረድ።

እዚ ብዛዕባ ፆምን ሕግታቱን፤ ኩነታት ሰባት ብኣንፃር ፆም ፤ ፆም ዘበላሽዉ ነገራትን ከምኡ ድማ ካልኦት ምስ ፆም ዝተተሓሓዙ ጉዳያትን ንምግላጽ ብሓፂሩ ዝቐረበ መልእኽቲ እዩ::

1.ፆም :- ማለት ፈጅሪ (ወጋሕታ) ካብ ዝወፀ ጀሚሩ ክሳብ ፀሓይ እትኣቱ ካብ ዘፍጥሩ ነገራት ብምቁጣብ ንኣላህ እንግዝኣሉ ዒባዳ እዩ::

2.ወርሒ ረመዳን ምጿም ካብቶም ዓበይቲ ዓንድታት ኢስላም ሓደ እዩ:: ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ከምዚ በሉ ‹ኢስላም ኣብ ሓሙሽተ መሰረታዊ ጉዳያት ዝተሃነፀ እዩ:: (ንሳቶም ድማ) ብጀካ ኣላህ ብሓቂ ከግዝእዎ ዝግባእ ኢላህ ከምዘየለ ከምኡ 'ዉን ነቢዩና መሓመድ ሰ.ዐ.ወ ልኡኽ ናይ ኣላህ እዮም ኢልካ ምምስካር፤ ሶላት ስርዓት ሓሊኻ ምስጋድ፤ ዘካ ምሃብ፤ ወርሒ ረመዳን ምጿም፤ ኣብቲ ዝኸበረ በይቱላህ ሓጅ ምግባር›

(ቡኻሪን ሙስሊምን ዝፀብፀብዎ)

## ፆም ዘበላሽዉ/ ዘፍጥሩ/ነገራት

ፀዋሚ ሰብ ካብቶም ዘፍጥሩ ነገራት ረሲዑ፣ ብዘይፍልጦ ወይ ድማ ተገዲዱ እንተደአ ፈፂሙ እቲ ፆሙ ኣይበላሸዉን (ኣፍጢሩ እዩ ኣይበሃልን) ምክንያቱም ኣላህ ከምዚ ኢሉ እዩ::

*‹‹..... (በሉ) ኦ ጎይታና፣ እንተረሲዕና ወይ እንተስሒትና ኣይትሓዘልና (ኣይትቕፃዓና)» ኣልበቀራህ 286*

*‹‹..... ፤ልቡ ብእምነት (ኢማን) ዝረግአ ኮይኑ (ናይ ክሕደት ቃል ንክዛረብ) ዝተገደደ ሰብ ጥራሕ እንተተርፍ» ኣል ነሕል 106*

*‹‹..... ኣብ ዝተጋገኹም ሓጥያት የብልኩምን፣ ግና ልብታትኩም ዝፈለጡ ብዝገበርዎ (ሓጢያት) ኣለኩም...›› ኣል ኣሕዛብ 5*

ስለዙይ ፀዋሚ ሰብ ረሲዑ እንተበሊዑ ወይ እንተሰትዩ፣ ኮነ ኢሉ ስለዘይኮነ እቲ ፆም ኣይፈረስን እዩ::

ፀሓይ ዝኣተወት መሲሉዎ ወይ ድማ ፈጅሪ ዘይወፀ መሲሉዎ እንተበሊዑ ወይ እንተሰትዩ ፆሙ ፈሪሱ ኣይበሃልን:: ምክንያቱም ድማ ብዘይፈልጦ ስለዝኾነ::

ከይሓሰበ ኣፉ እንተጉመፅምፅ ማይ ናብ ጎረርኡ እንተኣትዩዎ ኣፍጢሩ ኣይበሃልን:: ምክንያቱም ኮነ ኢሉ ኣይኮነን::

ደቂሱ እንክሎ ዘርኢ ፈሳሲ (ኢሕቲላም) እንተወፂኡዎ ኣየፍጠረን ምክንያቱም ብናቱ ምርጫ (ድልየት) ስለዘይኮነ።

### ዘፍጥሩ/ ፆም ዘበላሽዉ/ ነገራት ሸሞንተ እዮም::

1. ስጋዊ ረኽቢ :- ወርሒ ረመዳን ንክፀዉም ግዴታ ዝኾኖ ሰብ ኣብ ቀትሪ ስጋዊ ረኽቢ እንተፈፂሙ በዚ ተግባሩ ፆሙ ይበላሸዉ:: ብምጿኡ ድማ ናይታ መዓልቲ ንሳ ፆም ኣብ ካልእ ግዜ ንክፀዉም ግዴትኡ/ግቡኡ/ ካብ ምጿኡ ንላዕሊ ከቢድ መከሓሓሲ/ከፋራ/ ንክኽፍል ድማ ዋጂቡ እዩ:: እቲ መከሓሓሲ/ከፋራ/ ባርያ ነፃ/ሑር/ ምባል፤ ተዘይረኺቡ ክልተ ወርሒ ብተኸታታሊ ምፅዋም፤ እንተዘይኪኢሉ ድማ ስድሳ መሳኪን ንክምግብ ግዴትኡ እዩ::

2.ብልዕቲ ብምትንካፍ ወይ ድማ ምስ ተቃራኒ ፆታ ብምትሕስሳይ›: ብምትሕቁቃፍ ወይ ምስዕዓምን ካልኦት ዝኣመሰሉ ኩነታትን ዘርኢ ምፍሳስ

3.ከም ሽጋራ ዝኣመሰሉ ዝተኩ ነገራት ሓዊስካ ካልኦት ዝጠቕሙ ኮኑ ዝጎድኡ ነገራት ምብላዕ ወይ ምስታይ ፆም ካብ ዘበላሽዉ ነገራት ይሰርዑ::

4.ኣብ ክንዲ ምግቢ መተካእታ ኮይኖም (ሓይሊ ዝህቡ) መራፍእ ምዉጋእ ምክንያቱም ከምዚ ዓይነት መድሓኒታት ሙሉእ ናይ ምግቢ ጥቕሚ ክህቡ ስለ ዝኽእሉ እዩ:: ናይ ምግብነት ባህሪ ዘይብሎም መድሓኒታት ግና ብመርፍእ ኣብ ጭዋዳታትና ኮነ ብሰራዉር ደምና እንተተወጊእና ዋላ'ኳ ጣዕሚ ናይተን መድሓኒታት ኣብ ጎሮርና እንተተፈለጠና 'ውን እቲ ፆም ኣይበላሸዉን (ኣይፈርስን)::

> **ፀዋሚ ፈጅሪ ንኽወፅእ ቁሩብ ክሳብ ዝተርፎ ስሑር ምድሓር፤ ፀሓይ እንተኣትያ ድማ ንምፍጣር ክቕልጥፍ ይፍተወሉ:: ከምኡ ድማ ኣብ እዋን ፊጥሪ እንተረኺቡ ብሸዊት ተምሪ፤ ተዘየለ ብዝኾነ ዓይነት ተምሪ፣ ተዘይረኺቡ ብማይ፣ ተዘይኮይኑ ብዝኾነ ሓላል ምግቢ፣ ተዘይረኺቡ ክሳብ ዝረክብ ብልቡ ምፍጣሩ ይንይት::**

5.ደም ምዉሳድ:- እንተደአ ሓደ ፀዋሚ ደም ፈሲስዎ ኣብ ክንዲኡ መተካእታ ድማ ደም ዘድልዮ ኮይኑ ደም እንተተዋሂብዎ ፆሙ ይበላሸዉ::

6.ደም ወርሓዊ ፅግያትን ደም ወሊድን ምፍሳስ::

7.ብማሕጎማን ብዝኣመስሉ ነገራትን ደም ካብ ሰዉነት ምዉፃእ፤ ኮይኑ ግና ከም ነስርን ስኒ ምንቃልን ዝኣመሰሉ ብናይ ባዕሎም ዉሽጣዊ ድፍኢት ዝክሰቱ ፍሰት ደማት ምስ ማሕጎማ ተመሳሳልነት ስለዘይብሎም ፆም ኣየባላሸዉን::

8.ኮነ ኢልካ ተምላስ ምምላስ: ፆም ዘበላሸዉ እንተኸዉን; ካብ ድልየትካን ቁፅፅርካን ወፃኢ ብዝኾነ እንተኣምሊሱካ ግና ፆምካ ኣበላሸዉን::

### ምስ ፆም ዝዛመዱ ካልኦት ተወሳኺ ጠቀምቲ ነጥብታት

ፀዋሚ ምሕፃብ ግዴታ ዘግብረሉ (ጀናባ) እንክሎ ንምጿም ክንይትን ድሕሪ ፈጅሪ ክሕፀብን ይበቕዐሉ፥ዩ::

ካብ ወርሓዊ ፅግያትን ደም ወሊድን ቅድሚ ፈጅሪ ዝፀረየት ጓል ኣነስተይቲ ክትፀዉም ዋጅባ እዩ:: እቲ ምሕፃብ ድሕሪ ፈጅር እንተኾነ 'ዉን

ፀዋሚ ስኑ ከንቅል፡ ቁስሉ ክሕከም፡ ናብ ዓይኑ ይኹን ናብ እዝኑ ብጠብታ ዝዉሰዱ መድሓኒታት ክጥቀም ይፍቀደሉ:: ልክዕ ከምዘይፀዉም ሰብ ሲዋክ ንጉሆ ኮነ ምሸት (ድሕሪ ፋዱስ) ሱና ስለዝኾነ ንክጥቀም ይበቕዓሉ::

ፀዋሚ ናይ ሙቐት /ዋዒ/ ፤ናይ ፅምኢ ብርታዕን ንክቕንስሉ ብዝሑል ማይ ምሕፃብ ከምኡ ዉን /ሙከየፍ/ መሳርሒታት መዝሓሊ ኣየር ክጥቀም ይብቅዓሉ እዩ::

ፀዋሚ ክዕፍንዎ ካብ ዝኽእሉ (ኣስሚ) ዝኣምሰሉ ሕማማት ንዝኽሰት ሕፅረት ኣየር ንምክልኻል ብኣፍ ዝሰሓቡ (ሕፅረት ኣየር መከላኸሊ) መድሓኒታት ንክጥቀም ይፍቀደሉ እዩ::

ፀዋሚ ከናፍሩ እንተደሪቁ ብማይ ከርሕሶ፣ ኣፉ እንትነቒፁ ክጉፅጉፅ ዘበቕዐሉ እንትኽዉን ማይ ኣብ ጎሮሮኡ ዉሽጢ ምምልላስ ግና ክጥንቀቕ ይግባእ::

ፀዋሚ ፈጅሪ ንኽወፅእ ቁሩብ ክሳብ ዝተርፎ ስሑር ምድሓር፤ፀሓይ እንተኣትያ ድማ ንምፍጣር ክቕልጥፍ ይፍተወሉ:: ከምኡ ድማ ኣብ እዋን ፊጥሪ እንተረኺቡ ብሸዊት ተምሪ፤ ተዘየለ ብዝኾነ ዓይነት ተምሪ፣ ተዘይረኺቡ ብማይ፣ ተዘይኮይኑ ብዝኾነ ሓላል ምግቢ፤ ተዘይረኺቡ ክሳብ ዝረክብ ብልቡ ምፍጣሩ ይንይት::

ፀዋሚ ብሰናይ ድልየት ዝፍፀሙ (ሱና) ፅቡቓት ተግባራት ከብዝሕ፤ ኩልኩላት ነገራት ግና ብሙሉኦም ክርሕቕ ይግባእ::

ፀዋሚ ዋጂብ ዝኾኑ ተግባራት ከዘዉትር ካብ ሓራማት ክርሕቕ፤ ሓሙሽተ ወቕቲ ሰላት ኣብ ሰዓተን ክሰግድ፤ ጀማእ ሶላት ዝምልከቶ እንትኾይኑ ምስ ጀመእ ክሰግድ፤ ሓሶት፤ ሕምቀት፤ ምትላል፤ ስራሕቲ ሪባ (ወለድ) ከምኡ 'ዉን ኩሉ ሓራም ዝኾነዘረባ ይኹን ተግባር ክገድፍ ይግባእ:: ምክንያቱም ነብዩ ሰ.ዐ.ወ ከምዚ ስለዝበሉ "ሓሶት ዘረባ፣ ብሓሶት ምስራሕ ከምኡ 'ዉን ሀስነት ዘይገደፈ፤ ምግቡ ይኹን ዝስተ ምግዳፉ ንኣላህ ጉዳዩ ኣይኮነን::" ቡኻሪን ሙስሊም ዝፀብፀብዎ::

ኣብ መወዳእታ ምስጋና ንጎይታ ዓለማት ኣላህ ግቡእ እዩ፤ ሰላትን ሰላምን ኣብ ልዕሊ ነብይና ሙሓመድ፡ ስድረኦምን ሰሓባታቶምን ኣብ ኩሎም ይኹን::

*ምንጭ:-*

Brief Notes about Fasting From Sheikh Muhammed bin salih Al'u-saimeen (rahimehullah)

Translated by Abdulwasie Abrar

------------*********____________

[“ጌታዬ ሆይ እውቀትን ጨምርልኝ” በል ! ]

**ነሲሓ አካዳሚ ለመመዝገብ**

**ብዙዎችን በያሉበት ተጠቃሚ የሚያደርግ የትምህርት ተቋም !**

*www.nesiha.tv/acadamy*

**ኢስላማዊ ዕውቀት ለሁሉም**

Frequency - 11555

Symbol Rate - 27500

Polarization - vertical

Fec - 5/6